በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድኅረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

# በባህር ዳር ከተማ በሚገኙ የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ-ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ

በ
ማስተዋል ወርቁ

ሰኔ 1999 ዓ.ም.

# በባህር ዳር ከተማ በሚገኙ የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ-ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለድኅረ-ምረቃ
ትምህርት ቤት የቀረበ

አማርኛን በማስተማር (TEAM) የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ

በ

ማስተዋል ወርቁ

ሰኔ 1999 ዓ.ም.

# በባህር ዳር ከተማ በሚገኙ የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ-ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ

በ

ማስተዋል ወርቁ


በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት


የድኅረ-ምረቃ መርሃ ግብር

## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

1. [illegible] ________ ________
   አማካሪ ፊርማ
2. [illegible] ________ ________
   የውስጥ ፈተኝ ፊርማ
3. [illegible] ________ ________
   የውጭ ፈታኝ ፊርማ

# ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምስጋና....i

የሠንጠረዥ ዝርዝር....ii

የአባሪ ዝርዝር....v

አጠቃሎ....vi

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ....1

1.2 የጥናቱ ዓላማ ....4

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ....4

1.4የጥናቱ ክልልና ገደብ ....5

1.5 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ብያኔና ምህፃረ ቃላት....6

ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

2.1 የሥርዓተ ፆታና የፆታ ጽንሰ ሐሳብ....7

2.2 ሥርዓተ ፆታ ከተግባቦት ጋር ያለው ተዛምዶ....9

2.2.1 ቃላዊ ተግባቦትና ሥርዓተ ፆታ....9

2.2.2. ቃል-አልባ ተግባቦትና ሥርዓተ ፆታ....11

2.3 በክፍል ውስጥ መስተጋብር የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ....12

2.3.1 የክፍል ውስጥ መስተጋብር....12

2.3.2 የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ....13

2.4 በመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ የሚንፀባረቁ አድሏዊ ባህርያት....19

2.4.1 የመምህራን ምጋቤ ምላሽ....19

2.4.1.1 አዎንታዊ ምጋቤ ምላሽ....22

2.4.1.2 አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ....24

2.4.2 የመምህራን ጥያቄ አጠያየቅ....25

2.4.3 የመምህራን የቆይታ ጊዜ አሰጣጥ....28

2.4.4 የመምህራን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ....29

2.5 መምህራን ለሴትና ወንድ ተማሪዎች የሚኖራቸው
ግምት ከሥርዓተ ፆታ አያያዝ ጋር ያለው ተዛምዶ....32

2.6 የመምህራንን የሥርዓተ ፆታ ግንዛቤ ለማዳበር የሚረዱ ነጥቦች......................34
2.7 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት......................................................................37
ምዕራፍ ሦስት፡- የጥናቱ ዘዴ
3.1.ተጠኝዎች.........................................................................................40
3.2.የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ..............................................................41
3.2.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ...................................................................41
3.2.2 የፅሁፍ መጠይቅ ..........................................................................43
3.2.2.1 የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ.......................................................43
3.2.2.2. የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ.....................................................43
3.2.3. ቃለ መጠይቅ...............................................................................44
3.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ ....................................................................44
ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ
4.1 የጥናቱ መረጃ ምንጮች (የተጠኝዎች) አጠቃላይ ገለጻ.................................46
4.2 የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበር........................48
4.2.1 የመምህራን የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት.................................................48
4.2.2 የመምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ.....................................................58
4.2.3 የመምህራን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ.....................................................71
4.2.4 የመምህራን የቆይታ ጊዜ አሰጣጥ........................................................83
ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና አስተያየት
5.1 ማጠቃለያ ......................................................................................89
5.1.1 የመምህራንን የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት በሚመለከት..................................90
5.1.2 የመምህራንን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በሚመለከት......................................90
5.1.3 የመምህራንን የቆይታ ጊዜ አመዳደብ በሚመለከት.....................................91
5.1.4 የመምህራንን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ በሚመለከት.....................................91
5.2 አስተያየት .......................................................................................92
ሙዳየ ቃላት...........................................................................................93
ዋቢ ጽሑፎች..........................................................................................94
አባሪዎች..........................................................................................101-128

# ምስጋና

ለጥናቱ መሳካት በማንኛውም ጊዜና ቦታ ውይይት ሳይለያቸው ጊዜያቸውን ሳይሰስቱ ሥራው ዳር እንዲደርስ ላበቁት ለመምህሬና ለአማካሪዬ ለአቶ ዓለም እሸቱ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርበለሁ፤ በተለይ ፈጣን የሆነ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጣቸውን ሳላደንቅ አላልፍም፡፡

ሥራውን መሥራት ከጀመርኩበት ቀን አንስቶ የቁሳቁስም ሆነ የሞራል ድጋፍ ልገሳቸውን ላልነፈጉኝ ለውድ አባቴ ለመምህር ወርቁ አድማስ ቦጋለ፣ ለውድ እናቴ ለመምህርት የሽጥላ አምባዬ እና ለእጮኛየ ለጉልላት መንበረ ጥልቅ ፍቅሬን ልገልጽ እወዳለሁ፡፡ እንዲሁም የጥናት ወጭዬን ለሸፈነልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ጥናቱን ለማካሄድ ካሰብኩበት ጊዜ አንስቶ አስፈላጊውን መጻሕፍት በማዋስና አስተያየቶችን በመለገስ ከጎኔ ላልተለዩት ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለሚያስተምሩት ለቀድሞ መምህሬ ለአቶ ማረው ዓለሙ ያለኝን ክብር መግለጽ እወዳለሁ፡፡

የጥናቱን መረጃ ለመሰብሰብ በሦስቱም ትምህርት ቤቶች በተደረጉ ምልከታዎች አብረውኝ ቦታው ድረስ በመሄድ በጎ ትብብራቸው ላልተለየኝ ጓደኞቼ ለአሰፋ ወረታ እና ለምስራቅ ካሣ ምስጋና ይድረሳቸው፡፡

ለጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የማቀናበሪያ ብልሃት በተመለከተ ሙያዊ ምክራቸውን ላካፈሉኝ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሥነ ልቦና ክፍለ ትምህርት መምህር የሆኑት አቶ ረዳ ዳርጌ፣ አቶ ዳዊት አስራት እና አቶ ዳዊት ጥበቡን እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሥነ ልቦና ትምህርት ክፍል ለሚያስተምሩት አቶ ታምሬ አንዷለምን ሳላመሰግን አላልፍም፡፡

ይህ ሥራ ለንባብ እንዲበቃ የትየባ ሥራውን ላከናወኑልኝ ለወ/ት ትዝታ ከበደና ወ/ት ጤናዬ ታደሰ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

በመጨረሻም በምክር ከጎኔ ላልተለዩኝ ጓደኞቼ በተለይ ለተድላ ኩታየ ምስጋናዬን ሳቀርብ ደስታ ይሰማኛል፡

# የሠንጠረዥ ዝርዝር

ሠንጠረዥ

ገጽ

1. የተጠኝ መምህራን ብዛት፣ ፆታና የትምህርት ደረጃ ....................46
2. የተጠኝ መምህራን የአገልግሎት ዘመን ከስልጠና መስክ አንፃር....................47
3. የተጠኝ ተማሪዎች ብዛት፣ ከዕድሜ ከፆታና ከትምህርት ቤት አኳያ....................47
4. መምህራኑ ጥያቄ የጠየቋቸው ተማሪዎች ብዛት ....................48
5. የመምህራን ጥያቄ የፆታ ትኩረት....................48
6. ጥያቄ የተጠየቁ ተማሪዎች ....................49
7. የተማሪዎች የመጠየቅ ተነሳሽነት ....................50
8. ለጥያቄዎች የመምህራን አነሳሽነት ....................50
9. በተደጋጋሚ ቀላል ጥያቄዎችን መጠየቅ....................51
10. ቀላል ጥያቄዎችን ብቻ ስለመጠየቅ....................52
11. ከባድ ጥያቄዎችን ስለመጠየቅ....................52
12. ስም ጠርቶ መጠየቅ ....................53
13. የመምህራን ስም ተኰር አጠያየቅ....................53
14. በስም እየጠሩ ማሳተፍ....................54
15. ከስም ጥሪ በፊት ጥያቄ ማቅረብ....................54
16. የመምህራን ስም አጠራር ....................55
17. ስም ከጠሩ በኋላ ጥያቄ መጠየቅ ....................55
18. የመምህራን ከስም በፊት የጥያቄ አጠያየቅ....................56
19. የጥያቄ አጠያየቅ መረጃ ከቲ-ስሴት አንጻር....................56
20. አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ....................58
21. ለተማሪዎች መልስ የተሰነዘሩ አወንታዊ ምጋቤ ምላሾች....................59
22. የመምህራን አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ....................59
23. የተሳሳተ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች የሚሰጥ ምጋቤ ምላሽ....................60
24. ለተማሪዎች የተሳሳተ መልስ የሚሰጥ የመምህራን ትችት....................61
25. ሐሳብን በነፃነት መግለጽ ስለመቻል....................62
26. የመምህራን ማበረታቻ (ሙገሳ)....................62

27. ለጥሩ ባህርያት የመምህራን ማበረታቻ.....63
28. ከተሳትፎ ይልቅ ለጥሩ ባህርይ የሚሰጥ ማበረታቻ.....63
29. የመምህራን አስተያየት በክፍል ውስጥ.....64
30. በግል ተማሪዎችን በመጥራት አስተያየት መስጠት.....64
31. ምንም ምጋቤ ምላሽ አለመስጠት.....65
32. ለተማሪዎች መልስ የመምህራን ምጋቤ ምላሽ አለመኖር.....65
33. ምጋቤ ምላሽ ያልተሰጡ ተማሪዎች.....66
34. ከመምህራን ምጋቤ ምላሽ አለማግኘት.....66
35. ለተማሪዎች የተሰነዘሩ አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች.....67
36. ከመምህራን የተሰነዘሩ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ.....67
37. በመስተጋብር ወቅት የተሰነዘሩ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ.....68
38. ተማሪዎች ሲሳሳቱ የሚሰጥ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ.....68
39. የመምህራን አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ እጅ ሳያወጡ ከመመለስ አንፃር.....69
40. የመምህራን አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በቲ-ስሌት.....69
41. በተማሪዎች ተሳትፎ የመምህራን ጣልቃ ገብነት.....72
42. የመምህራን ጣልቃ መግባት በተማሪዎች ምላሽ.....72
43. በተማሪዎች ምላሽ የመምህራን ጣልቃ መግባት.....73
44. በሌሎች ተማሪዎች ያልተመለሱ ጥያቄዎች.....74
45. የተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ.....74
46. በመምህራን አሳታፊነት የተሰጡ ትክክለኛ ምላሾች.....74
47. ትክክለኛ መልስ የሰጡ ተማሪዎች.....75
48. የተማሪዎች የተሳሳተ ምለሽ.....75
49. ከተማሪዎች የተሰነዘሩ የተሳሳቱ ምላሾች.....76
50. በመምህራን አሳታፊነት የተገኙ የተሳሳቱ ምላሾች.....76
51. እጅ ሳያወጡ የመለሱ ተማሪዎች.....77
52. እጅ ሳያወጡ የተሳተፉ ተማሪዎች.....77
53. ተማሪዎች እጅ ሳያወጡ ተሳተፉ.....78
54. እጅ ሳያወጡ ተጠይቀው ትክክለኛ መልስ የሚሰጡ.....78
55. በተማሪዎች ፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ተሳትፎ.....79

56. የሁለቱንም ፆታ ተማሪዎች በቡድን ማሳተፍ......................................79
57. ተማሪዎችን በቡድን ሥራ እንዲሳተፉ ማድረግ........................................80
58. ተማሪዎችን በግል እንዲሠሩ ማድረግ ........................................................80
59. ፊትም ሆነ ኋላ የተቀመጡ ተማሪዎችን ማሳተፍ...............................81
60. የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ.......................................................................81
61. የመምህራን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ ውጤት በቲ-ስሴት.......................82
62. የጥያቄ ረዘም ያለ መመለሻ....................................................................83
63. የተማሪዎች መልስ መስጫ ጊዜ...............................................................84
64. የመምህራን ረዘም ያለ መመለሻ ጊዜ አሰጣጥ........................................84
65. መልስ ለመስጠት ለተቸገሩ ተማሪዎች የሚሰጥ ጊዜ.............................85
66. የመምህራን ረዘም ያለ ጊዜ አሰጣጥ....................................................85
67. ለመመለሻ ረዥም ጊዜ ያለመስጠት ሁኔታ..............................................86
68. የተመጣጣኝ ጊዜ አመዳደብ..................................................................86
69. የመምህራን የቆይታ ጊዜ አሰጣጥ በቲ-ስሴት...................................... 87

# የአባሪዎች ዝርዝር


አባሪ ገጽ

1. በመቅረጸ - ምስል የተገኙ መረጃዎች ....................................................101
    ሀ.የመቅረጸ- ምስል ቀረጻ አንድ ....................................................101
    ለ. የመቅረጸ- ምስል ቀረጻ ሁለት ....................................................105
    ሐ.የመቅረጸ- ምስል ቀረጻ ሦስት ....................................................108
    መ.የመቅረጸ- ምስል ቀረጻ አራት ....................................................113
    ሠ.የመቅረጸ- ምስል ቀረጻ አምስት ....................................................115
    ረ. የመቅረጸ-ምስል ቀረጻ ስድስት ....................................................119
2. የመምህር ተማሪ መስተጋብር ማመሳከሪያ ቅጽ ....................................................121
    ሀ. ከምልከታ አንድ እስከ ምልከታ አራት ....................................................121
    ለ. ከምልከታ አምስት እስከ ምልከታ ስምንት ....................................................122
    ሐ.ከምልከታ ዘጠኝ እስከ ምልከታ አስራ ሁለት ....................................................122
3. ለተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ ....................................................123
4. በመምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ ....................................................126
5. ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ ....................................................128

# አጠቃሎ

የጥናቱ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ-ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበራቸውን መመርመር ነው፡፡ ተጠኝዎች በባህር ዳር ከተማ በሚገኙ በጣና ሐይቅ፣ ግዮን እና ፋሲሎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል በ1999 ዓ.ም. አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት በምልከታ፣ በጽሑፍና በቃል መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎቹም ተደጋጋሚነት እንዲኖራቸው ተደርጎ ተተንትነዋል፡፡ ትንተናውም ዓይነታዊና መጠናዊ (Qualitative and Quantitative) ዘዴዎችን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በጥናቱ የተካተቱ ተማሪዎች ቁጥር ወደ መቶኛ ተለውጦ ለማቅረብ በቂ በመሆኑ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘው መረጃ በመቶኛ እየተለወጠ ቀርቧል፡፡ ከሴትና ከወንድ ተማሪዎች የተገኘው ውጤት ያለውን ጉልህ ልዩነት ለማረጋገጥ በቲ-ስሌት ተፈትሿል፡፡ ሌሎች በምልከታና ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ ተገኝተው ለስሌት አመቺ የሆኑ መረጃዎች በመጣኝ ትንተና ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ ሌሎች በክፍት የጽሑፍና የቃል ጥያቄዎች ለተገኙ መረጃዎች ደግሞ ዓይነታዊ ትንተና ዘዴ ተግባር ላይ ውሏል፡፡ በዚህም መሠረት መምህራኑ በርካታ ጥያቄዎችን ለወንድ ተማሪዎች እንደጠየቁ፣ ተማሪዎችን በስም ጠርቶ የማሳተፍ ተሞክሯቸው ደካማ እንደሆነ፣ አሉታዊና ምንም ምጋቤ ምላሽ ያልሰጡበት ሁኔታ በሴት ተማሪዎች ላይ አመዝኖ እንደታየ፣ ወንድ ተማሪዎች በአብዛኛው በሠሩት ሥራ እና ሴት ተማሪዎች ጥሩ ባህርይ ሲያሳዩ እንደሚበረታቱ፣ አወንታዊ ምጋቤ ምላሾች ለወንድ ተማሪዎች አመዝነው እንደታዩ፣ አስተያየቶች ለሴት ተማሪዎች በግል ለወንዶች ደግሞ በክፍል ውስጥ እንደሚነገራቸው፣ ለተማሪዎች መልስ ማሰቢያ ተመጣጣኝ የሆነ ጊዜ እንደማይመድቡ፣ በሴት ተማሪዎች ምላሽ ላይ ጣልቃ እንደሚገቡ፣ በአብዛኛው ፊት የተቀመጡ ሴት ተማሪዎችና ፊትም ሆነ ኋላ የተቀመጡ ወንዶች የተሳትፎ ዕድል እንደሚያገኙ፣ እጅ ሳያወጡ የሚመልሱ ወንድ ተማሪዎች በርካታ እንደሆኑ፣ ሴትና ወንድ ተማሪዎችን በቡድን ሥራ እንደሚያሳትፉ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በማጠቃለያውም ላይ መምህራን ለሥርዓተ-ፆታ አያያዝ ትኩረት በመስጠት በክፍል ውስጥ እንዲተገብሩ ተጠቁሟል፡፡ በመሆኑም መምህራን በሥርዓተ-ፆታ አያያዝ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ለማዳበር የሥራ ላይ ሥልጠና የሚኖርበት ሁኔታ ቢመቻች መልካም እንደሆነ አጥኚዋ ትጠቁማለች፡፡

# ምዕራፍ አንድ
# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የሥርዓተ ፆታ አያያዝ (Gender Treatment) በርካታ ጽንሰ ሐሳቦችን የሚዳስስ ቢሆንም በዋናነት በክፍል ውስጥ መምህራን ሴት እና ወንድ ተማሪዎችን በትምህርት ሂደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማስቻል የሚሰጡትን ምጋቤ-ምላሽ፣ የጥያቄ አጠያየቅ፣ የቆይታ ጊዜ፣የተሳትፎ ዕድል እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ በመሆኑም በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በሚገኙ ሀገራት የሥርዓተ ፆታ አያያዝን በሚመለከት በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዩናይትድስቴትስ፣ካናዳ፣ስዊድን፣ብሪታኒያ፣ ስፔን፣ አውስትራሊያ፣ ኒውዘርላንድ፣ ባንግላዴሽ፣ ኡጋንዳ፣ ማሊ፣ ጊኒ፣ ጋና እና ኢትዮጵያ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

Elliott et al. (2000:141) እና Odaga and Heneveld (1995:1) እንደገለጹት የመማሪያ ክፍል ውስጥ መስተጋብር እና ሥርዓተ ፆታ በእጅጉ ይቆራኛሉ፡፡ የመምህራን አመለካከትና የማስተማር ልምምድ የትምህርት ሂደቱን ዳር ለማድረስ ከሚረዱ ነገሮች ውስጥ በዋናነት ይፈረጃሉ፡፡ በመሆኑም የሥርዓተ ፆታ ልዩነቶች ከመምህራን በሚሰነዘሩ አስተያየቶች ላይ ጎልቶ ይታያል፡፡ በዚህም መምህራን ከወንድ ተማሪዎች ጋር የበለጠ መስተጋብር በማካሄድ ምጋቤ ምላሽ እንደሚሰጡ ጥናቶች አመላክተዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እነ Plessis and et al (2002:76) ሲያብራሩ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ልዩነት ሆነ ተብሎ እና ሳይታሰብ ሊካሄድ ይችላል፡፡ በዚህም ሴቶች እና ወንዶች ወደ ትምህርት ቤት በእኩል ጊዜ ይመጣሉ፣ በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ይመደባሉ፣ ተመሣሣይ ትምህርት በተመሣሣይ መምህራን ይማራሉ፣ ነገር ግን የትምህርት ውጤታቸው የተለያየ ይሆናል፡፡ ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ቢችሉም ከመኖሪያ ቤት ቀጥሎ የትምህርት ቤቱ አካባቢ፣ የመማሪያ ክፍል ሁኔታ እና መምህራን የሚያስተምሩበት መንገድ የመምህራን (ባህርይ እና አመለካከት) ሰፊ ድርሻ አላቸው፡፡

በዩናይትድ ስቴትስ፣ ካናዳ፣ስፔን፣ ስዊድን እና ብሪታኒያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቋንቋ መማሪያ ክፍል መስተጋብር የሥርዓተ ፆታ ልዩነቶች እንደተስተዋሉ ጥናቶች አመላክተዋል፡፡ በዚህም የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን ይበልጥ ትኩረት በማድረግ ማበረታቻ የሚሰጡት ለወንዶች ከመሆኑም በላይ መምህራን ሁለት ሦስተኛ (2/3)ኛ የሚሆነውን ጊዜ

የሚያሳልፉት ከወንዶች ጋር እንደሆነ ያሳያል፡፡ በዚሁ ጥናት ሴት ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ ነፃ ሆነው ሐሳባቸውን መግለጽ እንደተቸገሩ እና ያታዊ ጥቃት በወንድ መምህሮቻቸው እንደደረሰባቸው ጠቁመዋል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ በመቅረፀ-ምስል የተደገፈው ጥናት እንዳመለከተው ለተሳትፎ በተሰጠ ዕድል፣ በቆይታ ጊዜ (Wait time) እና በቃላት ብዛት የወንድ ተማሪዎች ልቆ ታይቷል፡፡ ምልከታው መምህራን 61.3 ከመቶ የሚሆነውን ጊዜ ወደ ወንዶች በአትኩሮት እንደሚመለከቱ አሳይቷል (Coates1993:187-199)፡፡በተጨማሪም ወንድ ተማሪዎች ማበረታቻ የሚሰጣቸው ትክክለኛ መልስ በሚመልሱበት ጊዜ ሲሆን በመምህራኑ የሚተቹት ደግሞ ደካማ ሥራ ሲሠሩ ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ሴት ተማሪዎች ቀለል ያሉ ጥያቄዎች እና ጥቂት የቆይታ ጊዜያት ስለሚሰጡ አነስተኛ የሆነ የመምህራንን ትኩረት ያገኛሉ፡፡ ይህ ትኩረት ያነሰው የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ደግሞ አሉታዊ ወይም መሃል ሰፋሪ የሆኑ አስተያየቶችን የያዘ ነው፡፡ አስተያየቶችም እንደ ማበረታቻ የሚሰነዘሩት ለተጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ በመስጠታቸው ብቻ ሳይሆን በዝምተኛነታቸውና በንፅህና አጠባበቃቸው ላይ ያነጣጠሩ እንደሆነ በመቅረፀ-ምስል የተደገፈው የምልከታ መረጃ አረጋግጧል (Fontana1995:11 እና Diller and Houston1996:41-55)፡፡

Cross (1985) እና Sandler (1987) ን ዋቢ አድርገው Kramer (1991:124) እና Sunderland (1992:288፣1994:149) እንዳስገነዘቡት በአውስትራሊያ፣ ኒውዚርላንድ እና ብሪታኒያ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍል የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያመላክት መምህራን በሚጠይቋቸው ጥያቄዎች፣ በሚሰጧቸው ምጋቤ ምላሾች፣ ተግሳጾች፣ ትችቶች፣ አስተያየቶች፣ እንዲሁም ማበረታቻዎች ላይ ልዩነት ተንፀባርቋል፡፡ በመሆኑም ሴት ተማሪዎች ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ የሚጋበዙት አልፎ አልፎ ከመሆኑም ባሻገር በስም የሚጠሩት እጅግ አናሳ እንደሆኑ ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረጉ ውይይቶች የወንድ ተማሪዎች የበላይነት ጎልቶ ታይቷል፡፡ በዚህም ወንዶች የበለጠ የመናገር ዕድል እንደሚወስዱ፣ በሴቶች ንግግር ላይ በተደጋጋሚ ጣልቃ እንደሚገቡ ከማሳየታቸውም በላይ ለሴቶች የሚሰጡ ርዕሰ ጉዳዮች በጣም ቀላል እንደሆኑ አመላክተዋል፡፡ በዚህም የተነሳ፣ሴቶች በራሳቸው ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት እና የሚያንፀባርቁት በራስ የመተማመን ስሜት ከወንዶች አንሶ መገኘቱን ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡ ይህን ጥናት በሚያጠናክር መልኩ Hatchell (1998:388) በበኩሏ የመማሪያ ክፍል ውስጥ መስተጋብርን በሚመለከት ለሴት ተማሪዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ መምህራን ስም እየጠሩ በሚያሳትፉበት ጊዜ ተማሪዎቹ ለበለጠ ውጤትና ተሳትፎ እንደሚበረታቱ ገልፀዋል፡፡

Plessis et al. (2002:87) እና Riley (1997:7) እንደሚያስገነዝቡት ከአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ በኡጋንዳ፣ ማሊ፣ ጊኒና ጋና የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በክፍል ውስጥ የመምህር ተማሪ መስተጋብር ላይ የተስተዋሉ የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ልዩነቶች በሴትና ወንድ ተማሪዎች ተሳትፎና ችሎታ ላይ ተፅዕኖ አስከትለዋል። ጥናቱ እንደሚያመለክተው መምህራን የተሻለ መስተጋብር የሚያካሂዱ ከወንዶች ጋር በመሆኑ፣ ለጥያቄዎች መልስ መስጫ የበለጠ ጊዜ ለወንዶች ከመስጠታቸውም ባሻገር በርካታ አወንታዊ ምላሾችን እንደሚሰነዝሩ ለማረጋገጥ ተችሏል።

በኢትዮጵያ ያሉትን ሁኔታዎች ደግሞ እነ Hirut (2002:15)፣ Genet(1998:26-27) ፣ Markos and Seyoum (1998:255) እና ሰብለወንጌል (1997:25) በበኩላቸው ሲገልጹ መምህራን ሴት ተማሪዎች በተፈጥሯቸው ዝቅተኛ ችሎታ እንዳላቸው ስለሚገምቱ ለሴት ተማሪዎች የሚሰነዝሩት የክፍል ውስጥ ማበረታቻ ቁጥብ ነው። ከዚህ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ፆታዊ ትንኮሳ ያደርሱባቸዋል። ይህን ሐሳብ በማጠናከር Alem(2003:100-109) ሲያስገነዝብ በኢትዮጵያ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን በርካታ ስድቦችን እና ሒሶችን በሴት ተማሪዎች ላይ ይሰነዝራሉ። ወንድ ተማሪዎችን ግን ከትምህርት ቤት ውጭ ድብደባ ያደርሱብናል በሚል ስጋት መምህራን ነፃ እንደሚያደርጓቸው እና በሴት ተማሪዎች ላይ ፆታዊ ጥቃት እንደሚያደርሱ ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ አረጋግጧል።

ከዚህ አንፃር አጥኚዋን ለዚህ ጥናት ያነሳሳት ጉዳይ በመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ላይ ህፀፆች መስተዋላቸው ብቻ ሳይሆን ችግሩ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ያለውን አተገባበር ገፅታ ምን እንደሚመስል ለማየት መውደዷም ጭምር ነው። በዚህ ረገድ የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ከላይ በተለያዩ ድርሳናት እንደተገለፀው ምንም እንኳ ከውጭ ሃገር በተካሄዱ ጥናቶች ሰፊ ሽፋን ቢሰጠውም በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሁፍ ትምህርት ተቋም እምብዛም ትኩረት አልተቸረውም። በመሆኑም ጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሥርዓተ ፆታን አያያዝ በተመለከተ ሊኖር ለሚገባው የግንዛቤ መሠረት አንዲት ጠጠርም ብትሆን ያበረክታል ተብሎ ይገመታል።

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ (Gender Treatment)ና የክፍል ውስጥ አተገባበርን መመርመር ነው። በዚህም መሠረት ጥናቱ የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች ይኖሩታል። እነሱም፦

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ ፆታ ግንዛቤ ምን ያህል ነው?
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን ይመስላል?
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለሴትና ለወንድ ተማሪዎቻቸው ያላቸው ትኩረት ምን ያህል ይመሳሰላል? ምን ያህልስ ይለያያል?
4. ልዩነት ካለ ልዩነቱ (ከምጋቤ ምላሽ፣ ከጥያቄ አጠያየቅ፣ ከተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ፣ ከቆይታ ጊዜ አንፃር) ምን ይመስላል?
5. የተስተዋለው የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ልዩነት በተራ ቁጥር 4 ከተዘረዘሩት ተላውጦዎች ውስጥ በየትኛው ላይ ጕልቶ ይታያል?

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

Plessis et al. (2002: 86-89) ሲያስገነዝቡ ለመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማነትም ሆነ ውድቀት ከፍተኛ ሚና የሚጫወተው የመምህር- ተማሪ መስተጋብር ነው። ለዚህም የሥርዓተ ፆታ አያያዝን መሠረት ያደረጉ ጥናቶች ሴት እና ወንድ መምህራን ለተማሪዎቻቸው እኩል የሆነ አያያዝ በሚከተሉበት ወቅት የተማሪዎች ችሎታ እንደጨመረ አመላክተዋል። በተጨማሪም Brophy (1983:631) ሲገልጽ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡት ግምት እና አመለካከት ተመሳሳይ ከሆነ በትምህርት ውጤታቸው ላይ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዛቸውን ለመመርመር የሚሞከር በመሆኑ፣የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፤

1. ለመምህራን በተለይም ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የእኩል ተሳትፎ አተገባበራቸው ከሥርዓተ ፆታ አያያዝ አንፃር ምን እንደሚመስል በማስገንዘብ ለወደፊቱ አስፈላጊውን ትኩረትና ለውጥ እንዲያደርጉ አጋዥ መረጃ ሊሠጥ ይችላል፣
2. በሁሉም ፆታ የሚገኙ ተማሪዎች የሥርዓተ ፆታ ግንዛቤያቸው እንዲጎለብትና መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት የሥርዓተ ፆታ አያያዝና አተገባበር በውጤታቸውም ሆነ

በስብዕናቸው ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ተፅዕኖ እንዲገነዘቡ ያደርጋል፣

3. ለትምህርት ቢሮዎች፣ ተቋማትና ትምህርት ቤቶች አስተዳዳሪና ሱፐርቫይዘሮች የመምህራንን የክፍል ውስጥ የሥርዓተ ፆታ አተገባበር ለመገምገም መነሻ ይሆናል፣
4. በተለያዩ ደረጃ ለሚገኙ (በትምህርት ሚኒስቴር እና በክልል) የትምህርትና የሥርዓተ ፆታ ፖሊሲ አውጪዎችና አስፈፃሚዎች መምህራን ያላቸውን የሥርዓተ ፆታ ግንዛቤና አያያዝ በተመለከተ መረጃ ይሰጣል፣
5. በተጨማሪም ተመሳሳይነት ያላቸውን ችግሮች በመያዝ በተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች እና የትምህርት ዓይነቶች ላይ ጥናት ለሚያካሂዱ ቀጣይ ተመራማሪዎች ጠቃሚ ይሆናል።

## 1.4 የጥናቱ ክልልና ገደብ

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበርን መመርመር እንደሆነ ከላይ ተጠቅሷል። ለዚህም ጥናቱ በባህር ዳር ከተማ በሚገኙ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የሚካሄድ ሲሆን፣ እነሱም ጣና ሐይቅ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ግዮን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ፋሲሎ ከፍተኛ ሁለተኛ ትምህርት ቤት ናቸው።

ይህ ጥናት በተመረጡት ሦስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ1999 ዓ.ም. በ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩ መምህራንና በተማሪዎች ላይ የተመሠረተ ነው። ጥናቱ በተተኳሪነት በተመረጡ መምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበር ተዛምዶ ላይ በመፈተሽ ብቻ ያተኩራል፤ በፍተሻውም የመምህራንን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ለመገምገም በሚያስችሉ ተላውጦዎች (ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ፣ የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት፣ የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ፤ እና ተማሪዎች መልስ እስኪመልሱ ባለው የቆይታ ጊዜ ላይ ብቻ) የሚስተዋለውን ሁኔታ በመመርመር ላይ የሚያተኩር በመሆኑ በክፍል ውስጥ መስተጋብር ወቅት በሚካሄዱ ቃላዊ ተግባራት ብቻ የተገደበ ነው።

## 1.5 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ብያኔና ምህፃረ ቃላት

### ሀ. የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ብያኔ

1. ሥርዓተ ፆታ (Gender)፡- የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ታሪክና አካባቢ መሠረት በማድረግ ለሴቶችና ለወንዶች ከሚሰጡ ግምቶች እና ሃላፊነቶች ጋር በእጅጉ ይያያዛል፡፡
2. የሥርዓተ ፆታ አያያዝ (Gender Treatment)፡- በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚካሄድ መስተጋብር መምህራን ሴት እና ወንድ ተማሪዎቻቸውን ከምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ፣ከጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት፣ ከቆይታ ጊዜና ከተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ አንፃር የሚያስተናግዱበት መንገድ ነው፡፡
3. ፆታ (Sex): - ከሥነ ፍጥረታዊ ምድብ ውስጥ የሚካተት ሆኖ በውልደት ጊዜ ሴት ወይም ወንድ የመሆንን ተፈጥሯዊ ሁነት የሚያሳይ ነው፡፡
4. መምህራን የሚሰጡት ግምት (Teachers' Expectation):- መምህራን ለሴት እና ለወንድ ተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛት ትኩረት ያመለክታል፡፡
5. መስተጋብር (Interaction)፡- በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚከናወኑ ተግባራት አማካይነት መምህራን ከተማሪዎች ጋር እና ተማሪዎች ከመምህራን ጋር እርስ በርስ ቃላዊ በሆኑ ባህርያት የሚያካሂዱት ተራክቧዊ የሆነ ትግበራ ነው፡፡
6. የቆይታ ጊዜ (Wait Time)፡- ተማሪዎች መልስ እንዲመልሱ መምህራን የሚሰጡት የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ይህ ቆይታ ደግሞ ተማሪዎች ጥያቄ ተጠይቀው ምላሽ እስኪሰጡ ያለውን ጊዜ ብቻ ይመለከታል፡፡

### ለ. ምህፃረ ቃላት

መ = መምህር

መሴ = ሴት መምህርት

መወ = ወንድ መምህር

ተወ1 = በመጀመሪያ የተጠየቀ ወንድ ተማሪ

$ተወ1_{(1)}$= ለመጀመሪያ ጊዜ የመለሰ

ተሴ1 = ለመጀመሪያ ጊዜ የመለሰች ሴት ተማሪ

# ምዕራፍ ሁለት
# የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

## 2.1 የሥርዓተ ፆታና የፆታ ጽንሰ ሐሳብ

በርካታ ፀሃፍት በ "ሥርዓተ ፆታ" እና "ፆታ" ብያኔዎች መካከል አወዛጋቢ ሁኔታዎች መኖራቸውን ያወሳሉ። እንደ Olson (2000፡237)፣ Subbo (2002፡10) እና Hirut (2002፡6-10) አገላለጽ፣ ተፈጥሮ የግለሰቦችን ፆታ ሲወስን፣ ባህል ደግሞ ለሴት ወይም ለወንድ ፆታ የሚኖርን አመለካከትና ባህርይ ያንፀባርቃል። በእያንዳንዱ ባህል ውስጥ ግለሰቦች ለሁለቱም ፆታዎች የሚሰጡት ግምት ይኖራል። ይህ የሥርዓተ ፆታ ግምት ለሴት ወይም ለወንድ ፆታ የሚሰጡ ባህርያትን እና አመለካከቶችን ያመለክታል።

Datnow and Hubbard (2002፡5)፣ Suzanne (2002፡4) እና Anker (1998፡9) በበኩላቸው ሲያብራሩ ፆታ በሰው ልጅ የህይወት ዘመን ቋሚ የሆነ ሥነ ፍጥረታዊ ባህርይ ነው። በዚህም በሴትና በወንድ መካከል እንደ ህብለ በራሂ (ሆርሞን) እና መራቢያ አካላት ያሉት ሥነ ፍጥረታዊ ልዩነቶች በሁሉም የዓለም ክፍሎች ተመሳሳይ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ የሌላቸው ናቸው። ሥርዓተ ፆታ ደግሞ በሴቶችና በወንዶች መካከል ቋሚ ያልሆኑ፣ የምንማራቸውን ልዩነቶች የሚያሳይ ሲሆን ልዩነቶችም በማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች አማካይነት ሊወሰኑ የሚችሉ ናቸው። የሥርዓተ ፆታ ልዩነቶች ከአገር አገር፣ ከሃይማኖት ሃይማኖት ብሎም ከጊዜ ጊዜ በትምህርት፣ በመንግሥት ፖሊሲ፣ በመገናኛ ብዙሃን እና በመሪዎች አመለካከት ሊለወጥ የሚችል ነው።

ከላይ የቀረበውን ሐሳብ በማጠናከር እነ Lindsey (2005፡4)፣ Santrock (2001፡178)፣ Papalia et al. (1999፡356) እና Andersen (1988፡75) እንዳስገነዘቡት ፆታ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአንድን ሰው ዝርያ እና አካላዊ የሆነውን መለያ ነው። ይህ እውነታ ሥነ ፍጥረታዊ ሲሆን የሥርዓተ ፆታ መገለጫ ግን ሊሆን አይችልም። በዚህም አንድ ሰው ሴት ወይም ወንድ ሆኖ ተወለደ ማለት እሷ ወይም እሱ ሴትነቷ ወይም ወንድነቱ አድሏዊነት አለበት ማለት አይደለም። ሥርዓተ ፆታ ግን በአንድ ማህበራዊ ዐውድ ውስጥ በሴትና ወንድ መካከል ያለውን ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ሥነ ልቦናዊ መገለጫዎችን ያካትታል።

በተጨማሪም Wood and et al (2005፡10)፣ Markhubu (2000፡4)፣ Grant and Sleeted (1999፡129)፣ Anderson and Collins (1998፡83) እና Sunderland(1992፡81፣ 1994፡2-3) በበኩላቸው ሲያብራሩ ሥርዓተ ፆታ ከሴቶች ጋር ብቻ የሚያያዝ ጽንሰ ሐሳብ አይደለም። ይሁን እንጂ በሴቶችና በወንዶች ሊኖሩ ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ ባህርያት ላይ ተመሥርቶ ለሴትነት ወይም ለወንድነት የሚሰጡ ሥነ ልቦናዊ እና ማህበረ ባህላዊ ሚናዎችን ይመለከታል። እነዚህ ሚናዎች ደግሞ በአብዛኛው በማህበረሰቡ ውስጥና በትምህርት ቤቶች በስፋት ይታያሉ። በመሆኑም ሥርዓተ ፆታ የሴቶችና የወንዶችን ማህበራዊና ባህላዊ የሆኑ መገለጫዎችን የሚመለከት ነው፤ መሠረት የሚያደርገውም ማህበራዊ ዐውዱን ሆኖ ውጤቱ ደግሞ የማህበረሰቡን አሻራ ማንፀባረቅ ነው።

በበርካታ መዝገበ ቃላት ውስጥ ሥርዓተ ፆታንና ፆታን አንድ አድርጎ የማቅረብ ሁኔታ ይታያል። ይሁን እንጂ ሥርዓተ ፆታ ተፈጥሯዊ ከሆነው ፆታ በተለየ መልኩ ባህላዊ የሆኑ ልዩነቶችን መሠረት ያደረገ ሲሆን በጊዜ፣ በቦታ፣ በተግባራት፣ በመሣሪያዎች (ቁሳቁሶች) በንግግር ቅርጾች፣ በሰውነት እንቅስቃሴ እና ለአንድ ፆታ በሚሰጥ ግምት ወይም አመለካከት ሊንፀባረቅ ይችላል። እነዚህ ነገሮች በማህበረሰቡ ተቀባይነትን በማግኘታቸው የምንማራቸው ማህበራዊ መገለጫዎች ናቸው። ለሥርዓተ ፆታ ከሚሰጡ ግምቶች አንፃር ልማዳዊ አድሏዊ ባህርያት ከወንዶች ይበልጥ ለሴቶች አሉታዊ ጎናቸው አመዝኖ ይታያል። ባህርያቱም በምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ በመዝሙሮች፣ በአባባሎች ወዘተ ይንፀባረቃል (Annan-Yao(2004፡1)፣ Habtamu et al. (2004፡11) Yonas (2003፡35)፣ Kagan and Tindall(2003፡200)፣ Markos and Seyoum(1998፡240)፣ Disch(1997፡91)፣ Asheroft and Foreman-peck (1994፡149)፣ Feldman (1996፡358)፣ Wilson (1989፡2) እና Birch and Malim (1988፡79))።

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡ ሐሳቦች እንደሚያስገነዝቡት የ "ሥርዓተ ፆታ" እና "ፆታ" ጽንሰ ሐሳቦች አብዛኛውን ጊዜ ሲያምታቱ ይታያሉ። አንዳንድ ጊዜም አንድን ነገር ለመግለጽ የሚያገለግሉ ተመሳሳይ ነገሮች ተደርገው ስለሚወሰዱ አንድን ጉዳይ ለመግለጽ እየተቀያየሩ ጥቅም ላይ ሲውሉ ይታያሉ። ነገር ግን ሁለቱ ሃሳቦች የተለያዩ ናቸው። የፆታንና የሥርዓተ ፆታን ምንነት ለመረዳት የተፈጥሯዊና ማህበራዊ መገለጫቸውን መሠረት ያደረገ ልዩነትን ማጤን ተገቢ ነው። ፆታ የሚባለው በተፈጥሮ ሴት ወይም ወንድ ሆኖ መፈጠርን ያመለክታል። ይህም ተፈጥሯዊ ገፅታን የተላበሰ ሲሆን ከአገር አገር፣ ከጊዜ ጊዜ ለውጥ የማያመጣ ቋሚ ክስተት ነው። በአንፃሩ ደግሞ ሥርዓተ ፆታ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ

በሚኖሩ አባላት መካከል ለሴት ወይም ለወንድ ፆታዎች የሚሰጡ የሚና ክፍፍሎችን ያሳያሉ። እነዚህም ሚናዎች ማህበራዊ ድንጋጌዎች ሲሆኑ ከአስተዳደግ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው። የሥርዓተ ፆታ ሚናዎች በትምህርት የሚገኙ ከአገር አገርና ከጊዜ ጊዜ ሊለወጡ የሚችሉ ባህላዊ አመለካከቶችን ያጠቃልላል።

## 2.2. ሥርዓተ ፆታ ከተግባቦት ጋር ያለው ተዛምዶ

ተግባቦት የሰው ልጆች ቃላዊና ቃል አልባ በሆኑ መንገዶች ሃሳባቸውን እርስ በርስ የሚለዋወጡበት መስተጋብር ነው። በእርስ በርስ ተግባቦት ወቅት ሃሳብን ያለመረዳት (ያለመግባባት) ችግር ሊከሰት ይችላል። ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሰው የመስተጋብሩ ተሳታፊዎች የተለያየ የተግባቦት ስልት በመጠቀማቸው ሊሆን ይችላል። የልዩነት ምንጮችም ሁለት ሲሆኑ እነሱም ሥርዓተ ፆታና ባህል ናቸው። አንዱ ባህል ከሌላው ባህል የተለያዩ የተግባቦት ስልቶችን ሊጠቀም ይችላል። በዚህ ሳቢያ በመስተጋብሩ ተሳታፊዎች መካከል የሚፈጠረው የተግባቦት ክፍተት በባህል ፈርጅ ውስጥ የሚካተት ሲሆን በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው የተግባቦት አጠቃቀም ልዩነት ደግሞ ሥርዓተ ፆታን ይመለከታል (Olson 2000:268)።

### 2.2.1 ቃላዊ ተግባቦትና ሥርዓተ ፆታ

እንደ Greenberg (1996:95)፣ Lynch (1996:3) እና Sunderland (1994:137) ገለፃ ቃላዊ ተግባቦት የሚባለው እርስ በርስ ቃላዊ በሆነ መንገድ የሚካሄድ መስተጋብር ነው። በተግባቦት ሂደቱም ሰዎች የተነገረውን መልዕክት በማዳመጥ ምን መገንዘብ እንደቻሉ በቋንቋ አማካይነት የሚገለጽበት ስልት ነው። በመሆኑም በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ቋንቋን ለመማር፣ መምህራን ደግሞ ለማስተማር የሚጠቀሙበትን ስልትና ብልሃት ያካትታል። ስለዚህ የቋንቋ መምህራን ቃላዊ ተግባቦት ለክፍል ውስጥ መስተጋብር መሠረት መሆኑን በማጤን ሁሉም ተማሪዎች በተግባቦት ሂደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ መጣር ይጠበቅባቸዋል።

ከላይ የሰፈረውን ሐሳብ በሚያጠናክር መልኩ እነ Cole and Chan (1994:37) ሲያስገነዝቡ ቃላዊ ተግባቦት ቃላዊና ትዕምርታዊ በሆኑ መገለጫዎች ላይ መሠረት የሚያደረግ የተግባቦት ዓይነት ነው። ይህም በበርካታ ምድቦች የሚከፈል ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አረጋጋጭ፣ ጠቋሚ፣ አስፈላሚ፣ ገላጭ፣ ውጤታማና ውሳኔ ሰጭ የሚባሉት ይጠቀሳሉ። በክፍል ውስጥ መምህራን አብዛኛዎቹን የቃላዊ ተግባቦት ዓይነቶች ተግባራዊ ያደርጋቸዋል። እነዚህ ደግሞ የተማሪዎችን የዕድገት ለውጥ ለማወቅ ያስችላሉ። Callaham and Clark (1988) እና Flanders

(1971: 177-185) በበኩላቸው እንደገለጹት በክፍል ውስጥ በሚካሄድ ተግባቦት የመምህራን ቃላዊ የማስተማር ባህርያት በሁለት ይከፈላል። ይኸውም ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ የማስተማር ባህርይ በሚል ተለይቶ ይታወቃል። ቀጥተኛ ከሚባሉት ውስጥ ገለፃ፣ ማብራሪያ መስጠት፣ አቅጣጫ መጠቆም እና ትችት ወይም ተግሳጽ ይካተታሉ። በሌላ በኩል ቀጥተኛ ያልሆነ የማስተማር ባህርያት የሚሰኙው ደግሞ መምህራን ተማሪዎች በትምህርት ሂደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያበረክቱትን ድጋፍና ማበረታቻ ይመለከታል። ይህም ሐሳብን (ስሜትን) መረዳት፣ ግልጽ ማድረግ፣ መሸለም(ማበረታታት)፣ ሐሳባቸውን ማጎልበት የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። በመሆኑም በመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን የተማሪዎችን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ትምህርቱን በቀጥታ ከሚያስተምሩ ይልቅ በተዘዋዋሪ መንገድ ቢያስተምሩ የተማሪዎችን ስሜት በመረዳት ገንቢ አስተያየቶችን በመለገስ በጉዳዩ ላይ የበለጠ እንዲሳተፉ ይጋብዛል።

በሌላ በኩል ደግሞ Wood et al. (2005:418) እነ Dindia and Allen (1992) እና Lewin and Herlitz (2002) ን ዋቢ በማድረግ በጥናታቸው እንዳሰፈሩት ተግባቦታዊ ችሎታዎች ከሥርዓተ ፆታ አንፃር ሲታዩ ይችላሉ። በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚካሄድ መስተጋብር ወንድ ተማሪዎች ቃላዊ ተግባራትን በተፎካካሪነት መንፈስ ሲያከናውኑ ሴት ተማሪዎች ደግሞ እርስ በእርስ በመተጋገዝ መሥራትን ይመርጣሉ። በተመሳሳይ መልኩ Coultas(2003:62-63) እና Olson (2000:268) በበኩላቸው ሲገልጹ የሥርዓተ ፆታ ልዩነት በሴትና ወንድ የማዳመጥና የመናገር ተግባቦት ስልት ላይ ይንፀባረቃል። በማዳመጥ ሂደት ላይ ወንዶች መጠነኛ የሆነ የዓይን ግንኙነት፣ አልፎ አልፎ ራስ መወዝወዝ፣ ተከታታይነት የሌለው«አሀ... አሀ" ማለት፣ ሌሎች ተናጋሪዎች እንደጨረሱ በዚያው መቀጠል፣ በንግግር ላይ ጣልቃ መግባት፣ የተናጋሪውን መልዕክት ለመገንዘብ መጠየቅን ያዘወትራሉ። ሴቶች ደግሞ የማያቋርጥ የዓይን መስተጋብር፣ ያለማቋረጥ ራስን መወዝወዝ፣ በተከታታይ ፣«አሀ...አሀ» ማለት፣ ሌሎች ተናጋሪዎች ከተናገሩ በኋላ ማቆም፣ ለመናገር ሲፈልጉ ቆይታ ማድረግ ሲያዘወትሩ፣ ጥያቄ ደግሞ የሚጠይቁት በርካታ መረጃዎችን ለማግኘት ነው። በአንፃሩ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው የንግግር ስልት ደግሞ ወንዶች በንግግር ወቅት ጥቂት ቆይታ መፍጠር፣ ከርዕስ ጉዳይ በድንገት መውጣት፣ ሌሎች ተናጋሪዎች እስኪያስቆሟቸው ድረስ መናገር፣ ከቀዳሚ ተናጋሪዎች በበለጠ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው መናገር፣ በተከታታይ "እኔ" የሚለውን ተውላጠ ስም መጠቀም፣ አልፎ አልፎ ስለራሳቸው ምስጢር መናገር፣ ሆን ብለው ፈገግ ሊያሰኙ የሚችሉ ቀልዶችን መጨመር ያዘወትራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የሴቶች

(1971: 177-185) በበኩላቸው እንደገለጹት በክፍል ውስጥ በሚካሄድ ተግባቦት የመምህራን ቃላዊ የማስተማር ባህርያት በሁለት ይከፈላል፡፡ ይኸውም ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ የማስተማር ባህርይ በሚል ተለይቶ ይታወቃል፡፡ ቀጥተኛ ከሚባሉት ውስጥ ገለፃ፣ ማብራሪያ መስጠት፣ አቅጣጫ መጠቆም እና ትችት ወይም ተግሳጽ ይካተታሉ፡፡ በሌላ በኩል ቀጥተኛ ያልሆነ የማስተማር ባህርያት የሚሰኘው ደግሞ መምህራን ተማሪዎች በትምህርት ሂደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያበረክቱትን ድጋፍና ማበረታቻ ይመለከታል፡፡ ይህም ሐሳብን (ስሜትን) መረዳት፣ ግልጽ ማድረግ፣ መሸለም(ማበረታታት)፣ ሐሳባቸውን ማጎልበት የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ በመሆኑም በመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን የተማሪዎችን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ትምህርቱን በቀጥታ ከሚያስተምሩ ይልቅ በተዘዋዋሪ መንገድ ቢያስተምሩ የተማሪዎችን ስሜት በመረዳት ገንቢ አስተያየቶችን በመለገስ በጉዳዩ ላይ የበለጠ እንዲሳተፉ ይጋብዛል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ Wood et al. (2005:418) እነ Dindia and Allen (1992) እና Lewin and Herlitz (2002) ን ዋቢ በማድረግ በጥናታቸው እንዳሰፈሩት ተግባቦታዊ ችሎታዎች ከሥርዓተ ፆታ አንፃር ሊታዩ ይችላሉ:፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚካሄድ መስተጋብር ወንድ ተማሪዎች ቃላዊ ተግባራትን በተፎካካሪነት መንፈስ ሲያከናውኑ ሴት ተማሪዎች ደግሞ እርስ በእርስ በመተጋገዝ መሥራትን ይመርጣሉ:፡ በተመሳሳይ መልኩ Coultas(2003:62-63) እና Olson (2000:268) በበኩላቸው ሲገልጹ የሥርዓተ ፆታ ልዩነት በሴትና ወንድ የማዳመጥና የመናገር ተግባቦት ስልት ላይ ይንፀባረቃል፡፡ በማዳመጥ ሂደት ላይ ወንዶች መጠነኛ የሆነ የዓይን ግንኙነት፣ አልፎ አልፎ ራስ መወዝወዝ፣ ተከታታይነት የሌለው«አሀ… አሀ” ማለት፣ ሌሎች ተናጋሪዎች እንደጨረሱ በዚያው መቀጠል፣ በንግግር ላይ ጣልቃ መግባት፣ የተናጋሪውን መልዕክት ለመገንዘብ መጠየቅን ያዘወትራሉ፡፡ ሴቶች ደግሞ የማያቋርጥ የዓይን መስተጋብር፣ ያለማቋረጥ ራስን መወዝወዝ፣ በተከታታይ ፣«አሀ...አሀ» ማለት፣ ሌሎች ተናጋሪዎች ከተናገሩ በኋላ ማቆም፣ ለመናገር ሲፈልጉ ቆይታ ማድረግ ሲያዘወትሩ፣ ጥያቄ ደግሞ የሚጠይቁት በርካታ መረጃዎችን ለማግኘት ነው፡፡ በአንፃሩ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው የንግግር ስልት ደግሞ ወንዶች በንግግር ወቅት ጥቂት ቆይታ መፍጠር፣ ከርዕስ ጉዳይ በድንገት መውጣት፣ ሌሎች ተናጋሪዎች እስኪያስቆሟቸው ድረስ መናገር፣ ከቀዳሚ ተናጋሪዎች በበለጠ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው መናገር፣ በተከታታይ “እኔ” የሚለውን ተውላጣ ስም መጠቀም፣ አልፎ አልፎ ስለራሳቸው ምስጢር መናገር፣ ሆነ ብለው ፈገግ ሊያሰኙ የሚችሉ ቀልዶችን መጨመር ያዘወትራሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሴቶች

ንግግር ረዘም ያለ ቆይታ፣ ከቀዳሚ ተናጋሪዎች ጋር የሚዛመድ መረጃ መግለጽ፣ የሚናገሩትን ሲጨርሱ ማቆም፣ ከቀዳሚ ተናጋሪዎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ የድምፅ መጠን መጠቀም፣ በተከታታይ "እኛ" የሚለውን ተውላጠ ስም መጠቀም፣ ብዙ ጊዜ ስለራሳቸው ምስጢር መግለጽ፣ አልፎ አልፎ ከውይይቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቀልዶች መናገርን ያዘወትራሉ፡፡

## 2.2.2. ቃል አልባ ተግባቦትና ሥርዓተ ፆታ

Brown (1994:241) እና Cole and Chan (1994:37) እንዳሠፈሩት ቃል አልባ ተግባቦት በእንቅስቃሴ፣ በቦታ፣ በአካላዊ ውዝዋዜ፣ የፊት ገፅታና የሰውነት ቅርጽን በመጠቀም መልዕክት መለዋወጫ መንገድ ነው፡፡ እነዚህ አካላዊ መገለጫዎች የንግግር ሂደቱን የድምፅ ቃና፣ መጠን፣ ዜማ እና ሌሎችን ሊያነፀባርቁ ይችላሉ፡፡ ከቃል አልባ የተግባቦት ዓይነቶች ውስጥ አንዱ አካላዊ ቋንቋ ነው፡፡ በዚህ ምድብ ውስጥ ደግሞ የዓይን መስተጋብር ተጠቃሽ ሲሆን በግንኙነቱ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለንን ሥነ ልቦናዊና ማህበራዊ ሁኔታ በመግለጽ ተቀባይነት ማግኘትን ያንፀባርቃል፡፡ በርካታ መምህራን በቃላዊ ተግባቦት የገለጹትን መልዕክት ለማዳበር ቃል አልባ ተግባቦትን ይገለገላሉ፤ ሁለቱ በአንድ ላይ የተግባቦት ሂደቱ እንዲፋጠን ያደርጋሉ፡፡

ተግባቦት ከሚያበረክተው አስተዋፅኦ ውስጥ አንዱ ጫናን መቀነስ ነው፡፡ በመሆኑም መልዕክትን ከቃላት ውጭ በሆነ መንገድ የምንገልጽበት ባህርይ ቃል አልባ ተግባቦት ይባላል፡፡ በአብዛኛው ይህ የተግባቦት ዓይነት የሚከሰተው ሆነ ተብሎ አይደለም፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥም የመስተጋብሩን ደረጃ፣ ሌላው ሰው ምን እያሰበ እንደሆነ ለማወቅ እና የተነገረውን ነገር አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ያገለግላል፡፡ ይሁን እንጂ ቃል አልባ ምልክቶች ቃላዊ መልዕክቱን ሊያጠናክሩ ወይም ሊቀንሱ ስለሚችሉ ትኩረት ማድረግን የግድ ይላሉ፡፡ እነዚህም ምልክቶች ለመምህራን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ እንደ ዋና ምንጭ በመሆን ያገለግላሉ (Greenberg (1996:94) እና Galloway (1971:190))፡፡

እነ Olson (2000:268) እና Wood et al. (2005:419) በጥናታቸው እንደገለፁት ቃል አልባ ተግባቦቶች ከባህል ባህል በአጠቃቀምና በሚይዙት ትርጉም ይለያያሉ፡፡ ለአብነት ያህል በኢንግላንድ ቃል አልባ የሆኑ አካላዊ እንቅስቃሴዎች የማይፈልጉ እና ድፍረትን መግለጫዎች እንደሆኑ ይቆጠራል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ተግባቦቶች በኢጣሊያ፣ ፈረንሳይ፣

በደቡብ ምዕራብ ፓስፊክ እና በሌሎች አካባቢዎች የተለመዱ መግባቢያዎች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ሥርዓተ ፆታ ከቃላዊ ተግባቦት አንፃር ሲታይ ሴቶችና ወንዶች አካላዊ እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት ባላቸው ግንዛቤ ላይ ልዩነት ይንፀባረቃል። በመሆኑም ሴት ተማሪዎች ማንኛውም በአካላዊ እንቅስቃሴ የሚገለፁ ተግባራትን በቀላሉ ተገንዝበ ምላሽ በመስጠት ረገድ ከወንዶች የላቀ ሚና እንዳላቸው ማረጋገጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ ከላይ ከምሁራን ሐሳብ መገንዘብ እንደተቻለው ተግባቦት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች እርስ በርስ ዕውቀት፣ ሐሳብ፣ መረጃዎችንና ገጠመኞቻቸውን የሚለዋወጡበት ሂደት ነው። ይህ ሂደት ቃላዊ እና ቃል አልባ በሆኑ መንገዶች ይገለፃል። በቃላዊ ተግባቦት ቋንቋን መሠረት ባደረጉ መገለጫዎች መልዕክትን ማስተላለፍ ሲቻል በቃል አልባ ተግባቦት ደግሞ ከቃላዊ ቋንቋ ውጭ የሆኑ የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም መረጃዎችን መለዋወጥ ይቻላል። በመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን ሁለቱን የተግባቦት ዓይነቶች በሚጠቀሙበት ጊዜ የተግባቦት ሂደቱን ከማፋጠኑም በተጨማሪ በተማሪዎች ላይ ሊታይ የታቀደውን የባህርይና የአሠራር ለውጥ በሚፈለገው መጠን ለማምጣት ያስችላል። ለውጤታማነቱም የመምህራን ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ የማስተማር ባህርይ ሰፊ ድርሻ አለው። ከሁለቱ የማስተማር ባህርያት መካከል መምህራን ቀጥተኛ ያልሆነውን መንገድ በሚጠቀሙበት ጊዜ የተማሪዎችን ተሳትፎ ስለሚያበረታታ ጠቀሜታው የላቀ ነው።

## 2.3. በክፍል ውስጥ መስተጋብር የመምህራን የሥርዓተ-ፆታ አያያዝ

### 2.3.1. የክፍል ውስጥ መስተጋብር

Sunderland (1994፡137) እንደገለፀችው መማሪያ ክፍል ማንኛውም ዓይነት የመማር ማስተማር ተግባራት የሚካሄዱበት ቦታ ነው። በሂደቱም የተማሪዎች የመማር ብልሃትና ስልት የሚንፀባረቅበት ከመሆኑም በተጨማሪ የመምህር ተማሪ መስተጋብር፣ ቃላዊና ቃል አልባ ባህርያትና የመሳሰሉት የሚስተዋሉበት ሥፍራ ነው። እነ Sullivan and Kramsch (1996፡203)፣ Shuell (1993፡726) እና Byrne (1987:3) በበኩላቸው ሲያስገነዝቡ መማሪያ ክፍል እንደ አንድ ቤተሰብ ሊታይ ይችላል። በዚህ ቤተሰብ ውስጥ መምህራን ያላቸውን ዕውቀት ለተማሪዎቻቸው ያካፍላሉ። ይህ ዕውቀት ደግሞ አእምሯዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ስሜታዊ እና ትምህርታዊ ሁኔታዎችን ያጠቃልላል። እነዚህን ዕውቀቶች ለተማሪዎች ለማስጨበጥ መምህራን በርካታ ተግባራትን በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን ይተገብራሉ። ተግባራቱም

በተማሪዎች ተነሳሽነት፣ ስሜት፣ ማህበራዊ መስተጋብርና በአንድ ነገር በሚኖራቸው ግምት ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ተፅዕኖዎችን ሊያሳድሩ ይችላሉ።

ይህን ሐሳብ በማጠናከር እነ Richards and et al (1992፡185)፣ Malamah-Thomas (1991፡vii-7) እና Rivers (1989:52) ሲገልጹ የመምህር ተማሪ መስተጋብር የሚባለው ተራክቧዊ የሆኑ ትግበራዎችን እርስ በርስ ማካሄድ ነው። የመማር ማስተማር ሂደቱም ከመምህር ወደ ተማሪ፣ ከተማሪ ወደ መምህር ሊሆን ይችላል። ሆኖም የመስተጋብር ሂደቱን ውጤታማ ለማድረግ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የእኩልነት መንፈስ ሊኖር ይገባል። የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜታቸው እንዲጎለብት አስተዋጽኦ አለው። በሌላ መልኩ ደግሞ የትምህርት ልማት አካዳሚ (ዓ.ም. ያልተጠቀሰ፡25) Howe (1997)ን ዋቢ በማድረግ እንዳሠፈረው የክፍል ውስጥ መስተጋብር በመምህራንና በተማሪዎች እንዲሁም በተማሪዎቹ በራሳቸው መካከል የሚኖረውን ተግባቦት ያካትታል። ተግባቦቱ መምህራንንና የተወሰነ የተማሪዎችን ቡድን ወይም መምህራንንና ግለሰብ ተማሪን ይመለከት ይሆናል። ተግባቦቱ አወንታዊ (ለምሳሌ አድናቆት) ወይም አሉታዊ (ለምሳሌ ትችት ወይም ስድብ) ሊሆን ይችላል። የመስተጋብሩ ተመልክና ሁኔታም በትምህርት ውጤታቸውና በሙያ ምርጫቸው ላይ ተፅዕኖ በማድረግ ሴትና ወንድ ተማሪዎች ለተለያዩ ትምህርቶች በተለያየ መንገድ እንዲሠሩ ያደርጋቸዋል።

### 2.3.2. የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ

Lindsey (2005፡4)፣ Clark and Trafford (1996፡41)፣ Naiman and et al (1996፡180-2)፣ Cruickshank and et al (1995፡35) እና Bukatko and Daehler (1992፡494) ሲገልጹ መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሳያውቁ ፆታን መሠረት በማድረግ ሴትና ወንድ ተማሪዎችን የሚይዙበት መንገድ የተለያየ ነው። ከዚህ የተነሳ ተማሪዎችን የሚያበረታቱ እና የሚገስጿቸው በፆታቸው አማካይነት ባህሪያቸውን በመመርኮዝ ነው። ተግባራትን ደግሞ ሴቶች ተማሪዎች በጋራ ተባብረው እንዲሠሩ ሲያበረታቱ ወንድ ተማሪዎችን ግን ተፎካካሪ (እርስ በርስ ተወዳዳሪ) እንዲሆኑ ያበረታታሉ። ከዚህ አኳያ መምህራን ከወንድ ተማሪዎች ጋር በርካታ ጊዜ በማሳለፍ የበለጠ ትኩረት ይሰጣሉ። ለተስተዋለው የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ልዩነት ደግሞ የመምህራን ግላዊ ባህርያት (ስብዕና)፣ የማስተማር ልምድና ዐውድ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ።

Clegg (1998፡465) Patricia (1996)ን ዋቢ. በማድረግ እንዳሠፈረችው ሥርዓተ ፆታ እና ሥነ ትምህርት እርስ በርስ ይቆራኛሉ፤ ሥነ ትምህርት በመምህራን፣ በተማሪዎች እና በትምህርት ተግባራት ላይ ያለውን መስተጋብር ያሳያል። የእነዚህ መስተጋብር ውጤት የሚገኘው ደግሞ ተነሳሽነት፣ በራስ መተማመንና በጎ አመለካከት ሲኖር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የእነ Ryckman and Peckham (1987)ን ጥናት ምንጭ በማድረግ Valian (1998፡59) ስታስገነዝብ መምህራን ሴትና ወንድ ተማሪዎችን የሚይዙበት መንገድ ይለያያል። በዚህም ከአራተኛ እስከ አሥራ ሁለተኛ የክፍል ደረጃ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የተካሄደው ጥናት እንዳመለከተው በቋንቋ እና ሒሳብ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት ላይ የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ የተለያየ ሆኖ ተገኝቷል።

የሥርዓተ ፆታ ልዩነቶች በመምህር-ተማሪ፣ በተማሪ-ተማሪ መስተጋብር፣ በሥርዓተ ትምህርት ይዘትና በፈተናዎች ላይ ሊንፀባረቅ ይችላል። በክፍል ውስጥ መስተጋብር መምህራን ለተማሪዎቻቸው ቃላዊ እና ቃል አልባ ምጋቤ ምላሾችን ይሰነዝራሉ። እነዚህ ደግሞ አሉታዊ ገፅታን የተላበሱ ከሆኑ በተማሪዎች የወደፊት የትምህርት ዕድልና ለራሳቸው በሚኖር ግምት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው። በማስተማር ሂደት ላይ መምህራን ለሁሉም ፆታ ተማሪዎች አወንታዊ ምጋቤ ምላሾችን በመለገስ እኩል ትኩረት ሊሰጡ ይገባል። በዚህም ስማቸውን በመጥራት፣ እንዲሳተፉ በመጋበዝ፣ በንግግራቸው ጣልቃ ባለመግባት፣ ገንቢ አስተያየቶችን በመለገስ፣ ልማዳዊ የሆኑ አድሏዊ ባህርያትን የሚያንፀባርቁ ምሳሌዎችን አለመጥቀስ ተገቢ ነው (Makhubu 2000፡4 እና Elliott and et al 2000:139)።

እነ Sunderland (1992፡88፣1994፡148) እና Salisbury and Riddell (2000፡158-165) በበኩላቸው እንዳስገነዘቡት በእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሥርዓተ ፆታ ልዩነት በሦስት ዐውዶች ሊንፀባረቅ ይችላል። እነዚህም በመማር ሂደት (በመምህር-ተማሪ ና በተማሪ ተማሪ መስተጋብር)፣ በቋንቋ እና በማስተማሪያ መሣሪያዎች (መጽሐፍ፣ መዝገበ ቃላት፣ የመምህር መምሪያ) ናቸው። በኢንግላንድ በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን ለበርካታ ወንድ ተማሪዎች የበለጠ ትኩረት በመስጠት ወንድ ተኮር የሆነ መስተጋብርን ለማየት ተችሏል። ሁኔታውም ሆነ ተብሎ ወይም ሳይታሰብ የሚተገበር ሲሆን ልዩነቱ ሊከሰት የቻለው በሚያገኙት በርካታ ቃላዊ የተሳትፎ ዕድሎችና ምጋቤ ምላሾች አማካይነት ነው።



ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

በሌላ በኩል ደግሞ በኮሎምቢያ ከመጀመሪያ እስከ ከፍተኛ የክፍል ደረጃዎች በሚገኙ መቶ (100) መማሪያ ክፍሎች ውስጥ የተካሄደው ጥናት መምህራን ከሴት ተማሪዎች ይልቅ ለወንዶች ትኩረት መስጠታቸውን አመልክቷል፡፡ በትኩረቱም ወንድ ተማሪዎችን በርካታ ጥያቄዎች መጠየቅ እና ለምላሾቻቸው ደግሞ ማበረታቻዎችን እና አወንታዊ ምጋቤ ምላሾችን መሰንዘራቸውን አሳይቷል፡፡ በአንፃሩ ግን ሴት ተማሪዎች በአብዛኛው እንደተረሱ ወይም ለሠሩት ተግባር የሚሰጡት ምላሽ የማያበረታታ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ወንድ ተማሪዎች ከሴቶች የላቀ የመምህራንን ትኩረት ከሚያገኙበት ምክንያት ውስጥ አንዱ በጥያቄና መልስ ሂደት በበላይነት መሳተፍ መቻላቸው ነው፡፡ እንዲሁም ከመምህራን ፈቃድ ሳያገኙ በሚመልሱበት ጊዜ መምህራን አስተያየታቸውን በቸልተኝነት ይቀበላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሴት ተማሪዎች ያለፈቃድ መልስ ሲሰጡ ግን ህግ ጥሰው መመለሳቸውን በመንገር ይገስጿቸዋል፤ ይቆጧቸዋል፡፡ ሌላው የመምህራን ትኩረት ወደ ወንድ ተማሪዎች ሊያመዝን የቻለበት ምክንያት አጠቃላይ በማህበራዊ ህይወት በሥርዓተ ፆታ ሚናዎች ላይ ያለውን የተዛባ አመለካከት መምህራን በክፍል ውስጥ ማንፀባረቅ መቻላቸው ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች በቡድን በሚያሳትፉበት ጊዜ ወንዶችን የበላይ አድርጎ የማየት ሁኔታዎች ተስተውለዋል (Sadker and et al 1999፡136-137)፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ Borich and Tombari (1995፡613-4) የእነ Sadker and Sadker (1990፡115) ን ጥናት ዋቢ በማድረግ እንዳሠፈሩት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተካሄዱ ምልከታዎች እንዳመለከቱት በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሴት ተማሪዎች እንደማይታዩ አባላት ይቆጠራሉ፡፡ ለዚህም ከመምህር ጋር ያላቸው መስተጋብር አነስተኛ፣ የሚያገኙት ማበረታቻ መጠነኛ፣ የርስ በርስ መስተጋብር አናሳ እና ጥቂት ውስብስብና ረቂቅ ተግባራትን እንደሚተገብሩ ታይቷል፡፡ በተጨማሪም የሚመልሱት የጥያቄ መጠንና የሚቀበሉት አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ ከወንዶች ያነሰ ነው፡፡ እንዲሁም ለወንድ ተማሪዎች የሚሰጥ እርማት (ማስተካከያ) ስህተታቸውን በማየት ወደፊት በልምምድ ክህሎታቸውን እንዲያጎለብቱ የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ሴት ተማሪዎች ከመዋለ ህፃናት እስከ ኮሌጅ ደረጃ ትምህርት እስኪያጠናቅቁ ድረስ አንድ ሺህ ስምንት መቶ (1,800) ለሚሆን ጊዜ ብቻ የመምህራንን ትኩረት እንዳገኙ ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

Plessis and et al (2002፡86) እና Jabre (1988፡23) በበኩላቸው ሲያስገነዝቡ በአፍሪካ በሚገኙ ሀገራት የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ደካማ እንደሆነና በምክንያትነት ደግሞ ከቤተሰብ ጀምሮ

ማህበረሰቡ ለትምህርታቸው ያለው አሉታዊ አመለካከት ተጠቃሽ ነው። በዚህም የሴት ልጆች ትምህርት ከወንዶች አንሶ ይታያል፤ ትምህርትን በማቋረጥ የሴቶች ቁጥር ልቆ ይገኛል። በመማሪያ ክፍል መስተጋብር ላይ የተካሄደውም ጥናት የመምህራን መስተጋብር በብዛት ከወንድ ተማሪዎች ጋር እንደሆነ፣ ለጥያቄዎች መልስ መስጫ ረዘም ያለ ጊዜ እንደሚሰጡ እና በርካታ አወንታዊ ምጋቤ ምላሾችን ከሴቶች ይልቅ ለወንድ ተማሪዎች እንደሚለግሱ ማረጋገጥ ተችሏል።

ከላይ የተገለፁትን ጥናቶች በማጠናከር የትምህርት ልማት አካዳሚ (ዓ.ም.የልተጠቀሰ:25-26) እንዳሠፈረው የፆታ ልዩነቶች በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ይታያሉ። ለዚህ ጥሩ ምልክት የሚሆነን ወንድ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የበለጠውን የተሳትፎ ድርሻ መሸፈናቸው ነው። ወንድ ተማሪዎች አዘውትረው እጃቸውን ያወጣሉ። እንዳጋጣሚ መምህራን መጀመሪያ እጅ ላወጡ ተማሪዎች በሚፈቅዱበት ሁኔታ፣ የዚያ ዕድል ተጠቃሚ ወንድ ተማሪ የመሆኑ ነገር የሰፋ ነው። የወንድ ተማሪዎች የመማር ሂደት ብዙሐኑን በሚያሳትፍ መስተጋብር ውስጥ የተመቻቸ ሊሆን ሲችል የሴቶቹ ግን በግል ደረጃ ተገናኝቶ መነጋገርን ግድ ይላል። በክፍል ውስጥ አድናቆት ማግኘት፣ ምናልባት በሥራ ቦታም ተደማጭነትን ለማግኘት ሊያበቃ ይችላል።

Santrock (2001፡188) በበኩሉ ሲገልጽ በክፍል ውስጥ መስተጋብር የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ልዩነት ከሚንፀባረቅባቸው ነጥቦች ውስጥ መምህራን የበለጠ ትኩረት የሚሰጡትና ብዙ መመሪያዎችን የሚያቀርቡት ከሴቶች ይልቅ ለወንድ ተማሪዎች ነው፤ በዚህ ጊዜ ሴት ተማሪዎች ዝምታን ያበዛሉ። እንዲሁም ስድቦችን እና ተግሳጾችን በመሠንዘር ከክፍል የሚያስወጡት በአብዛኛው ወንድ ተማሪዎችን ነው። በተጨማሪም መስተጋብራቸው የሚያመዝነው ወደ ወንድ ተማሪዎች በመሆኑ ሴት ተማሪዎች በዚህ ወቅት በፀጥታ ሥራቸውን ይሠራሉ። ከዚህ አልፎ መምህራን በርካታ ጥያቄዎችን ወንድ ተማሪዎችን ስለሚጠይቁ ለአስቸጋሪ ጥያቄዎች የመምህራንን እገዛ ያገኛሉ። ለወንድ ተማሪዎች የጥያቄ መመለሻ የሚሰጣቸው ጊዜ ሰፊ በመሆኑ ለትክክለኛ መልሶች በርካታ ፍንጮችን ይሰጣሉ። ከዚህ ባሻገር የተሳሳተ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ እንደገና እንዲሞክሩ ሌላ ዕድል ይሰጣቸዋል።

እነ Sadker and et al (1999፡ 135) የ Carter (1987) ን ጥናት ዋቢ በማድረግ እንዳሠፈሩት በመምህር ተማሪ መስተጋብር ወቅት የፆታ አድሎዎች በተለያየ መንገድ ይንፀባረቃል። ለዚህ

ማስረጃ ይሆን ዘንድ በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ በሙዚቃ ክፍለ ጊዜ የታየው ምልከታ እንደሚከተለው ቀርቧል።

መሴ= የዕለቱን ትምህርት የሞዛርትን ቅኝት በመቅረፀ ድምፅ በማሰማት ጀመሩ።

መሴ= የዚህ ሙዚቃ አቀናባሪ ስም ማን ነው?

(ጥቂት እጆች ወጥተዋል፤ጆን "ብሩስ ስፒሪንግስተን" በማለት (ሳይፈቀድለት) ጮክ ብሎ ተናገረ፤ መምህርቷ የአንድ ወንድ ተማሪ ስም ጠሩ)

ተወ1(1)= ሀይደን (ብሎ መለሰ)

መሴ = እንዴት ይህን ልታስብ ቻልክ?

ተወ1(2)= ምክንያቱም ትናንት ይህን ያሰሙን ስለነበረ ነው።

መሴ = ኤሪክ ምን ታስበለህ? (ሌላ ወንድ ተማሪ ጠየቁ)

ተወ2 = አላውቀውም።

መሴ = ኤሪክ! ባለፉት ሁለት ሳምንታት የተለያዩ የጥንት ዘመን የሙዚቃ አቀናባሪዎችን አዳምጠናል። ከእነዚያ ውስጥ ይህን አሁን ያዳመጥነውን የደረሰው ማን ነው? (ዝምታ)

መሴ = ጆን! ኤሪክ የተጠየቀውን ጥያቄ ልታግዘው ትችላለህ?

ተወ3(1) = ቤትሆቨን

መሴ = አይደለም። ቤትሆቨን አይደለም። አስብ! ቤትሆቨን በቀደምት የሮማ ዘመን የነበረ ነው። (በመጨረሻ መምህርቷ እጁን ያወጣ ተማሪ በስም ጠሩ)

ተወ3(2) = እርግጠኛ አይደለሁም፤ ሞዛርት ይሆን?

መሴ = ኦ! ከመካከላችሁ መልሱ የሚያስማማው አለ?

ተወ1(3)= ሞዛርት ነው። ትናንት ካዳመጥነው የሞዛርት ቅኝት ጋር ይመሳሰላል። (ሳይፈቀድለት ጮክ ብሎ)

መሴ = በጣም ጥሩ። እሱ ከጻፋቸው ሥራዎች ውስጥ ሌሎችን የሚነግረኝ?

ተወ1(4)= አዎ! የቫዮሊን ዝግጅት ነው።

መሴ = በእርግጥ ትክክል ነው። በሁለት መሣሪያዎች መጫወት የሚያስችል ልዩ ዝግጅት አዘጋጅቷል። ሌላውን መሣሪያ ለመጠቆም ያህል የሚቀጥለውን ትንሽ አዳምጡ። (መምህርቷ ካስደመጡ በኋላ ከላይ የሞከረውን ተማሪ በስሙ ጠሩት)

ተወ1(5)= ሌላ ቫዮሊን።

መሴ = ፒተር? (ብለው ጠሩት)

ተወ4(1)= ቼሎ፡፡

መሴ = ልክ አይደለም፡፡ ሌላ መሣሪያ እንጂ ሌላ ቫዮሊን ወይም ቼሎ አይደለም፡፡

ተሴ1 = ቫዮላ? (ሳይፈቀድላት መለሰች)

መሴ = ሩት! እንድትጮሂ አልፈቀድኩልሽም፤ ታውቂያለሽ! ለሚቀጥለው ጊዜ እጅሽን አውጪ፡፡ ፒተር? (ደግመው ተጣሩ)

ተወ4(2)= ቫዮላ፡፡ (የሩትን መልስ ደግሞ ተናገረ)

መሴ = በጣም ጥሩ፡፡ ይህ ልዩ ዝግጅት ለቫዮሊን እና ቫዮላ ሞዛርት የጻፋቸው ናቸው፡፡ የሁለቱን ልዩነት ከመግለጼ በፊት በመጀመሪያ ቫዮሊኑን በመቀጠል ቫዮላውን ስለማስደምጣችሁ በመካከላቸው ያለውን አንድነትና ልዩነት ትለያላችሁ፡፡

በመማሪያ ክፍል ውስጥ በነበረው መስተጋብር መምህርቷ በተደጋጋሚ ስማቸውን በመጥራት ያሳተፉት ወንድ ተማሪዎችን ነው፡፡ ሁለቱም ፆታዎች እጃቸውን ሳያወጡ በሚመልሱበት ወቅት ወንዶችን ችላ በማለት ምላሾቻቸውን ሲቀበሉ፣ ለሴት ተማሪዎች ግን የማያበረታታ ምላሽ ሰንዝረዋል፡፡ በተጨማሪም ከፍተኛም ሆነ ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸውን ጥያቄዎች በተደጋጋሚ የተጠየቁ ወንድ ተማሪዎች ናቸው፡፡ እንዲሁም በርካታ ምጋቤ ምላሾችን፣ ገንቢ አስተያየቶችንና ማስተካከያዎችን በማበረታቻ መልክ አክለው ሰንዝረዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ጥናቶች በየትኛውም የትምህርት ዓይነትና የክፍል ደረጃ በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የመማር ማስተማር ሂደት ለወንድ ተማሪዎች ያደሉ በመሆናቸው ወንድ ተኮር ገፅታን እንዲላበሱ አስችሏቸዋል፡፡ ይህ ገፅታም በጥናቶች ላይ ተመሳሳይ ይዘት መኖሩን ያሳያል (Sadker et al. 1999፡135-137)፡፡

በአጠቃላይ ቀደም ሲል በነበሩት ማብራሪያዎች ላይ በክፍል ውስጥ መስተጋብር በመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ፆታን መሠረት ያደረጉ ሁኔታዎች መንፀባረቃቸውን ያመላክታሉ፡፡ ለዚህም በመምህር ተማሪ መስተጋብር ወቅት መምህራን የተለያዩ ተግባራትን ሲያሰሩ ከሴት ተማሪዎች ይበልጥ ለወንዶች ተሳትፎ የላቀ ድርሻ እንደሚሰጧቸውና በተሳትፎም የመምህራንን ፈቃደኝነት ሳያገኙ በሚመልሱበት ጊዜ ከመምህራን አወንታዊ አፀፋ መኖሩ ታይቷል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የሴቶች ተሳትፎ በጣም አናሳ እንዲያውም የለም የሚያሰኝ ሲሆን ያለፈቃድ በሚመልሱበት ወቅት የመምህራን አፀፋ ተግሳጽ መሆኑ ተንጸባርቋል፡፡ በመስተጋብር ወቅት መምህራን ለወንድ ተማሪዎች አወንታዊ ምላሾችን በብዛት ሲሰጡ ለሴቶች የሚሠነዝሩት ግን አሉታዊ ጎናቸው አመዝኗል፡፡ ስም እየጠሩ ከማሳተፍ አንፃር

የወንድ ተማሪዎች ስም በተደጋጋሚ እንደሚጠራና በተግባራት እንቅስቃሴ ወቅት ሰፊ ጊዜ ከሴቶች ይበልጥ ለወንዶች እንደሚሰጡ አሳይቷል። በተጨማሪም ለወንድ ተማሪዎች የሚሰጡ እርማቶች (ማስተካከያዎች) ለወደፊቱ በልምምድ ክህሎታቸውን የሚያጎለብቱ ሆነው ተገኝተዋል። ከእነዚህ መረጃዎች አንፃር በክፍል ውስጥ መስተጋብር የመምህራን የሥርዓተ-ፆታ አያያዝ ላይ ክፍተት መኖሩን ጠቁመዋል።

## 2.4. በመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ላይ የሚንፀባረቁ አድሏዊ ባህርያት

በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስተጋብር የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ልዩነት ከሚንፀባረቁባቸው ተላውጦዎች ውስጥ ምጋቤ ምላሽ፣ የጥያቄ አጠያየቅ፣ የቆይታ ጊዜ፣ የተሳትፎ እድል አሰጣጥ፣ አስተያየት፣ ማበረታቻ፣ ትችት፣ ሒስ ወይም ተግሳጽና ሌሎቹም እንደሚጠቀሱ ከላይ በንዑስ ክፍል 2.3.2. ሥር ለመዳሰስ ተሞክሯል። በመሆኑም ከእነዚህ ተላውጦዎች አንፃር ንድፈ ሐሳባዊ መሠረቶችን በመጨመር በሥርዓተ ፆታ አያያዝ ላይ ልማዳዊ አድሏዊ ባህርያት የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ በሚከተለው መልኩ ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል።

Blood and et al (1998፡181)፣ Matlin (1996፡30) እና Hayes (1993፡349) ሲገልጹ ልማዳዊ አድሏዊ ባህርያት ከግለሰቦች ስብዕና ጋር የሚያያዙ ሲሆን በተለያየ መንገድ ሊገለጹ ይችላሉ። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ለሴቶችና ለወንዶች የሚሰጥ የልምድ ስብስብን ይመለከታል። አድሏዊ ባህርያት ልምዶች እንጂ የገሃዱን ዓለም እውነታ በትክክል የሚያንፀባርቁ አይደሉም። ከአድሏዊ ባህርያት ውስጥ ከፍተኛውን ተፅዕኖ የሚያስከትለው ከሥርዓተ ፆታ አንፃር ያሉ ተያያዥ ነገሮች ናቸው። መገለጫቸውም ተፅዕኖ ማድረስና መለየት (መነጠል) ነው። ተፅዕኖ ማድረግ ለአንድ የተወሰነ የቡድን አባላት የሚኖር አሉታዊ አመለካከትን ይመለከታል። መለየት ሲባል ደግሞ አንድን ግለሰብ ወይም የቡድን አባላት ተቃራኒ በሆነ መንገድ በአድሏዊ ተግባራት የሚገለጹ ሁኔታዎችን ማንፀባረቅ ይመለከታል፤ እነዚህ ደግሞ በተለያዩ ክስተቶች ላይ ሊታዩ ይችላሉ።

### 2.4.1. የመምህራን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ

እነ Plessis and et al (2002፡64) እንዳስገነዘቡት ምጋቤ ምላሽ የሚባለው መምህራን የተማሪዎችን ችሎታ በሚመለከት የሚሰጡት መረጃ ነው። ምጋቤ ምላሾች አበረታች የሆኑ አስተያየቶችንና ድጋፎችን የያዙ ከሆነ የተማሪዎችን ችሎታ በማጎልበት የመማርና የማሰብ አድማሳቸውን ያሰፋሉ። መምህራን ለተማሪዎቻቸው ቃላዊ ወይም ጽሑፋዊ መንገድን በመጠቀም ሊገልጹት ይችላሉ። ከዚህ አንፃር ምጋቤ ምላሾች ተማሪዎች እንዴት

ችሎታቸውን ማሻሻል እንደሚገባቸው የሚያሳዩ ነጥቦችን ማካተት ይገባቸዋል፡፡ Dheram (1995:160) እና Perrott (1982:9) በበኩላቸው እንደገለፁት ምጋቤ ምላሽ በተግባቦት ሂደት ላይ የመጨረሻው ደረጃ ሲሆን በክፍል ውስጥ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ቃላዊ እና ቃል አልባ በሆኑ ተግባቦቶች የሚሰጡትን አፀፋዊ መረጃዎች ይመለከታል፡፡ እነዚህ ደግሞ ለመማር ማስተማር ሂደት እንደ ማዕከላዊ ነጥብ ይታያሉ፡፡ በመሆኑም ከመምህራን የሚሰነዘሩ ምጋቤ ምላሾች ዕውቀት ያዘሉ ሲሆኑ ይችላሉ፤ ከዚህ አንፃር ያለ ምጋቤ ምላሽ የአንድ ተማሪ ችሎታ ሊሻሻል አይችልም፡፡

ይህን ሐሳብ በማጠናከር Cole and Chan(1994:215) እንዳብራሩት ምጋቤ ምላሽ ተማሪዎች ለሠሯቸው ተግባራት ከመምህራን የሚሰጥ ተመጣጣኝ መረጃ ነው፡፡ እነዚህም ለትምህርት ውጤት ጥራት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ የምጋቤ ምላሽ ዓይነቶች በርካታ ሲሆኑ የተለመዱት አወንታዊና አሉታዊ ይባላሉ፡፡ አወንታዊ ምጋቤ ምላሾች ተማሪዎች በትምርታቸው ወይም በችሎታቸው ትክክለኛ የሆነ ገፅታ ሲያሳዩ የሚሰጥ መረጃ ነው፡፡ መምህራን አወንታዊ ምላሾችን በቃላዊ ምላሾች፣ የጥሩ ሥራ ማረጋገጫ በመስጠት ወይም በደብተራቸው ላይ አበረታች አስተያየቶችን በመጻፍ ሊገልጹ ይችላሉ፡፡ አወንታዊ ምጋቤ ምላሾች የመማር ሂደቱን ከማጎልበታቸው በተጨማሪ ተማሪዎች ለቀጣይ ሥራ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ ተማሪዎች ያላቸው ችሎታ ወይም ባህርይ ተገቢ ወይም ትክክለኛ አለመሆኑን ለመግለፅ የሚውል መረጃ ነው፡፡ እነዚህ ደግሞ አልፎ አልፎ የሚሠነዘሩ ከሆነ ጠቃሚ ጎን ይኖራቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ለተማሪዎች አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች በተደጋጋሚ የሚሰነዘሩ ከሆነ ለመማር ያላቸውን ተነሳሽነት በማዳከም ለውድቀትና ጭንቀት ይዳርጋቸዋል፡፡

Lynch (1996:117) ሲገልጽ ምጋቤ ምላሾች በግልጽ በሚታይ እና በማይታይ ሁኔታ ሊገለፁ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም አወንታዊ ምጋቤ ምላሾች ግልጽ ባልሆነ መንገድ ተሰንዝረዋል የሚባለው አድማጮች እንዲገነዘቡ የተወሰነ ፍንጭ ሲሰጥ ነው፡፡ ግልጽ የሆነ አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ የሚባለው ደግሞ አድናቆትን ወይም ተቀባይነት ማግኘትን ሲያንፀባርቅ ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ በግልጽ በማይታይ ሁኔታ ሲሰነዘር የቀረበውን ጥያቄ ለማገዝ አስፈላጊ ምልክቶችን (ፍንጮችን) መስጠትን ይመለከታል፡፡ በግልጽ የሚታየው አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ ደግሞ መተቸት (መገሰጽ) ወይም ማስተካከያ (እርማት) መስጠትን ያጠቃልላል፡፡

Rogers (1987) ን ዋቢ በማድረግ እነ Stein and et al (1994:44) ሲገልጹ መምህራን በክፍል ውስጥ ለሴትና ለወንድ ተማሪዎቻቸው የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ ከውስጣቸው ካለው ልማዳዊ አድሏዊ ባህርያት አንፃር የሚመራ ነው፡፡ በዚህም አማካይነት መምህራን ለሴትና ወንድ ተማሪዎቻቸው የሚለግሱት ማበረታቻ፣ ትችት፣ ተግሳጽና ሽልማት የተለያየ ይሆናል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ Good and Brophy (1990:34) ን ዋቢ በማድረግ እነ Cruickshank and et al (1995:34-35) ሲያብራሩ መምህራን ለተማሪዎቻቸው በሚሰነዝሩት ምጋቤ ምላሽ ላይ የሥርዓተ ፆታ ልዩነት ይታያል፡፡ በመሆኑም መምህራን ለሴት ተማሪዎች በርካታ የማያበረታታና ግልጽ ያልሆነ ትርጉም የለሽ ምጋቤ ምላሾችን ሲሰነዝሩ ለወንድ ተማሪዎች ደግሞ አበረታችና ውሱን ምጋቤ ምላሽችን ይለግሳሉ፡፡

Bukatko and Daehler (1992:524) እና Rhona and et al (1982:678) በበኩላቸው እንዳስገነዘቡት መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ ፆታቸውን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም የምጋቤ ምላሹ መለያየት (ለተወሰኑት ሙገሳ ለሌሎች ትችት መሆኑ) ተማሪዎች ስለራሳቸው ባላቸው ግምት እና አጠቃላይ በትምህርት ችሎታቸው ላይ ተፅዕኖ አለው፡፡ እነዚህም ትችቶች እና ግሳፄዎች ተማሪዎችን ወደ ውድቀት የሚወስዱ ድርጊቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መምህራን ለሴት ተማሪዎች የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ አቀማመጣቸውን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን ይበልጥ ትኩረት የሚሰጡት ፊት ላይ በፀጥታ ለተቀመጡ ሴት ተማሪዎች ሲሆን ወንድ ተማሪዎች ግን በየትኛውም ቦታ ቢቀመጡ ከፍተኛ የሆነ የመምህራንን ትኩረት ያገኛሉ፡፡

በክፍል ውስጥ የመምህራንን ምጋቤ ምላሽ ሁኔታ ጠቅለል በማድረግ እነ Cole and Chan (1994:223-225) ሲገልጹ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ላይ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ለዚህም መምህራን የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ ዓይነትና መጠን ከተማሪዎች ምላሽ ጋር ማመጣጠን መቻል አለባቸው፡፡ ዘግይቶ ከሚሰጥ ምጋቤ ምላሽ ይልቅ በአፋጣኝ የሚሰጥ ምጋቤ ምላሽ ጠቀሜታ አለው፡፡ ምላሹ ወዲያው በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪዎች ስህተታቸውን በማየት እንደገና እንዲሠሩ ዕድል ይሰጣል፡፡ ከዚህ አንፃር ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ የሚሠጠው በሠሩት ሥራ ላይ ተመስርቶ እንጂ ሌሎች ተጓዳኝ ነገሮችን ማካተት የለበትም፡፡ ለዚህም ምላሾቹ ውስን እና ግልጽ እንጂ ሰፊና የተድበሰበሱ መሆን የለባቸውም፡፡



ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

#### 2.4.1.1 አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ

Lindsey (2005:4) ስትገልጽ የሥርዓተ ፆታ ሚናዎች ለግለሰቦች በምንሰጠው ማበረታቻ እና ቅጣት ላይ ተፅዕኖ ያስከትላሉ። ይህ ሁኔታ ደግሞ ለግለሰቦች ከሚኖረን ግምት ጋር በእጅጉ ይያያዛል።የእነ Archer and Lioyed (1985) እና Rosser (1988)ን ጥናት ዋቢ. በማድረግ Hatchell (1998:378) እንዳሠፈረችው ልጆች ሴት ወይም ወንድ ሆነው በመወለዳቸው ሳቢያ በተለያየ አያያዝ ያድጋሉ፤ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን በህፃንነት ጊዜ የሚሰጣቸው የተለያዩ መጫዎቻዎች (አሻንጉሊቶች) ናቸው። የዚህ ዓይነቱ አስተዳደግ በጉርምስና ዕድሜያቸው በመማር ማስተማር ሂደትም ሆነ በትምህርት መስክ መረጣ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ ያስከትላል። የዚህ አይነትን ችግር ለመቅረፍ በክፍል ውስጥ መስተጋብር ተማሪዎች ለሚተገብሩት ሥራ መምህራን የተለያዩ ማበረታዎችን መለገስ ይጠበቅባቸዋል።

ማበረታቻ ወይም ሽልማት መምህራን ለተማሪዎች የሚሰጡት ምላሽ ወይም የተወሰኑ ባህርያትን ለማጠናከር የሚያሳዩት ተግባር ነው። ይህ ደግሞ ግለሰቦችን ለበለጠ ሥራ እንዲተጉና እንዲነቃቁ የማድረግ ሃይል አለው። እየተከናወነ ያለው ተግባር ደግሞ ምቹና ለወደፊቱ መልካም ነገርን የሚያመለክት እንዲሆን ያደርጋል። ከዚህ ባሻገር በሰው ልጆች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ እኩልነትን በማስፈን ረገድ ጉልህ ሚና ይጫወታል (Cole and Chan (1994:219) እናRosenthal (1971:33) )። እነ Plessis and et al (2002:38) በበኩላቸው ሲገልጹ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ማበረታቻ በሚሰጡበት ሰዓት ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት በመትጋት ዕውቀታቸውን በአዳዲስ ነገሮች ላይ እንዲያተኩሩ ይረዳል። ይህ ደግሞ ተማሪዎች ባላቸው ችሎታ ላይ በራስ የመተማመን ስሜትን በማጎልበት ለበለጠ ሥራ እንዲተጉ ያደርጋል። በተመሳሳይ መልኩ ትምህርት ሚኒስቴር (1990:34) እንዳሠፈረው መምህራን ተማሪዎችን የተወሰነ ጥያቄ ጠይቀው ትክክለኛ መልስ ከሰጡ፣ በዚሁ እንዲቀጥሉ ማበረታታት ይገባል። ትክክለኛ መልስ ያልመለሱ ተማሪዎች እንኳን ቢኖሩ መልሱን ለማግኘት እንዲሞክሩ መገፋፋት፣ መልሱን ካላገኙም ትክክለኛውን መልስ መንገርና የተማሪዎችን ሙከራ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ተማሪዎቹ ትክክለኛ መልስ ባለመናገራቸው መምህራን ተስፋ ማስቆረጥ የለባቸውም።

Elliott and et al (2000:140) ሲያስገነዝቡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚታየው የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ልዩነት በዋናነት የሚጠቀሰው ለሥርዓተ ፆታ የሚሰጥ ልማዳዊ አድሏዊ አመለካከት ነው።በዚህም ወንድ ተማሪዎች ከመምህራን ለችሎታቸው ማበረታቻ

ሲሰጡ ሴቶች ተማሪዎች ደግሞ ለሚያሳዩት ጥሩ ፀባይ ይበረታታሉ። መምህራን ይበልጥ የወንድ ተማሪዎችን ውጤት መቀነስ ከተነሳሽነት ጉድለት ነው በማለት ሲፈርጁ የሴት ተማሪዎች ውጤት ዝቅተኛ መሆን ደግሞ ከችሎታ ማነስ ነው በማለት በተደጋጋሚ ይገልጻሉ። Feldman (1996:358) እና Ayim and Houston (1996:52) በበኩላቸው እንደገለጹት በመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ልዩነት መኖሩን የሚያንፀባርቁ ማህበራዊ ሁኔታዎች ታይተዋል። በዚህም መምህራን ከሴት ተማሪዎች በአምስት (5)እጥፍ የሚበልጥ ትኩረት ለወንዶች ሰጥተዋል። በዚህም ወንድ ተማሪዎች በርካታ ሽልማትና፣ አበረታች እገዛ ከሴቶች በላቀ ሁኔታ ሊያገኙ ችለዋል። የወንዶች ሽልማት በሥራቸው ጥሩ ውጤት ሲያመጡ የተሰጠ ሲሆን የሴት ተማሪዎች ደግሞ በንፅህና አጠባበቃቸው ላይ የተመሠረተ ነው። ይህን ሐሳብ በማጠናከር እነ Olson (2000:274)፣ Fontana (1995:11)፣ Cruickshank et al. (1995:35)እና Delamont (1994:42) በበኩላቸው እንደገለፁት ሁለቱ ፆታዎች በሚገኙበት መማሪያ ክፍል ውስጥ በርካታ ቃላዊ የሆኑ ማበረታቻዎችና አስተያየቶች ለወንድ ተማሪዎች ይሰጣሉ። ወንድ ተማሪዎች ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ በቸልታ ይታለፋሉ፤ በተጨማሪም በሴቶች ንግግር ወቅት መምህራንም ሆኑ ወንድ ተማሪዎች ጣልቃ ይገባሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ Kramer (1991:155) የ Becker (1981)ን ጥናት በመጥቀስ እንዳሠፈረችው በአሥር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍል ውስጥ የተካሄደ ጥናት እንደሚያሳየው መምህራን የበለጠ መስተጋብር ያላቸው ከፊትም ሆነ ኋላ ከተቀመጡ ወንድ ተማሪዎች ጋር ነው። በዚህ ወቅት ወደ ሰባ በመቶ (70%) የሚሆኑ አበረታች አስተያየቶች ለወንድ ተማሪዎች ተሰንዝረዋል። ዘጠና በመቶ (90 %) የሚሆኑ የማያበረታቱ አስተያየቶች (ተግሳጾች) ደግሞ ለሴት ተማሪዎች ሊሰነዘሩ ችለዋል። Fontana (1995:151) Desforgers (1990)ን ዋቢ በማድረግ ሲገልጽ ጥቂት መምህራን ለተማሪዎች የሚሰጥ ማበረታቻ ጥሩ ውጤት ሊያስገኝ እንደሚችል አይገነዘቡም። ሆኖም ማበረታቻ ተማሪዎችን ለበለጠ ሥራ የሚያነሳሳ፣ ወደ ትምህርት እንዲያተኩሩ የሚያደርግ ከመሆኑም ባሻገር በመስተጋብር ወቅት ምቹና ውጤታማ የሆነ መማሪያ ክፍል እንዲኖር ያደርጋል።

Hatchell (1998:378) በበኩሏ ስታስገነዝብ በአውስትራሊያ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች በክፍል ውስጥ መስተጋብር መምህራን ሴትና ወንድ ተማሪዎችን እኩል በሆነ የሥርዓተ ፆታ አያያዝ መተግበራቸውን ከምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል። ምልከታው ሴት ተማሪዎች ለተጠየቁ ጥያቄዎች ብቻ ሳይሆን የተሳትፎ ዕድል የተሰጣቸው ወንድ ተማሪዎች ያልመለሷቸው

ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ተጋብዘዋል። በዚህ ወቅት መምህሩ ማበረታቻ በመስጠታቸው ሴት ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት ከፍተኛ ሊሆን ችሏል። በመጨረሻም ለሴት ተማሪዎች በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ለሠሯቸው ሥራዎች መምህሩ የሰጧቸው ማበረታቻዎች ብርታት እንደሆናቸው ገልፀዋል።

### 2.4.1.2 አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ

በተማሪዎች ትምህርት ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርሱ ነገሮች ውስጥ አንዱ መምህራን ትምህርት ነክ በሆኑ ጉዳዮችና ከትምህርት ውጭ ባሉ ባህርያት ላይ ተመርኩዘው የሚሰነዝሯቸው ትችቶች ይጠቀሳሉ። በመሆኑም መምህራን በሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ላይ በሚሰነዝሩት ትችት አማካይነት ምንም እንደማያውቁና ብቁ እንዳልሆኑ በመቁጠር ራሳቸውን መውቀስ ይጀምራሉ። ከዚህ አንፃር በመማሪያ ክፍል ውስጥ ወንድ ተማሪዎች ከሁለት ሦስተኛ (2/3)ኛ በላይ የሚሆኑ ትችቶችን ትምህርት ነክ ባልሆኑ ባህርያት ላይ ተሰጥተዋል። ለሴት ተማሪዎች የተሰነዘሩት ትችቶች ከሁለት ሦስተኛ (2/3)ኛ በላይ የሚሆኑት በትምህርት በሚያሳዩት ጥረት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። የመምህራን ትችቶች በትምህርት ላይ ያነጣጠሩ በመሆናቸው ሴት ተማሪዎች ለትምህርታቸው ዝቅተኛ ግምት ሊኖራቸው ችሏል (Bukatko and Daehler 1992:526)።

በተመሳሳይ ሁኔታ Arnold (1999:89) የ De porter (1995: 24-26)ን ጥናት ዋቢ በማድረግ ሲያስገነዝብ በአንድ የቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በተካሄደ መስተጋብር መምህራን ለተማሪዎቻቸው በአማካይ አራት መቶ ስልሳ (460)የሚሆኑ ወሳኝ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል። ከእነዚህ አስተያየቶች መካከል ሰባ አምስቱ(75)ቱ ብቻ አወንታዊ ናቸው። የዚህ ዓይነቱ አስተያየት ለተማሪዎች በተደጋጋሚ የሚሰነዘር በመሆኑ የተማሪዎች የመማር ሂደት እያሽቆለቆለ መጥቷል፤ ተማሪዎች በፈቃደኝነት አይማሩም፤ ቢማሩም በውስጣቸው ጥሩ ሁኔታ ላይሰማቸው ይችላል። እነ Papalia et al. (1999:357) ሲገልጹ ተማሪዎች የዝቅተኝነት ስሜት እንዳይሰማቸው መምህራን ከትችት ይልቅ ገንቢ የሆኑ አበረታች አስተያየቶችን መለገስ ይጠበቅባቸዋል።

የመምህራን ሚና በትምህርት ስልጠና ሂደት (1998:40) የተገኘ መረጃ እንደሚያስገነዝበው መምህራን በተማሪዎች ላይ አካላዊም ሆነ ሥነልቦናዊ ቅጣት ከቶውኑ መፈጸም አይገባቸውም። ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ እንዲደርሱ በማበረታታት፣ የተማሪዎችን ዝንባሌና ችሎታ፣ የሥነ ልቦናና የአካል እድገት፣ የስሜት ጥንካሬና እንዲሁም

ማህበራዊ ግንኙነታቸውን በመኮትኮት ስብዕናቸው እንዳይነካና ሃፍረት እንዳይሰማቸው ጥንቃቄ በማድረግ ብቁ ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ የመምህርነት የሙያ ሥነ ምግባር በእጅጉ ይፈልጋል። በመጨረሻም ትምህርት ሚኒስቴር (1990፡33) እንዳስፈረው ተማሪዎች በሚጠይቁበት፣ መልስ በሚመልሱበት ወይም በሚሳሳቱበት ጊዜ ተገቢውን እርምት በአግባቡ ማድረግ እንጂ ተማሪዎችን መገሰጽ፣ ማንቋሸሽ፣ መስደብ፣ መምታት፣ ማስፈራራት እንደገና ትምህርቱን እንዲጠሉት ማድረግ ስለሚሆን በመምህራን በኩል ትኩረት ሊሰጥበት ይገባል። ተማሪዎች ቢሳሳቱ እንደገና አሻሽለው እንዲመልሱ ማድረግ ያለዚያም በሌሎች ተማሪዎች እንዲመለስ ማድረግ ያም ካልሆነ መምህራን ራሳቸው ትክክለኛውን መልስ መንገር ይገባቸዋል። ተማሪዎች ያልገባቸው ነገር ካለም በትዕግስትና በጥሞና ደጋግሞ ማስረዳት፣ መሞከር፣ በተጨማሪ ተማሪዎች ቤታቸው ሄደው ወይም ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን እንዲሠሩትና አብረው እንዲወያዩበት መንገር አስፈላጊ ነው።

### 2.4.2. የመምህራን ጥያቄ አጠያየቅ

እነ Nunan and Lamb (1996:80-88) ሲገልጹ በክፍል ውስጥ መምህራን ጥያቄዎችን ለተማሪዎች ያቀርባሉ፣ ለቀረቡ ጥያቄዎች ደግሞ ተማሪዎች መልስ ሲሰጡ መምህራን ይገመግማሉ። ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በርካታ ተግባራትን ያከናውናሉ። ከእነዚህም ውስጥ የተለያዩ ጽንሰ ሐሳቦች እንዲንሸራሸሩ፣ ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለመገምገም እና አጠቃላይ መስተጋብሩን ለመቆጣጠር ይውላሉ። የትምህርት ሂደቱን ለመቆጣጠር የሚቻለው ለጥያቄዎቹ ሥርጭት ትኩረት ሲሰጥ ነው። ለዚህም ጥያቄዎች መዳረስ ያለባቸው ለሁሉም ተማሪዎች እንጂ ለተወሰኑ ጥቂት ተማሪዎች ብቻ መሆን የለበትም። ጥያቄዎቹም መመረጥ ያለባቸው እንደ ትምህርቱ ዓላማ፣ እንደ ተግባራቱና እንደ ተማሪዎች ብዛት ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ነው።

የክፍል ውስጥ ጥያቄዎች በአብዛኛው ቃላዊ መሣሪያዎች ሲሆኑ ሌሎች አድማጮች ምላሽ እንዲሰጡ የሚያነቃቁ ናቸው። መምህራን ለሚያነሷቸው ነጥቦች ተማሪዎችን በማነሳሳት አስበው ምላሽ እንዲሰጡ ይጠቀሙባቸዋል። በዚህም መጠየቅ መስተጋብራዊ ሂደት ሲሆን ዓላማውም ተማሪዎችን በትምህርት ሂደቱ በማሳተፍ ውጤታማ የሆኑ ምላሾችን ማስገኘት መቻል ነው። ጥያቄዎች በተለያየ ምድብ ሊከፈሉ ይችላሉ። ከፍተኛና ዝቅተኛ፣ ክፍትና ዝግ፣ የማስታወስና የፍለጋ፣ የሂደት (ውጤት)ና የመለካካት፣ በመጠየቂያ ቃላት የሚቀርቡ፣ በግልጽና በሥውር የሚቀርቡ እና ዳራዊ ዕውቀትን የሚፈትሹ ጥያቄዎች ወዘተ ይባላሉ።

ጥያቄዎች በየትኛውም መልክ ይቅረቡ ዋናው የሚከተሉትን ዓላማዎች ማስገኘት መቻላቸው ነው፡፡ መስተጋብሩን ማፋጠን፣ ተማሪዎች ለትምህርት ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ፣ ዕውቀትና ግንዛቤን መፈተሽ፣ መሠረታዊ ይዘቶችን መከለስ፣ አዕምሯዊ ተግባራትን ማነቃቃት፣ የቡድን ውይይቶችን ማጎልበት እና ማህበራዊ ባህርያትን ማዳበር ነው (Cole and Chan 1994:170-173)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ Perrott (1982:41) እና Kenneth and William (1982:414) በበኩላቸው ሲያስገነዝቡ በክፍል ውስጥ የጥያቄና መልስ ሂደት ሰፊውን ድርሻ ይይዛል፡፡ በዚህም መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች የተማሪዎችን የማሰብ ችሎታ ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በመሆኑም ጥያቄዎች በተለያዩ ንዑሳን ምድቦች ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ በማስታወስ ችሎታና በአጠቃላይ ዕውቀት የሚመለሱ እውነታን የያዙ ጥያቄዎች ዝቅተኛ ደረጃ ጥያቄዎች ይባላሉ፤ በማነፃፀር (በማወዳደር)፣ ማብራራት፣ መግለጽ፣ ማጠቃለል፣ ማሳጠርና መገምገምን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን ደግሞ ከፍተኛ ደረጃ ጥያቄዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነ Brophy (1983:64) እና Bennett (1982:88) እንዳሠፈሩት መምህራን የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃታቸው ውጤታማ ይሆን ዘንድ የተማሪዎችን ሐሳብ በጥሞና ማዳመጥ፣ ለተማሪዎች መልስ ከመስጠታቸው በፊት ደግመው መጠየቅ ወይም ፍንጭ መስጠት አለባቸው፡፡ ለውጤታማነቱም ትችቶችን (ተግሳፆችን) ማስወገድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የመምህራን የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት አወንታዊና አሉታዊ ገፅታ ሊኖረው ይችላል፡፡ አወንታዊ የሆነው አጠያየቅ መምህራን ተማሪዎችን በስም ከመጥራታቸው በፊት ጥያቄውን ሲጠይቁ ሲሆን አሉታዊ የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት የሚባለው ደግሞ መምህራን የሚጠይቁትን ተማሪ በስም ከጠሩ በኋላ ሲያቀረቡ ነው፡፡

ተማሪዎች ባላቸው አካዳሚያዊ ነፃነት ማንኛውንም ጥያቄ የመጠየቅና መልስ የማግኘት፣ ሀሳባቸውን የመግለጽና አስተያየት የማቅረብ፣ እንዲሁም በመረጡት የግል አቀጣጫና አመለካከት የመራመድና ውሳኔ የመስጠት መብታቸውን መምህራን ሊያከብሩላቸው ይገባል (የመምህራን ሚና በትምህርት ስልጠና ሂደት 1998:40)፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ትምህርት ሚኒስቴር (1990:32) እንዳሰፈረው በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን የማይመልሱ ወይም የሚመልሱ ወንዶችም ሴቶችም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ታዲያ ጥያቄውን ባይመልሱ በመምህር በኩል ምን ምላሽ ይሰጣል?፣ ሌሎች የክፍል ተማሪዎችስ ምን አስተያየት ይሰጣሉ?፣ ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ሲሰጡስ ምን ይባላሉ?፣ መምህራን የበለጠ

ያበረታቷቸዋል?፣ በተለይ መልስ ለመመለስ የሚሞክሩ ሴት ተማሪዎችን ማበረታታት አስፈላጊ ይሆናል። ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ እንዲያፈልቁ፣ ከልምዳቸው እንዲናገሩ እርስ በርሳቸው እንዲወያዩ ማድረግ የበለጠ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ሌሎቹ ዝም ያሉ ከኋላ የተቀመጡትንም ማበረታታትና ጥያቄዎችን እንዲሞክሩ ማድረግ፣ መምህራን በአጠገባቸው እየሄዱ ወይ በስም እየጠሩ እንዲመልሱ መገፋፋት ይኖርባቸዋል። Makhubu (2000:6) እና Cruickshank and et al (1995:35) ሲገልጹ መምህራን ከእያንዳንዱ ፆታ ማህበራዊ ባህርይ በመነጨ ሁኔታ በክፍል ውስጥ በርካታ ጥያቄዎችን ለወንድ ተማሪዎች ያቀርባሉ። በዚህም ወንድ ተማሪዎች ያለ ፈቃድ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ በቸልታ ያልፋሉ፤ ነገር ግን ሴት ተማሪዎች ሳይፈቀድላቸው መልስ ሲመልሱ በመምህራን ይቀጣሉ፤ ይገሰጻሉ።

እነ Elliott and et al (2000:146) ደግሞ Bailey (1993) ን ዋቢ በማድረግ እንዳሠፈሩት በክፍል ውስጥ መስተጋብር ወንድ ተማሪዎች በተደጋጋሚ ከሴቶች የበለጠ የመምህራንን ትኩረት ስለሚያገኙ በበርካታ ጥያቄዎች ይሳተፋሉ። በዚህም ለወንድ ተማሪዎች የተሰነዘሩ ጥያቄዎች በሰማኒያ ከመቶ (80%) ከሴቶች ልቀው ተገኝተዋል። Sunderland (1992:88-89) ስታስገነዝብ በአውስትራሊያ እና ኒውዘርላንድ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን በርካታ ጥያቄዎችን ወንድ ተማሪዎች እንዲመልሱ ዕድል ሰጥተዋል። ወንዶችም በተፈጠረላቸው አጋጣሚ በመጠቀም በርካታ የንግግር ተሳትፎ አካሂደዋል። በእነዚህ ሁኔታዎች የወንዶች የመናገርና የተነሳሽነት ሚና ከፍ ለማለት ችሏል። ለእነዚህ በምክንያትነት መምህራን ሴትና ወንድ ተማሪዎችን በተለያየ መንገድ መያዛቸውን ከሚያመላክቱት ውስጥ ጥያቄዎችን ማንን ልጠይቅ? ማን ይመልስ? ብሎ መምረጥ፣ የጥያቄዎችን ደረጃ (ክብደት) በማየት መጠየቅ፣ ተደራራቢ (ተጓዳኝ) ተግባራትን ማሠራት የሚሉት ይጠቀሳሉ። እነዚህ ነገሮች በመምህራን ሆነ ተብለው ወይም ሳያውቁ የሚተገበሩ ናቸው።

ከዚህ በተለየ መልኩ Alexander (1997:77) እና Greenberg (1996:235) በበኩላቸው ሲያብራሩ የመምህራን ፆታን መሠረት ያደረገ ልማዳዊ አድሏዊ ባህርያት በተለያዩ መንገዶች ሊገለጹ ይችላሉ። ከእነዚህም ውስጥ መምህራን ለሴትና ወንድ ተማሪዎች የሚጠይቁት የጥያቄ ዓይነት ተጠቃሽ ነው። በመሆኑም መምህራን ሴት ተማሪዎችን በርካታ ቀላል ጥያቄዎች ይጠይቃሉ። ወንድ ተማሪዎች ደግሞ የተለያዩ ዓይነት ጥያቄዎችን እንዲሠሩ ስለሚጠየቁ ደረጃ በደረጃ የቀረቡ መመሪያዎችን በማየት ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደሚችሉ

መምህራንን ይጠይቃሉ። በዚህ መሠረት የመምህራን ትኩረት በአብዛኛው ወደ ወንድ ተማሪዎች በመሆኑ ከሴት ተማሪዎች በስምንት (8) እጥፍ የሚበልጡ ጥያቄዎችን እንዲሠሩ ዕድል ሰጥተዋል። ይህ ሁኔታ ለወንዶች በራስ የመተማመን ብቃታቸውን ሲያጎለብት ሴቶች ግን ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጓል። ይህን የጥናት ውጤት በማጠናከር Subbo (2002:10-11) የMolokemme (1999) ን ጥናት ጠቅሶ እንዳሠፈረው በአፍሪካ አገሮች በሚገኙ ሴቶች ላይ እንደ መመዘኛ የሚታዩት ባህላዊ የሆኑ አመለካከቶች ያመዝናሉ። በዚህም ሴቶችና ወንዶችን በየትኛውም ማህበራዊ መስተጋብር ላይ መለካት የሚገባው በሚያሳዩት ተሳትፎ እና ባላቸው ችሎታ እንጂ በሌሎች ስሜታዊ በሆኑ መመዘኛዎች መሆን የለበትም።

### 2.4.3. የመምህራን የቆይታ ጊዜ አሠጣጥ

Nunan (1991)'ን ዋቢ በማድረግ Thornbury (1996:282) እንዳሠፈረው የቆይታ ጊዜ ማለት ተማሪዎች መልስ እንዲመልሱ መምህራን የሚሰጡት የጊዜ መጠን ነው። ይህ ጊዜ ተማሪዎች መልስ ከመስጠታቸው በፊት፣ ጥያቄውን እንደገና ከመመለሳቸው በፊት ወይም ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ ከመስጠታቸው በፊት ያለውን ቆይታ ያመላክታል። Rowe(1986:43) ስትገልጽ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ጥያቄ ጠይቀው መልስ ለመቀበያ ከአንድ እስከ ሶስት ሰከንድ የሚያንስ ጊዜ ይሰጣሉ። በተጨማሪም ተማሪዎች ንግግራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ለመምህራን ጥያቄ አፀፋ ወይም ምላሽ መስጫ ወይም ሌላ ጥያቄ ለመጠየቅ ተመሳሳይ የሆነ ጊዜን ይጠቀማሉ። የመጀመሪያው ቆይታ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ መስጫ ጊዜ ሲሆን ሁለተኛው ቆይታ ደግሞ ተማሪዎች ምላሽ ከሰጡ በኋላ ያለ ጊዜን ይመለከታል። እነ Cole and Chan (1994:170) በበኩላቸው ሲያስገነዝቡ የቆይታ ጊዜ በቀረበው ጥያቄና በተማሪዎች ምላሽ መካከል የሚኖር የጊዜ መጠን ነው። ተማሪዎች ምላሽ ለመስጠት የሚዘገዩ ወይም ቀስ የሚሉ ከሆነ መምህራን ዘወትር የጥያቄውን መልስ ሊያስገኙ የሚችሉ ሌሎች ማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለባቸው። እነዚህ ጥያቄዎች የተማሪዎች ምላሽ ግልጽ እንዲሆን የሚያግዙ በመሆናቸው ተማሪዎች በቅድሚያ የተጠየቁትን ጥያቄ በስፋትና በጥልቀት እንዲያስቡ እድል ይሰጣል።

እነ Shrum and Tech (1985) ን ዋቢ በማድረግ Nunan and Lamb (1996:84-87) እንዳመለከቱት በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚኖር መስተጋብር የቆይታ ጊዜ ቁልፍ ጉዳይ ነው። በመሆኑም መምህራን ለተማሪዎቻቸው በጣም ጥቂት የሆነ የቆይታ ጊዜ የሚሰጡ ከሆነ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ተማሪዎች ስለጥያቄው እንዲያስቡ ያደርጋል። ሆኖም ተመጣጣኝ የሆነ የቆይታ ጊዜ ጠቀሜታው የላቀ ነው። በርካታ መምህራን ለመልስ መስጫ የሚመድቡት ሰዓት ከአንድ ወይም ከሁለት ሰከንድ አይበልጥም። ለጥያቄዎች መልስ ከተሰጠ በኋላ ከሦስት እስከ አምስት ሰከንድ ጊዜ ይመድባሉ። ይህ ደግሞ በርካታ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ዕድል ይሰጣል። በመሆኑም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በፈረንሳይኛና ጀርመንኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን አማካይ የሆነ ርዝመት ያለው የቆይታ ጊዜ በመጠቀማቸው ውጤታማ ሆነዋል። ለዚህም አስተዋጽኦ ያደረገው ከጥያቄዎቹ ቀጥሎ ያለው የቆይታ ጊዜ ከሁለት ሰከንድ ያነሰ መሆኑ ነው። ከዚህ አንፃር በምልከታው የሚከተሉትን ውጤቶች ማግኘት ተችሏል። በራሳቸው ተነሳሽነት የማይሳተፉ ተማሪዎች እንዲሳተፉ፣ አላስፈላጊ ምላሾች እንዲቀንሱ፣ አስፈላጊ የሆኑ ምላሾች እንዲበራከቱ፤ ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች እንዲጨምሩ፣ በአማካይ የተማሪዎች ምላሽ ርዝመት እንዲጨምር፤ ገላጭነት ያላቸው ዐረፍተ ነገሮች እንዲበራከቱ፣ የተማሪ-ተማሪ መስተጋብር እንዲጎለብት በአጠቃላይ ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ ቃላዊ ተሳትፏቸው እንዲልቅ አድርጓል።

በስፔን በሚገኙ ከአንደኛ እስከ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ደረጃ መማሪያ ክፍል ውስጥ የተከናወኑ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የቆይታ ጊዜ ጽንሰ ሐሳብ በርካታ የሆኑ ዕይታዎችን አመላክቷል። መምህራን ተማሪዎቻቸውን ጥያቄ በሚጠይቁበት ሰዓት ያለው የቆይታ ጊዜ ለተማሪዎችም ሆነ ለመምህራን በአጠቃለይ ለመማር ማስተማር ሂደቱ ጠቀሜታ አስገኝቷል። ይህ ደግሞ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ከሚኖራቸው ግምት ጋር በእጅጉ ይያያዛል። በመሆኑም በመምህርና በተማሪ የአጠያየቅ ሂደት ላይ ያለው የቆይታ ጊዜ የመምህራን አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች የተመጠኑ እንዲሆኑና ተማሪዎች ተነሳሽነት እንዲኖራቸው አድርጓል። በተለይ ይበልጥ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች በተማሪዎች በራስ የመተማመን እና ሌሎች ተፅዕኖዎችን በመቀነስ ረገድ ሚናቸው ከፍተኛ ነው። ይሁን እንጂ በስፔን የተካሄዱ የጥናት ውጤቶች መምህራን ተማሪዎቻቸውን ጥያቄ ሲጠይቁ አንዱን ፆታ ከሌላው ፆታ የበለጠ የቆይታ ጊዜ እንደሰጡ Rowe (1986:44-48) በጥናቷ አረጋግጣለች።

### 2.4.4. የመምህራን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ

Allwright (1988:126) እንደገለፀው በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚካሄድ ተሳትፎ ማህበራዊ ሁኔታን የሚያሳይ ሲሆን በዚህም ተማሪዎች በተሳታፊነት ይንቀሳቀሳሉ። ተሳትፎውም

በአብዛኛው በቃላዊ መስተጋብር ላይ ያተኮረ ነው። Ashcroft and Foreman-Peck (1994:145) በበኩላቸው ሲያስገነዝቡ ለተሳትፎ ዕድል መስጠት በትምህርት መስክ ሁለንተናዊ የሆነ ፋይዳ ያስገኛል። ከዚህ አንፃር እኩል ዕድል አለመስጠት ፆታን መሠረት ባደረገው ለሥርዓተ ፆታ ሚና ከሚኖረን አመለካከት ጋር ይያያዛል። በክፍል ውስጥ መስተጋብር መምህራን ለሴትና ለወንድ ተማሪዎች እኩል የተሳትፎ ዕድል ቢሰጡ በትምህርት መስክ የሚንፀባረቀውን ያልተመጣጠነ የሥርዓተ ፆታ አያያዝ በማጥበብ ብሎም በማስወገድ ረገድ ሰፊ ድርሻ ይኖረዋል።

ትምህርት ሚኒስቴር (1990:31-35) እንዳሠፈረው በክፍል ውስጥ በሚካሄድ የመማር ማስተማር ሂደት ብዙ ነገሮችን ማገናዘብ ይቻላል። መምህራን ሲያስተምሩ ወይም ጥያቄ ሲጠይቁ መልስ ለመስጠት የሚዘጋጁት የትኞቹ ተማሪዎች ናቸው? ሴቶች ተማሪዎች ብቻ ናቸው ወይም ወንዶች ተማሪዎች? እዚህም ላይ መታየት ያለበት እጃቸውን የሚያወጡ ተማሪዎች ብቻ ናቸው ትክክለኛውን መልስ የሚመልሱት ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ ለመመለስ ፈቃደኛ መሆን፣እኔ እሞክረዋለሁ ማለት፣ ብሳሳትም እታረማለሁ ብሎ እንጅ አውጥቶ ጥያቄ መመለስ ፍርሃትን ለማስወገድ አንዱ የጥሩ ተሳትፎ ምልክት ነው። ሆኖም አንዳንድ ተማሪዎች መምህራን ካልጠየቋቸው በስተቀር አስተያየት የማይሰጡ ወይም ሀሳብ ለመስጠት የማይፈልጉ፣ የሚፈሩ ተማሪዎች አሉ። ይህ በብዙ ሴት ተማሪዎች ላይ የሚታይ ነው። ስለዚህ መምህራን በስም እየጠሩ ተማሪዎች እንዲሳተፉ፣ ጥያቄ እንዲመልሱ ወይም እንዲጠይቁ ማደፋፈር ይጠበቅባቸዋል። በክፍል ውስጥ የሚሠሩ ልምምዶች፣ የማስመሰል ጨዋታዎች ወይም ድራማዎች፣ ተረት መናገርና ግጥም ማንበብ በመሳሰሉት ድርጊቶች ላይ ተማሪዎችን እንዲሳተፉ ማደረግ ይኖርባቸዋል።

Sunderland (1992: 89) በበኩሏ ስትገልጽ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በጥንድ ወይም በቡድን ሥራ ሊሳተፉ ይችላሉ። እነዚህ ተግባራት ደግሞ ተግባቦትን በማጎልበት ረገድ ጠቀሜታ አላቸው። ሆኖም በቡድንም ሆነ በጥንድ ተግባራት ላይ ወንድ ተማሪዎች በብዛት የተሳትፎ ዕድል ስለሚያገኙ የሴት ተማሪዎችን የመናገር ድርሻ ይሻማሉ። ይህን ጉዳይ እነ Sadker and et al (1999:140) ሲያብራሩ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከመምህራን ጥቂት ትምህርታዊ ቀረቤታ፣ አነስተኛ ማበረታቻና ምጋቤ ምላሽ፣ ጥቂት ውስብስብና ረቂቅ ጥያቄዎች እንዲሁም አነስተኛ መመሪያዎች ይቸራቸዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ Eckert and Mc Connell-Ginet (2003:116) እንዲሁም Cruickshank and et al (1995:34) እንደገለጹት በመማሪያ ክፍል ውስጥ



ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

በሴትና ወንድ ተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ልዩነት ይታያል፡፡ ይኸውም ወንድ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ዘወትር የተሳትፎ ዕድል ስለሚያገኙ የመናገር ዕድል አላቸው፡፡ በአንፃሩ ግን ሴት ተማሪዎች የንግግር ተሳትፏቸው አነስተኛ በመሆኑ፣ በመስተጋብር ሂደቱ የወንድ ተማሪዎች ንግግር ከሴቶች በ 2 ½ እጥፍ ልቆ ታይቷል፡፡

Elliott and et al (2000:140) እና Clark and Trafford (1996:46) እንዳስገነዘቡት መምህራን በክፍል ውስጥ "ማንኛውም ተማሪ ለመናገር ሲፈልግ እጅ ማውጣት አለበት" የሚል ህግ ይደነግጋሉ፡፡ ይሁን እንጂ በምልከታ የታየው ሁኔታ ተቃራኒ ገፅታ ይዟል፡፡ ይኸውም በክፍል ውስጥ ተግባራት ወንድ ተማሪዎች በውይይቶች ላይ ይበልጥ በመሳተፍ የበላይነትን ሊይዙ ችለዋል፡፡ ሁኔታው ከመምህራን ፈቃድ ሳያገኙ (እጅ ሳያወጡ) ያለውን ተሳትፎ ሲያካትት በጥቅሉ ከሴቶች ተሳትፎ የወንዶች በስምንት (8) እጥፍ ሊበልጥ ችሏል፡፡ Valian (1998:65) በበኩሏ ስታስገነዝብ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሁሉም ወንድ ተማሪዎች ባይሆኑም ከሴቶች በላቀ ሁኔታ ይሳተፋሉ፡፡ በተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ ላይ ሴት ተማሪዎች ሳይፈቀድላቸው በሚመልሱበት ወቅት በመምህራን እገዳ ይደርስባቸዋል፡፡ ነገር ግን ወንድ ተማሪዎች ያለ ፈቃድ በሚሳተፉበት ጊዜ መምህራን በቸልተኝነት ምላሻቸውን ይቀበላሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለሥርዓተ ፆታ ከሚኖረን አመለካከት የሚመነጭ ነው፡፡

ከላይ በተለዩ ንዑሳን ርዕሶች የሰፈሩ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ላይ የሚንፀባረቁ ልማዳዊ አድሏዊ ባህሪያትን ነው፡፡ እነዚህ አድሏዊ ባህርያት በተለያየ መልክ የሚንፀባረቁ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ መምህራን ለተማሪዎቻቸው በሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ፣ በጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት፣ በመልስ መመለሻ የጊዜ አመዳደብ፣ በተሳትፎ ዕድል አሰጣጥና በሌሎች ጉዳዮች ነው፡፡ በዚህም የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ከምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ አንፃር ሲታይ፣ የምላሹ ገፅታዎች ሁለት ሲሆኑ እነዚህም አወንታዊ እና አሉታዊ ናቸው፡፡ በመሆኑም በክፍል ውስጥ መስተጋብር ወቅት ለተማሪዎች ሁሉም ምጋቤ ምላሾች ተሰንዝረዋል፡፡ በዚህም በአብዛኛው ግልጽነትን የተላበሱና አበረታች የሆኑ ምጋቤ ምላሾች ለወንድ ተማሪዎች አመዝነው ሲታይ የተድበሰበሱና ግልጽነት የሌላቸው ምላሾች ደግሞ ለሴት ተማሪዎች ተሰንዝረዋል፡፡ በመምህራን የጥያቄ አጠያየቅ ስልት ወቅት በአብዛኛው የወንድ ተማሪዎች የበላይነት ተንፀባርቋል፡፡ ወንድ ተማሪዎች በሚያገኙት ሰፊ የተሳትፎ ዕድል በመጠቀም በርካታ ጥያቄዎችን ሊመልሱ ችለዋል፡፡ የመምህራንን ፈቃድ ሳያገኙ የመመለስ ሁኔታ በአብዛኛው በወንድ ተማሪዎች ላይ ስኬታማ ሲሆን ሴት ተማሪዎች

እጃቸውን ሳያወጡ በሚመልሱበት ጊዜ መምህራን ትችትን ሰንዝረዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ወንድ ተማሪዎች ለጥያቄዎች መመለሻ ጊዜ አንፃራዊ የሆነ ርዝመት ሊያገኙ ችለዋል። በተጨማሪም በክፍል ውስጥ መስተጋብር መምህራን ሴት ተማሪዎችን የሚያበረታቱት ባሳዩት ጥሩ ምግባር እና በንፅህና አጠባበቃቸው ሲሆን ወንዶች ደግሞ የሚበረታቱት ላስመዘገቡት ውጤት ነው። መምህራን ለሴት ተማሪዎች የሚሰነዝሩት ትችት ትምህርታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያነጣጠሩ ሲሆኑ ለወንድ ተማሪዎች የሚሰነዝሩት ደግሞ ትምህርታዊ ያልሆኑ ጉዳዮችን ያማከሉ እንደሆነ ያስገነዝባሉ።

## 2.5 መምህራን ለሴትና ለወንድ ተማሪዎች የሚኖራቸው ግምት ከሥርዓተ ፆታ አያያዝ ጋር ያለው ተዛምዶ

Feldman and Andrew (1982:217) ሲገልጹ የባህሪያዊያን ሳይንቲስቶች አበክረው እንደሚያስገነዝቡት ለአንድ ነገር የምንሰጠው ጥሩ ወይም በጎ ግምት ከነገሮቹ (ከክስተቶቹ) ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ የሁኔታዎች አወንታዊ ጎን እንዲጨምር ያደርገዋል። በዚህም ግምት የራስን ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ባህርይ ሊጎዳ ይችላል። ለዚህ እንደ አንድ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚኖራቸውን ግምት ማየት ነው። Brainard (2002:123) እንዳሰፈረው ከጥሩ መምህር ባህርያት ውስጥ አንደኛው ለተማሪዎች ትምህርትና ስኬት ውጤታማ ነገሮችን ማቅረብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች በትምህርት ሂደቱ ደስተኞች እንዲሆኑ ማበረታታት ነው። Mortimore (1999:94) እና Clifton et al. (1986:58) በበኩላቸው ሲያስገነዝቡ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚኖራቸውን ግምት ከሚወስኑ ነገሮች ውስጥ የመምህራን ግላዊ ባህርይ ዋናው ነው። ይህ ባህርይ ደግሞ ለተማሪዎች በሚኖራቸው አመለካከት ላይ ይንፀባረቃል። ለተማሪዎች የሚሰጡት ግምት መለያየት በራሱ በአያያዝ ወቅት የትኩረት ልዩነትን ያስከትላል።

በሌላ በኩል ደግሞ Plewis (1997:236) ስትገልጽ መምህራን በተማሪዎቻቸው ላይ ዝቅተኛና ከፍተኛ ግምት የሚኖራቸው ከሆነ አድሏዊ ባህርያት አለባቸው ያስብላል። ይሁን እንጂ የግምቱ መለያየት ምንጩ በርካታ ሊሆን ቢችልም በመምህራን ባህርይና ለተማሪዎች በሚኖራቸው ግምት መካከል ዝምድና አለ። የግምት መለያየት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተማሪዎች ችሎታ ላይ የሚንፀባረቅ ቢሆንም ልዩነቱ ግን ከመምህር መምህር ሊለያይ ይችላል።

Rhona et al. (1982:678) እና Cole and Chan (1994:362) በበኩላቸው ሲያብራሩ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በተለያየ መንገድ መያዛቸውና ያላቸው ግምት መለያየት በተማሪዎች ችሎታ ላይ ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ተፅዕኖ ያስከትላል፡፡ ለምሳሌ መምህራን ለተማሪዎች ተሳትፎ የተለያየ ዕድል የሚሰጡ ከሆነ ተማሪዎች በትምህርት ሂደቱ ባለመሳተፍ በውጤታቸው ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተፅዕኖ ያስከትላል፡፡ ይህ የተለያየ አያያዝ ደግሞ በተማሪዎች ተነሳሽነትና ለራሳቸው በሚሰጡት ግምት ላይ ቀጥተኛ ያልሆነ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ ተፅዕኖውም በመምህራን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ፣ ጥያቄ አጠያየቅና በሌሎች ተላውጦዎች ላይ ሊንፀባረቅ ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ እነ Rosenthal (1971:33) እና Mortimore(1999:54-6) ሐሳቡን ሲያጠናክሩ መምህራን ለሴትና ለወንድ ተማሪዎች የሚኖራቸው ግምት አንድ ሊሆን ይገባል፡፡ ሆኖም ለተማሪዎች የሚኖር ከፍተኛም ሆነ ዝቅተኛ ግምት በመማር ማስተማር ሂደት ላይ አሉታዊ ገጽታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ዝቅተኛ ግምት የሚሰጣቸው ተማሪዎች የበታችነት ስሜት ስለሚሰማቸው ውጤት አልባ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ Hatchell (1998:381) ስትገልጽ መምህራን ለሴት ተማሪዎች ከሚኖራቸው ዝቅተኛ ግምት የተነሳ በመማሪያ ክፍል በሚያከናውኗቸው ተሳትፎዎች ላይ ተፅዕኖ ያስከትላሉ፡፡ ይህ ዓይነቱን ልዩነት መምህራን ሆነ ብለው ሳይሆን ከግንዛቤ ውጭ በመሆን ይተገብራሉ፡፡ እነ Makhubu (2000:11) እና Sadker et al. (1999:137) ሲያብራሩ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚኖራቸው ትኩረት ከፍተኛ ግምት ከመስጠትና ከሃላፊነት ጋር ይያያዛል፡፡ በዚህም ሴቶች ተማሪዎች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ዝቅተኛ መሆንና በራስ የመተማመን ችሎታ መሸርሸር ዋና ምክንያት በወንድ መምህራን በኩል የሚኖር የበላይነት አመለካከት ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ እነ Greenberg (1996:117) እና Papalia et al. (1999:357) ሲገልጹ ተማሪዎች ስለራሳቸው ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ግምት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ያላቸው ግምት ከፍተኛ ከሆነ የበለጠ ውጤት ለማምጣት ሊነቃቁ ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንፃር መምህራን ለራስ የሚሰጥ ግምትን በማጎልበትና ውድቀትን በመቀነስ ረገድ ጉልህ ድርሻ አላቸው፡፡ Matlin (1996:60) እና Fontana (1995:12) እንዳስገነዘቡት መምህራን በወንድና ሴት ተማሪዎች ችሎታ ላይ ልማዳዊ የሆነ አድሏዊ ባህርያትን ያንፀባርቃሉ፡፡ በመሆኑም ሴት ተማሪዎች ህግጋትን በመከተልና ጠንክረው በመሥራት ውጤት እንደሚያመጡ ሲያምኑ የወንድ ተማሪዎች ስኬት ደግሞ በተፈጥሮ ስጦታና በፈጠራ ችሎታ እንደሚመጣ ይገምታሉ፡፡

በአጠቃላይ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚኖራቸውን ግምት አስመልክተው የሰፈሩ ድርሳናት እንደሚያስገነዝቡት የመምህራን ግምት መለያየት ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑን ነው፡፡ ተፅዕኖው ደግሞ በመስተጋብር ወቅት በተማሪዎች ተሳትፎና ውጤት ብሎም የወደፊት ራዕይ ላይ ይበረታል፡፡ መምህራን በተማሪዎች ላይ ዝቅተኛ ግምት ካላቸው ተማሪዎች በራስ የመተማመን ብቃት እና ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት አናሳ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ከዚህ አንፃር በክፍል ውስጥ መስተጋብር ለሚከሰተው የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ልዩነት የመምህራን የግምት መለያየት ሰፊ ድርሻ ይዟል፡፡ በመሆኑም የሴት ተማሪዎች ችሎታ በበርካታ ጥረት የተገኘ እንደሆነ ሲገልጹ የወንድ ተማሪዎችን ችሎታ ደግሞ ከተፈጥሮ ከተሰጠ ስጦታ ጋር ያዛምዱታል፡፡ የዚህ ዓይነቱ የግምት መለያየት ከመምህር መምህር ሊለያይ ቢችልም በአብዛኛው ሆነ ተብሎ ሳይሆን ሳያውቁ የሚተገበር መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

## 2.6 የመምህራንን የሥርዓተ ፆታ ግንዛቤ ለማዳበር የሚረዱ ነጥቦች

UNESCO (2003:116)፣ Schumch et al. (2002:197)፣ Connolly (1998:139) እና Alexander (1997:22) እንደገለፁት የሥርዓተ ፆታ ግንዛቤ ሊዳብር የሚችለው በትምህርት ቤት ውስጥ በተማሪዎችና በመምህራን ብሎም በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ አድሏዊ ባህርያንትና ልዩነቶችን መገንዘብ ሲቻል ነው፡፡ ለዚህም ስኬታማነት የአንድ ማህበረሰብ አባላት የሆኑ መምህራን ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በተለየ መልኩ ስለ ሥርዓተ ፆታ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በቂ ግንዛቤ ካላቸው ደግሞ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ሴትና ወንድ ተማሪዎችን እኩል የሆነ ዕድል በመስጠት ያሳትፋሉ፡፡ እነ Rich and Brown (2002:80)፣Schultz (1997:177) እናGhosh and Tarrow(1993:82-5) ሲያብራሩ የመምህራን ስልጠና ሥርዓተ ፆታን መሠረት ሊያደርግ ይገባል፡፡ በስልጠና ወቅት ደግሞ ለባህል ነክ ጉዳዮች ቅድሚያ መሰጠት አለበት፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ መምህራን በክፍል ውስጥ ከሴትና ወንድ ተማሪዎች ጋር ለሚኖራቸው መስተጋብር በማህበረ ባህላዊ ግፊት ሳቢያ ለሚከሰቱ መሰናክሎች መፍትሄ ያገኛሉ፡፡ ለዚህም በሚጠቀሙት የማስተማሪያ ዘዴና በክፍል ውስጥ አመራር ላይ አወንታዊ አመለካከትን በማስረጽ ባህልን ከግምት ውስጥ በማስገባት ረገድ ጉልህ ድርሻ አላቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ Elliott et al. (2000:134)፣ Katapa and Swilla (1999:26) እና Shaffer (1994:310) እንዳሠፈሩት መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ በክፍል ቁጥጥር ከአለቃ ጀምሮ በመማር ማስተማር ሂደቱ በሚከናወኑ ችግር ፈቺ ተግባራት ላይ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማበረታታት አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ሥርዓተ ፆታን የተመለከቱ ልማዳዊ

አድሏዊ ባህርያትን ለማስወገድ ለሴትና ወንድ ተማሪዎች እኩል የተሳትፎ ዕድል መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መስተጋብሩ አወንታዊ ይሆን ዘንድ አሉታዊ ምስል ሊፈጥሩ የሚችሉ ባህርያትን መገንዘብ፣ በጥያቄና መልስ ሂደት ሴቶችን ስም በመጥራት ማሳተፍና ማበረታቻ መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ይህን ሃሳብ በማጠናከር Ayim and Houston (1996:55) ሲያስገነዝቡ መምህራን በሥርዓተ ፆታ ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ ለመለካት ከሚያስችሏቸው ነጥቦች ውስጥ በክፍል ውስጥ ሴትና ወንድ ተማሪዎችን እኩል እይዛለሁ?፣ በመስተጋብር ሂደቱ ሁለት ሦስተኛ (2/3)ኛ የሚሆነውን ጊዜ ከወንድ ተማሪዎች ጋር አሳልፋለሁ?፣ ወንዶች ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ፤ ሴቶች ደግሞ ጥሩ ምግባር ሲኖራቸውና ንፅህናቸውን ሲጠብቁ ነው የማበረታታ?፣ ወንዶች ደካማ ሥራ ሲሠሩ ሴቶችን ደግሞ በሌላ መስፈርት ነው የምተቻቸው?፣ የወንዶችን ውጤት ከችሎታ፤ የሴቶችን ደግሞ ከዕድል ወይም ከፈተና(ከትምህርት) ክብደት ጋር አያይዛለሁ?የሚሉትን ማጤን ይጠበቅባቸዋል፡፡

እነ Fackson and Salisbury (1996:105) በበኩላቸው ሲገልጹ በትምህርት መስክ የሚስተዋለውን የሥርዓተ ፆታ ልዩነት ለማጥበብ በብሪታኒያ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ መምህራን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በስልጠናውም የተወሰኑ ሴት መምህራን ለውጥ በማምጣት ቀዳሚውን ሥፍራ ይዘዋል፡፡ ይኸውም በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ይታይ የነበረውን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ልዩነት ለማጥበብ ችለዋል፡፡ በሂደት ደግሞ ወንድ መምህራን ችግሩን በመቀነስ ረገድ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ሰፊ ነው፡፡ ጉዳዮን አስመልክቶ አንድ ወንድ ተማሪ“ በሥርዓተ ፆታ ሚናዎች ላይ ማንኛውም ሰው ቢጠየቅ የተሳሳተ መንገድ ሲከተል እንደነበር ይገልፃል” በማለት አስተያየት ሰጥቷል፡፡

Santrock (2001:190) በበኩሉ ሲያስገነዝብ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሴቶችም ሆኑ ወንድ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ከግብ ለማድረስ ከሥርዓተ ፆታ አድልዎ ነፃ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከመምህራን የሚከተሉት ባህርያት ይጠበቃሉ፡፡

- ከፆታዊ አድሎዎች ውጭ ለሆኑ ሚናዎች ናሙና መምህር መሆን፣
- ሁለቱንም ፆታዎች በክፍል ውስጥ የቡድን ተግባራትን እንዲያከናውኑ በማድረግ በተቆጣጣሪነት (በአለቃነት) ማሳተፍ፣
- መልመጃዎች ከሥርዓተ ፆታ አድልዎ ነፃ ስለመሆናቸው በቅድሚያ ማረጋገጥ፣
- በጥያቄ አጠያየቅና ማበረታቻ አሰጣጥ ወቅት ለሁሉም እኩል ትኩረት መስጠት፣
- ከአድሏዊ ገለፃ የፀዳ ቋንቋ መጠቀም፤ ተውላጠ ስሞችን በተገቢ ቦታቸው መገልገል፣

- በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ፆታዊ አድሎዎችን የሚያንፀባርቁ ነጥቦች ከተካተቱ ከተማሪዎች ጋር በጉዳዩ ላይ መወያየት፣
- በትምህርት ላይ የፆታ እኩልነትን በሚመለከት ያለንን ዕውቀት ማጎልበት፣ሙያዊ መጣጥፎችን ማንበብ፣ ስለሴቶችና ወንዶች ያለብንን ግጼታ መገንዘብ ናቸው፡፡

በመጨረሻ የትምህርት ልማት አካዳሚ (ዓ.ም ያልተጠቀሰ:42) እንዳሰፈረው የሥርዓተ ፆታ ግንዛቤ ለማዳበር በመምህራን እንዲወሰዱ ከሚበረታቱ ርምጃዎች ውስጥ ቀጥሎ የቀረቡት ነጥቦች ይጠቀሳሉ፡፡

- ሴት ልጆች በክፍል ውስጥ እንዲሳተፉ ያበረታቱ፣
- ውጤታማ የሆነ ተግባቦት ያካሂዱ፣ፆታ ተኮር የሆነ ቋንቋ ይጠቀሙ፣
- የሚያስተላልፉት መልዕክት ግልጽ ይሁን፣መልዕክትዎንም ሁሉም ተማሪዎች መረዳታቸውን ያረጋግጡ፣
- ሁለቱም ፆታዎች ከትምህርቱ ተግባራት ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ያረጋግጡ፣
- ሴትና ወንድ ልጆችን ባካተተ መልክ የተማሪ-ተማሪ መስተጋብር ያበረታቱ፣
- ሁሉንም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያትጓቸው፣
- እርስዎና ተማሪዎቹ (ሴቶችም ወንዶችም) እርስ በርስ መግባባታችሁን ያረጋግጡ፣
- ሴቶችና ወንዶች ልጆች አንድ አይነት ሚና መጫወት፣ አንድ አይነት ሥራ መስራት እንደሚችሉ አድርገው ይሳሏቸው፣
- በዓበይት ሥራዎች ላይ ሴቶችና ወንድ ተማሪዎችን ይወክሏቸው፣
- በመጽሐፍትና በማስተማሪያ መሣሪያዎች ውስጥ የሚገኙ የሥርዓተ ፆታ ልማዳዊ አጉል አስተሳሰቦችን እየለዩ በማውጣት ያቃኗቸው፣
- ሴት ተማሪዎችን የሰው የበታች አድርጎ የማያቀርብ ተገቢ ቋንቋ ይጠቀሙ፣
- ፆታ ተኮር የሆኑ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ይጠቀሙ፣
- በክፍል አወንታዊነት ያላቸውን እንስቶች በአርአያነት ይደግፉ፣ በአካባቢው ያሉ ስኬታማ ሴቶችን በመጥራት ለክፍሉ ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉ ይጋብዙ፣
- በክፍል ውስጥ ተግባራት ለሁለቱም ፆታዎች እኩል የሃላፊነት ድርሻ ይስጡ፣
- ሴቶችንም ሆነ ወንዶች ተማሪዎች በሚያበረክቱት ተሳትፎ አይሳለቁባቸው፣
- ጊዜ ይስጧቸው፣ይህም ተማሪዎቹ እንዲያስቡ፣ መልስ እንዲያሰናዱና በራስ መተማመን ዕድል የሚሰጣቸው ከመሆኑም በላይ፣ በመምህርና በተማሪዎቹ መካከል ያለውን መስተጋብር ለማጎልበት ይረዳል፡፡ በዚህ ጊዜ ዋናው ጉዳይ መልሶቹ ክትትል ወይም

ስህተት መሆናቸውን ሳይሆን፣ ቁምነገሩ በአእምሯዊና በስሜታዊ ትምህርትነቱ ላይ ነው፣

- በክፍል ውስጥ ተግባራት እኩል ድርሻና ኃላፊነት ይስጡ፤ ለምሳሌ ሁሉም ተማሪዎች በቡድን የሚሠራ ፕሮጀክት ቢሰጣቸው መምህሯ(ሩ) በቡድን ውስጥ ያሉት ተሳታፊዎች ከሁለቱም ፆታዎች መውጣጣታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፣
- የፕሮጀክት መሪ ወይም የክፍል አለቃ በሚመረጥበት ጊዜ ወይም የክፍል ውስጥ አቅርቦቶች በሚካሄዱ ጊዜ ሁለቱም ፆታዎች መወከል አለባቸው፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ የመምህራንን የሥርዓተ ፆታ ግንዛቤ ለማዳበር የቀረቡ ጽንሰ ሐሳቦች እንደሚያስረዱት መምህራን የሙያ ግዴታቸውን በአግባቡ ለመወጣትና ልፋታቸው ፍሬ እንዲታይበት የሥርዓተ ፆታ ግንዛቤያቸው መዳበር አለበት፡፡ ለዚህም በክፍል ውስጥ መስተጋብር አሉታዊ አመለካከቶችን ማስወገድ ቀዳሚ ነጥብ ነው፡፡ አሉታዊ የሆኑ አመለከከቶችን ለማስወገድ ደግሞ ሴትና ወንድ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መስተጋብር የሚሰጣቸውን ሚና ማመሳሰል ይገባል፡፡ ለዚህም በትምህርት ሂደቱ የሚሰሩ ተግባራትን ሴትና ወንድ ተማሪዎች በእኩል ሊተገብሩት እንደሚችሉት ማመን በራሱ ለውጥ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የተወሰኑትን ተማሪዎች የሚያንቋሽሽና የማያበረታታ አስተያየቶችን ከመስንዘር መቆጠብ ይገባል፡፡ ለውጤታማነቱም በአርዓያነት በሚጠቀሱ እንስት ፆታዎች ላይ ውይይት እንዲያካሂዱ መጋበዝ መልካም ነው፡፡ በውይይት ሂደት ለተግባቦት የሚያውሉት የቋንቋ አጠቃቀም የሥርዓተ ፆታ አድሏዊ ባህርያትን የሚያንፀባርቅ መሆን የለበትም፡፡ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማጎልበት በክፍል ውስጥ በጥንድም ሆነ በቡድን በሚሰሩ ተግባራት ላይ ሁለቱንም ፆታዎች ለቁጥጥር ሂደት ማጨት ተገቢ ነው፡፡ ለዚህና መሰል መሠረታዊ ለውጦች ደግሞ መምህራን ራሳቸውን ከአዳዲስ ዕውቀቶች ጋር በማስተዋወቅ ግንዛቤያቸውን ሊያጎለብቱ ይገባል፡፡

## 2.7 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ-ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበራቸውን መመርመር ነው፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ ይኖራቸዋል በሚል በኢትዮጵያና በውጭ ቋንቋዎች ክፍለ ትምህርት የቀረቡ ጥናቶችን ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡

ሥርዓተ ፆታን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቋንቋን ከመማርና ከማስተማር ረገድ ያለውን ልዩነት የፈተሹ ጥናቶች ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ያህል ፋንቱ ደምሴ (1989) የፆታ ልዩነት አማርኛ

ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና በሚል ርዕስ ጥናት አቅርባለች፡፡ የጥናቷ ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ አጠቃላይ ብቃት ረገድ የፆታ ልዩነት ያለውን ሚና መመርመር ነው፡፡ ይህን ዓላማ መሠረት በማድረግ በአማርኛ ቋንቋ አጠቃላይ ብቃት ረገድ የሴትና የወንድ ተማሪዎች ፆታ መለያየት ምንም ሚና እንደሌለው የጥናቷ ውጤት አረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር በመማር ማስተማር ክንውን ዝርዝር ጉዳዮች ላይ የፆታ ልዩነት ያለውን ሚና መፈተሽ እንደሚቻል አስተያየት ሰጥታለች፡፡

ሌላው ሂሩት ካሣው (1997) የሴትና የወንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት በሚል ርዕስ ጥናቷን አካሄዳለች፡፡ ይህ ንጽጽራዊ ጥናት በአዲስ አበባ ክልላዊ መስተዳደር የሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት በሁለቱ ፆታዎች መካከል የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ልዩነት መኖሩንና ልዩነቱ የጎላ መሆኑን ማየት ነው፡፡ የጥናቱ ውጤት ሴት መምህራን የተማሪዎችን ተነሳሽነት በመጨመር፣ ዴሞክራሲያዊ የሆነ አመራር በመስጠት፣ ሥነ-ስርዓትን በማስጠበቅ ተማሪዎችን በዓይን በመከታተልና በመሃላቸው በመዘዋወር እንደሚተገብሩ አመላክቷል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች በተጨማሪ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቀረቤታ አላቸው ከሚባሉት ውስጥ የበላይ ሰይድ (1992) እና የዳናይት በላይ (2006) ጥናቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በላይ ሰይድ (1992 ዓ.ም.) የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ የሚል ጥናት አቅርባለች፡፡ የጥናቱ ዓላማም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ መስተጋብር የሴት ተማሪዎችን ቃላዊ ተራክቦ መጠን መመርመርና የመምህራን ትኩረት ከተሳትፏቸው ጋር ግንኙትት እንዳለው መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ዓላማ መሠረት በማድረግ ከመረጃዎች ትንተና የተገኘ ውጤት ሴቶች ከወንዶች በሚበዙበት፣ ሴቶችና ወንዶች ተመጣጣኝ በሆኑበትና ሴቶች ከወንዶች በሚያንሱበት ምድብ ውስጥ የወንዶች ተሳትፎ ከሴቶች የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በየምድቦቹ በሚማሩ ሴት ተማሪዎች መካከል የመምህራን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ወንዶች በሚበዙበት ምድብ ውስጥ ከሚማሩ ሴቶች ከሌሎች ምድቦች አንጻር የበለጠ የመምህራን አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽና ትኩረት ሊያገኙ እንደቻሉ አስገንዝባለች፡፡ በመጨረሻም የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን

የሚያደርጉ ችግሮችን ለመፈተሽ እንዲያስችል በሌሎች የክፍል ደረጃዎች ጥናቱ ቢካሄድ ተጨማሪ መፍትሔ ለመፈለግ ያስችላል የሚል አስተያየት ሰንዝራለች፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ ቋንቋዎች ክፍለ ትምህርት ዳናይት በላይ እ.ኤ.አ. በ2006 በእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ልዩነት በመምህር ተማሪ መስተጋብር በሚል ርዕስ ጥናት አቅርባለች፡፡ ጥናቷ በአዲስ አበባ መስተዳድር በሚገኙ አራት የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ እና 11ኛ ክፍል በሚያስተምሩ መምህራን ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ በመምህር ተማሪ መስተጋብር ወቅት የተማሪዎች ፆታ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ መፈተሽ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በክፍል ውስጥ መስተጋብር የመምህራን የንግግር ድርሻ ሰፊ መሆኑንና አብዛኛው ትኩረታቸው ወደ ወንድ ተማሪዎች እንደሆነ በጥናቷ አስገንዝባለች፡፡

ከላይ በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ላይ የተዳሰሱ ሥራዎች ሥርዓተ-ፆታ ተኮር በመሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ ሆኖም በመምህራን የሥርዓተ-ፆታ አያያዝና በክፍል ውስጥ አተገባበራቸው ላይ ማተኮሩ ጥናቱ በሚካሄድበት ቦታ፣ በተጠኝዎች፣ በክፍል ደረጃ፣ በጊዜ፣ በዓላማና በአቀራረብ ይለያል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴ

ይህ ገላጭ ቃኝ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበርን የሚያጠና ሲሆን የአጠናን ዘዴው ደግሞ መጠናዊ (Quantitative) እና ዓይነታዊ (Qualitative) የምርምር ዘዴን የተከተለ ነው።

## 3.1. ተጠኝዎች

በተጠኝነት የተመረጡት በከተማው የሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው። እነሱም በጣና ሐይቅ፣ በግዮንና በፋሲሎ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ1999ዓ.ም በ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራንና ተማሪዎች ናቸው። ለዚህ ዓላማም ተግባራዊነት ይሁነኝ የናሙና አመራረጥ ስልት (Purposive Sampling) ሥራ ላይ ውሏል። ለዚህ በምክንያትነት የሚፈረጁት በባህር ዳር ከተማ ዘጠነኛ ክፍልን በማስተማር ላይ የሚገኙ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች እነዚህ ብቻ በመሆናቸውና አጥኝዋ ለጥናቱ መረጃ በዓይነትና በመጠን ወካይ ናሙና ለመሰብሰብ ያስችላል የሚል ሀሳብ ስላደረባት የተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል። በተጨማሪም ክልሉ እና የክፍል ደረጃው የተመረጠበት ምክንያት እስካሁን ሥርዓተ ፆታን መሠረት ያደረጉ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች በአዲስ አበባ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች እና ይበልጥ በ11ኛ ክፍል ላይ ያተኮሩ በመሆናቸውና በ9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራንንና ተማሪዎችን ጥናቱ እስኪ.ጠናቀቅ ድረስ ማግኘት ስለሚቻል ነው።

ከላይ በተዘረዘሩት ሦስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን 10 ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል በክፍል ውስጥ እያስተማሩ እያሉ የምስል ቀረጻው እንዲካሄድ ፈቃደኛ የሆኑ ስድስቱ ብቻ በተጠኝነት ተመርጠዋል። ከእነዚህ መካከል ሦስቱ ወንዶችና ቀሪዎቹ ሦስት ሴቶች ናቸው። እነዚህም ሁለቱ ከጣና ሐይቅ፣ ሁለት ከግዮንና ሁለት ከፋሲሎ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ ናቸው። መምህራን በተጠኝነት ከተለዩ በኋላ ስድስቱ መምህራን ከሚያስተምሩባቸው ስድስት ስድስት ምድብ (Section) የመማሪያ ክፍሎች መካከል ሁለት በነሲብ ናሙና (Random Sampling)ተወስደዋል። ከፋሲሎ (9ኛ C፣ F፣S እና W)፣ ከጣና ሐይቅ (9ኛ 2፣4፣6 እና 9)፣ ከግዮን (9ኛN፣ Q፣V እና Z)።

በአጠቃላይ 12 የመማሪያ ክፍሎች ላይ ጥናት ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም ከሦስቱ ትምህርት ቤቶች መካከል እያንዳንዳቸው መምህራን ከሚያስተምሩበት ምልከታ ከተደረገባቸው በ12ቱ ምድብ ክፍሎች ከሚገኙ 792 ተማሪዎች መካከል አንድ ሦስተኛ ከክፍሉ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ (Proportionally) 264 ተማሪዎች በዚህ ጥናት ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ከነዚህ መካከል 132 ሴቶች ሲሆኑ ቀሪ 132 ወንድ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ለዚህም በየምድቡ ያሉት የወንድና ሴት ተማሪዎች ስም ዝርዝር ለየብቻ ከተለየ በኋላ ባላቸው እለፍ ተቀደም መሠረት ከሦስት ተከታታይ ተማሪዎች ውስጥ አንዱን ሥርዓታዊ የነሲብ ናሙና ዘዴን (Systematic Random Sampling) በመጠቀም ከእያንዳንዱ ክፍል 22 ተማሪዎች ተወስደዋል፡፡ ከነዚህም መካከል 11 ሴትና 11 ወንድ ናቸው፡፡

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

በዚህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የሥርዓተ ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበራቸውን ለመመርመር ተገቢ ይሆናሉ ተብለው የተመረጡ የመረጃ መሰብሰቢያዎች ምልከታ፣ ለመምህራንና ለተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከጥናቱ የሚገኘውን ውጤት ለማጠናከር ሦስት ጎንዮሻዊ ጥምርታን (Triangulation) መሠረት ያደረገ የአጠናን ዘዴ ነው፡፡

### 3.2.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

Bailey (1994:242-246)ሲገልጽ የምልከታ ዓይነቶች በተለያዩ ምድብ ይከፈላሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል መጠናዊ (Quantitative) እና ዓይነታዊ (Qualitative)፣አሳታፊ (Participant) እና ኢ-አሳታፊ (Non-Participant) እና የተደራጀ (Structured) እና ያልተደራጀ (Un Structured) ይባላሉ፡፡ ለዚህ ጥናት ተግባር ላይ የዋለው ቀደም ብሎ የተዘጋጀ የምልከታ ማመሳከሪያ ቅጽ (Observation Checklist) ወይም መጠናዊ (Quantitative) የሚባለው የምልከታ ዓይነት ነው፡፡ የምልከታ ማመሣከሪያ ቅጹም እነ Plessis and et al (2002:86) በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚካሄድ የመምህር ተማሪ መስተጋብር የመምህራንን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ለመመርመር የሚያስችሉ ናቸው ያሏቸውን ነጥቦች መሠረት ያደርገ ነው፡፡

በተጨማሪም ይህን የክፍል ውስጥ የምልከታ ማመሳከሪያ ቅጽ አማካሪዬና ሌሎች ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በምልከታ ማመሳከሪያ ቅጹ ትኩረት የሚሰጥባቸው ነጥቦች አስቀድመው በፈታሽ ጥናት(Pilot Study) ወቅት ተለይተዋል፡፡ በጥቅል አገላለጽ የመምህራን ጥያቄ አጠያየቅ፣ የተማሪዎች ትክክለኛም ሆነ የተሳሳተ መልስ

አሰጣጥ፣ የመምህራን አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ ወይም ምንም ምላሽ አለመስጠት፣ የጥያቄ መጠየቂያ ጊዜ አመዳደብ፣ በስም እየጠሩ ማሳተፍ፣ በተማሪዎች ምላሽ ጣልቃ መግባት፣ የተማሪዎች እጅ ሳያወጡ መመለስ የሚሉት በዋናነት የሚነሱ ሲሆኑ አጠቃላይ የትኩረት ነጥቦች 10 ናቸው፡፡ የመማሪያ ክፍል ምልከታው ስልጠና በተሰጣቸው ሁለት አጋሮችና በአጥኝዋ አማካይነት ተካሂዷል፡፡ በምልከታው ጊዜ የግል አስተያየት እንዳይካተት እና የትግበራዎችን ድግግሞሽ መጠን በውል በመለየት መረጃውን ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል፡፡

የክፍል ውስጥ ምልከታው በመቅረፀ-ምስል (Video-Camera) እንዲታገዝ ተደርጓል፤የምስል ቀረጻው ሂደት ሁለት ዓይነት ገጽታን የተላበሰ ነው፡፡ የመጀመሪያው ቀረጻ በማስመሰል (Simulation) ተካሂዷል፡፡ በዚህም መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በመስተጋብር ወቅት የሚያካሂዷቸው ተዘውታሪ የሆኑ ተግባራት በመቅረጫ መሣሪያውና አዲስ ሰው በመኖሩ ሳቢያ እንዳይገታ ለማድረግ ውሏል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የተካሄዱ ቀረጻዎች ለጥናቱ በቀጥታ ተግባራዊ የሆኑ ሲሆን በምልከታ ወቅት ሳይስተዋልባቸው የቀሩ ነጥቦችን እንደገና ደግሞ በማየት መረጃውን እንዲያጠናክሩ ሆነዋል፡፡

Bailey (1994:247) እንዳስገነዘበው የተደራጀ የምልከታ ማመሣከሪያ ሰነድ በምንጠቀምበት ጊዜ የሚታዩትን ባህርያት ድግግሞሽ መጠን በመቁጠር ወዲያው መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም በምልከታ ወቅት እየተደጋገመ የሚታዩ ባህርያትን በማመሣከሪያ ቅጽ ላይ ማስፈር ተገቢ ነው፡፡ ድምሩ ጥርጣሬን እንዳያስከትል የተወሰኑትን የድግግሞሽ መጠን በአንድ እየተጣመሩ ተደራጅተዋል፡፡

በክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት ከአጥኝዋ በተጨማሪ ሌሎች ሁለት አጋሮች ተሳታፊ ሆነዋል፤ አጋሮች የምልከታው ተቀዳሚ አላማ ምን እንደሆነ ከተገለጸላቸው በኋላ በክፍል መስተጋብር ላይ ሊተኩርባቸው የሚገቡ ተላውጦዎችን በዝርዝር እንዲገነዘቡ ተደርጓል፡፡

### 3.2.2. የፅሁፍ መጠይቅ

ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ የጽሑፍ መጠይቆች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው ለመምህራን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለተማሪዎች የተዘጋጁ ናቸው፡፡ እነዚህ የጽሑፍ መጠይቆች ለዋናው ጥናት ተግባራዊ ከመደረጋቸው በፊት በአማካሪዬ እና በሌሎች

ባለሙያዎች ከተገመገመ በኋላ በፈታሽ ጥናት (Pilot Study) አማካይነት ለኪነታቸው ተፈትኖ አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል።

### 3.2.2.1. የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ

የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሚከናወኑ ተግባራት አንፃር የመምህራንን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ለመፈተሽ የቀረቡ ናቸው። እነዚህም መምህራን በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ያለውን የተሳትፎ ልዩነት ለመለየት የሚያስችሉ፣ መምህራን ስም በመጥራት የሚያሳትፏቸው በአብዛኛው ለየትኞቹ ፆታዎች እንደሆነ፣ ለተማሪዎች የሚሰጧቸው ጥያቄዎች፣ አስተያየቶች እና ማበረታቻዎች ምን መልክ እንዳላቸው፣ የጥያቄ መመለሻ ጊዜ አሰጣጥ፣ የሴትና የወንድ ተማሪዎች ጥያቄ የመጠየቅ ተነሳሽነትን ወዘተ በተመለከተ የጽሐፍ መጠይቆች በማዘጋጀት ተሞልቷል። የመጠይቆች አቀራረብም በምርጫ መልክ በደረጃ የቀርቡ ሲሆኑ ብዛታቸው ደግሞ 10 ነው። አቀራረባቸውም አምስት ምርጫዎችን አካቷል። በዚህ መሠረት ምርጫ 1= በፍጹም አልስማማም፣ 2= አልስማማም፣ 3= ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 4= እስማማለሁ እና 5= በጣም እስማማለሁ የሚሉትን ያመለክታሉ። የጥያቄዎቹ ይዘቶች አወንታዊና አሉታዊ ገጽታን የተላበሱ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ የመምህራንን የጥያቄ አጠየየቅ የሚመለከቱት በተራ ቁጥር 6፣7 እና 10 ላይ የሰፈሩት ሲሆኑ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን የሚጠይቁት ደግሞ በተራ ቁጥር 1፣ 4 እና 8 ላይ የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው። በተጨማሪም የመምህራንን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ የሚጠይቁት በተራ ቁጥር 2፣ 3 እና 9 ላይ ሲሰፍሩ የቆይታ ጊዜ አሰጣጥን የሚለካ ደግሞ በተራ ቁጥር 5 ላይ ቀርቧል።

### 3.2.2.2. የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ

በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመምህራንን የሥርዓተ ፆታ አያያዝና አተገባበር በሚመለከት ለሚደረግ ጥናት የተማሪዎች በጥናቱ ተሳታፊ መሆን አያጠያይቅም። በዚህ መሠረት ለጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ 132 ሴት እና 132 ወንድ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል። የጥያቄዎች አቀራረብ በደረጃ በምርጫ መልክ የቀረበ ዝግ እና ክፍት ሲሆን ይዘቶችም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ስለሚሰጣቸው የተሳትፎ ዕድል፣ አሉታዊ ሆነ አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ፣ ስለሚኖራቸው ተሳትፎ፣ ተነሳሽነት፣ በአጠቃላይ ምን ያህል እኩል የሆነ ፆታዊ ተሳትፎን ወይም የሥርዓተ ፆታ እኩሌታን ተግባራዊ እንደሚያደርጉ መረጃ ለማግኘት ተዘጋጅቷል።

በደረጃ የሰፈሩ ጥያቄዎች አቀራረብ አራት ምርጫዎችን ይዘዋል። ምርጫ 1= ፈፅሞ ሐሰት ነው፣ 2= አንዳንድ ጊዜ (አልፎ አልፎ) ትክክል ነው፣ 3= አብዛኛውን ጊዜ ትክክል ነው እና 4= ሁልጊዜ ትክክል ነው የሚሉትን የሚያመለክቱ ናቸው። አጠቃላይ አወንታዊ እና አሉተዊ ይዘት ያላቸው 22 ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመምህራንን አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ የሚያንፀባርቁ በተራ ቁጥር 1፣11፣13 እና 15 ላይ ሲገኙ አሉታዊ ምጋቤ ምላሾችን የሚያሳዩት ደግሞ በተራ ቁጥር 4፣7፣16 እና 20 ላይ ሰፍረዋል። የመምህራንን የጥያቄ አጠያየቅ የሚያመለክቱ ደግሞ በተራ ቁጥር 2፣3፣5፣9፣12 እና 19 ላይ የቀረቡ ሲሆን የቆይታ ጊዜ አሰጣጥን የሚያሳዩት ደግሞ በተራ ቁጥር 10፣17፣ እና 22 ላይ ይገኛሉ። የመምህራንን የተሳትፎ እድል አሰጣጥ የሚያንፀባርቁ ጥያቄዎች በተራ ቁጥር 6፣8፣14፣ 18 እና 21 ላይ ተካተዋል። በተጨማሪም በክፍት ጥያቄ አቀራረብ የተዘጋጁ ሦስት ጥያቄዎች ይገኛሉ።

### 3.2.3 ቃለ መጠይቅ

ምልከታው ከተካሄደ በኋላ ለመምህራን ቃለ መጠይቅ ተደርጓል። የቃለ መጠይቁ የትኩረት ነጥቦችም ለመምህራን በሚዘጋጁ የጽሑፍ መጠይቆች አማካይነት ሊገኙ ባልቻሉ መረጃዎች ላይ ነው። በውስጡም በሴትና በወንድ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ ያለው ልዩነት ምን እንደሆነ፣ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ ለየትኛው ፆታ እንደሚያደላ፣ ምጋቤ ምላሹ ምን ዓይነት ተፅዕኖ እንደሚኖረው፣ ለሁለቱም ፆታዎች እኩል የሃላፊነት ድርሻ እንደሚሰጡ ለመለየት የተዘጋጁ ናቸው።

## 3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ለጥናቱ የሚያስፈልገው መረጃ በምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅ እና በቃለ መጠይቅ ከተሰበሰበ በኋላ ትንተናው ዓይነታዊ (Qualitative) እና መጠናዊ (Quantitative) ዘዴዎችን ተጠቅሟል። በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ ተማሪዎች ቁጥር ወደ መቶኛ ተለውጦ ለማቅረብ በቂ በመሆኑ ከተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በመቶኛ እየተለወጠ በአማካይ (Mean) የሴቶችና የወንዶች ልዩነት በቲ- ስታስቲካዊ ስሌት ቀርቧል። የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ1= ፈጽሞ ሐሰት ነው፣ 2= አንዳንድ ጊዜ(አልፎ አልፎ) ትክክል ነው፣ 3= አብዛኛውን ጊዜ ትክክል ነው፣ እና 4= ሁልጊዜ ትክክል ነው የሚሉ ምርጫዎችና 22 ጥያቄዎችን አካትቶ ይዟል። እነዚህ ጥያቄዎች በአራት ጽንሰ ሀሳቦች ዙሪያ እንደሚያጠነጥኑ በንዑስ ክፍል 3.2.2.2 ሰፍሯል፤ ዝርዝሩን ይመለከቷል። ጥያቄዎቹ አወንታዊና አሉታዊ ይዘት ያላቸው ሲሆን በደረጃ በቀረቡበት መልክ የሚይዙት ዋጋ እየተደመረ ተተንትኗል።

ሌሎች በምልከታ እና ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ በመገኘት ለስሌት አመቺ የሆኑ መረጃዎች በመጣኝ ትንተና ዘዴ ተተንትኗል፡፡

የክፍል ውስጥ ምልከታው በአጥኝዋና ስልጠና በተሰጣቸው ሁለት አጋገሮች አማካይነት በማመሳከሪያ ቅጹ መሠረት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በእያንዳንዱ ምልከታ የተገኙ ውጤቶችን ደምሮ ለሶስት በማካፈል አማካይ ውጤቱ ለትንተና በቅቷል፡፡ በመምህር ተማሪ መስተጋብር ወቅት የተካሄዱትን ቃላዊ ተግባቦቶች ከመቅረፀ ምስሉ በማየት ተመዝግቧል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ1ን ይመለከቷል) የንግግር ልውውጦች ከተመዘገቡ በኋላ ለጥናቱ መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦችን ድግግሞሽ በመቁጠር መምህራን ለሴትና ለወንድ ተማሪዎቻቸው የሚሰጡት አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ፣ የጥያቄ አጠያየቅ ስልት፣ የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥና የጥያቄ መመለሻ ጊዜ አመዳደብን በተመለከተ የተስተዋለው ልዩነት በዝርዝር ቀርቧል፡፡

የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ለመፈተሽ ከምልከታው በተጨማሪ ለመምህራን መጠይቅ ቀርቧል፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ 10 ጥያቄዎችንና በደረጃ የቀረቡ አምስት ምርጫዎችን እንዳካተተ በንዑስ ክፍል 3.2.2.1 ሰፍሯል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች አራት ጽንሰ ሐሳቦችን (የምጋቤ ምላሽ፣ የጥያቄ አጠያየቅ፣ የቆይታ ጊዜ እና የተሳትፎ እድል አሰጣጥን) የሚመለከቱ ናቸው፡፡ እነዚህ አወንታዊና አሉታዊ ይዘትን የተላበሱ ጥያቄዎች የያዙት ምርጫ ቁጥሮች እርስ በርስ ተደምረዋል፡፡ ለዚህም በምርጫ ቁጥር 5 እና 4 የያዙት ዋጋ አንድ ላይ ተደምሯል፤ ምርጫ ቁጥር 1 እና 2 ደግሞ አሉታዊ ገጽታ ያላቸው በመሆኑ አንድ ላይ በመደመር ሲተነተን ምርጫ ቁጥር 3 ግን እንዳለ ለትንተና ቀርቧል፡፡ ሌሎች ከመምህራን በቃለ መጠይቅና ከተማሪዎች ክፍት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በዓይነታዊ አተናተን ዘዴ ሊተነተኑ ችለዋል፡፡ በአጠቃላይ ከምልከታ ፣ ከመምህራንና ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ እና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በአንድ ላይ እየተደጋገፉ ተተንትነው ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የሥርዓተ ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበራቸውን መመርመር ነው። ይህንን መሠረታዊ ዓላማ በመያዝ በምዕራፍ ሦስት በቀረቡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አማካኝነት መረጃዎች ተሰብስበዋል። የተሰበሰቡት መረጃዎች ከዚህ በታች በተለያዩ ዓብይና ንዑሳን ክፍሎች የቀረቡ ሲሆን በጣና ሐይቅ፣ ግዮን እና ፋሲሎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተደረጉትን ምልከታዎች፣ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ ውጤቶች ትንተና እየተደረገባቸው ማብራሪያ ይሰጥባቸዋል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ መረጃዎችን በዓይነታቸው በመመደብ በሰንጠረዥ መልክ ለማቅረብ ተሞክሯል።

## 4.1. የጥናቱ መረጃ ምንጮች (የተጠኝዎች) አጠቃላይ ገለፃ

በዚህ ጥናት ውስጥ በተጠኝነት የተመረጡ መምህራን ከብዛት፣ ከፆታ፣ ከትምህርት ደረጃ፣ ከአገልግሎት ዘመንና ከስልጠና አንፃር ገለፃ ተሰጥቶባቸዋል። በተጨማሪም ተጠኝ ተማሪዎች ከሚማሩበት ትምህርት ቤት፣ ከብዛት፣ ከፆታ እና ከዕድሜ አንፃር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 1፡- የተጠኝ መምህራን ብዛት፣ ፆታና የትምህርት ደረጃ

| ትምህርት ቤት | የመምህራን ብዛት | ፆታ | | የትምህርት ደረጃ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | 12+2 | 12+4 |
| ጣና ሐይቅ | 2 | 1 | 1 | - | 2 |
| ግዮን | 2 | 1 | 1 | - | 2 |
| ፋሲሎ | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 |

በጣና ሐይቅ፣ ግዮን እና ፋሲሎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በዘጠነኛ ክፍል ለማስተማር የተመደቡ ሁለት ሁለት መምህራን ይገኛሉ። ከእነዚህም መምህራን ውስጥ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ከየትምህርት ቤቶቹ ተመድበዋል። መምህራኑ በጥናቱ ውስጥ የታቀፉ ሲሆን ከአንድ መምህርት በስተቀር ሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ናቸው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ሠንጠረዥ 2:- የተጠኝ መምህራን የአገልግሎት ዘመን ከስልጠና መስክ አንፃር፣

| ትምህርት ቤት | የአገልግሎት ዘመን | | የስልጠና መስክ | |
|---|---|---|---|---|
| | ሴ | ወ | ዓብይ | ንዑስ |
| ጣና ሐይቅ | 28 | 32 | ፔዳጎጂክስ | አማርኛ |
| | | | አማርኛ | እንግሊዘኛ |
| ግዮን | 22 | 21 | ፔዳጎጂክስ | አማርኛ |
| | | | አማርኛ | እንግሊዘኛ |
| ፋሲሎ | 14 | 36 | ፔዳጎጂክስ | አማርኛ |

በጥናቱ ለመታቀፍ ፈቃደኛ ከሆኑ በጣና ሐይቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን ውስጥ አንድ መምህርት 28 ዓመት የአገልግሎት ዘመን ሲኖራቸው ሌላው ተጠኝ መምህር ደግሞ በማስተማር ሙያ 32 ዓመት አገልግለዋል:: ሁለቱ መምህራን በስልጠና መስክ በዓብይ ዘርፍ ፔዳጎጂክስን ሲያጠኑ በንዑስነት ደግሞ አማርኛ ቋንቋን አጥንተዋል:: በግዮን ትምህርት ቤት ደግሞ አንድ መምህር የ22 ዓመት የአገልግሎት ዘመን ሲኖራቸው የሰለጠኑበት መስክ ደግሞ በዋናነት አማርኛ ሲሆን በንዑስ መስክ እንግሊዝኛ ቋንቋን አጥንተዋል:: በዚሁ ትምህርት ቤት 21 ዓመት ያገለገሉ መምህር ሲኖሩ ፔዳጎጂክስን በዓብይነትና አማርኛ ቋንቋን በንዑስነት ያጠኑ ናቸው:: በተጨማሪም በፋሲሎ ትምህርት ቤት 14 ዓመት ያገለገሉ መምህርት ይገኛሉ:: የስልጠና መስካቸውም በዓብይነት አማርኛ ቋንቋ ሲሆን በንዑስነት ደግሞ እንግሊዘኛ ቋንቋ ነው:: የ36 ዓመት የአገልግሎት ዘመን ያላቸው መምህር ደግሞ ፔዳጎጂክስን በዓብይነት ሲያጠኑ አማርኛ ቋንቋን በንዑስነት አጥንተዋል::

ሠንጠረዥ 3:- የተጠኝ ተማሪዎች ብዛት ከዕድሜ፣ ከፆታና ከትምህርት ቤት አኳያ

| ትምህርት ቤት | የተማሪዎች ብዛት | ፆታ | | ዕድሜ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | 13 - 15 | 16 -18 |
| ጣና ሐይቅ | 88 | 44 | 44 | 50 | 38 |
| ግዮን | 88 | 44 | 44 | 42 | 46 |
| ፋሲሎ | 88 | 44 | 44 | 53 | 35 |

በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በተጠኝነት የተመረጡ ተማሪዎች ብዛት 88 ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 44 ሴቶችና 44 ወንድ ተማሪዎች ይገኛሉ:: ከጣና ሐይቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከተመረጡ ተማሪዎች ውስጥ 50 የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከ13 እስከ 15 ሲሆን ቀሪ 35 ደግሞ ከ 16 እስከ 18 የዕድሜ ክልል ውስጥ ይገኛሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ በግዮን ትምህርት ቤት 42 ተማሪዎች ከ13 እስከ 15 የሚሆን ዕድሜ ሲኖራቸው ቀሪ 46ቱ ደግሞ ከ 15 ዕድሜ

በላይ ያላቸው ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ በተጨማሪም በፋሲሎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከተመረጡ ተማሪዎች ውስጥ 53ቱ ዕድሜያቸው 15ና ከዚያ በታች ሲሆን 35 የሚሆኑት ደግሞ ከ16 እስከ 18 የዕድሜ ክልል ውስጥ ይገኛሉ፡፡

## 4.2. የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበር

### 4.2.1. የመምህራን የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት

መምህራን ጥያቄ በሚጠይቁበት ጊዜ ለተማሪዎች የተሳትፎ ዕድል ቢሰጡ በትምህርት መስክ ሁለንተናዊ የሆነ ፋይዳ ያስገኛል፡፡ ይሁን እንጂ እኩል ዕድል ያለመስጠት ሁኔታ ፆታን መሰረት ባደረገው ለሥርዓተ ፆታ ሚና ከሚኖረን አመለካከት ጋር ይያያዛል Ashcroft and Foreman– Peck (1994:145)፡፡ ከዚህ ንድፈ ሃሳብ አንፃር የተጠኝ መምህራኑ የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት በምልከታዎች የታየው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 4፡- መምህራኑ ጥያቄ የጠየቋቸው ተማሪዎች ብዛት

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሦስት | | ምልከታ አራት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 1. | መምህሯ (ሩ) ጥያቄ ጠየቀ | 6 | 13 | 7 | 10 | 5 | 13 | 7 | 12 |

በሠንጠረዥ አራት ከምልከታ አንድ እስከ አራት የመምህራንን የጥያቄ አጠያየቅ የሚመለከቱ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በመምህራን ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ከመስጠት አንፃር ሴት ተማሪዎች ከወንዶች አነስተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=6፡ወ=13፣ሴ=7፡ወ=10፣ሴ=5፡ወ=13 እና ሴ=7፡ወ=12)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ተጠኝ መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ በጥያቄና መልስ ሂደቱ ያሳተፏቸው ተማሪዎች ከምልከታ አምስት እስከ ስምንት ባሉት ላይ ተንፀባርቋል፡፡

ሠንጠረዥ 5፡- የመምህራን ጥያቄ የፆታ ትኩረት

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አምስት | | ምልከታ ስድስት | | ምልከታ ሰባት | | ምልከታ ስምንት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 1. | መምህሯ (ሩ) ጥያቄ ጠየቀ | 9 | 13 | 8 | 12 | 10 | 15 | 7 | 14 |



ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

በአራቱም የምልከታ ምድቦች የሰፈሩ መረጃዎች እንደሚያስገነዝቡት በመስተጋብር ወቅት የወንድ ተማሪዎች ተሳትፎ ጎላ ብሎ መታየቱን ነው፡፡ ይህ በክፍል ውስጥ ከተሰነዘሩ ጥያቄዎች አንፃር ሲታይ የወንዶች ምላሽ ከሴቶች ተማሪዎች በልጦ ተገኝቷል፡፡ አስረጅ፡- (ሴ=9፡ወ=13፣ሴ=8፡ወ=12፣ሴ=10፡ወ=15 እና ሴ=7፡ወ=14)፡፡

የመምህራንን የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት ለመፈተሽ ከተካሄዱ ምልከታዎች ውስጥ የመጨረሻዎቹ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ምልከታዎች የተገኙ ውጤቶች ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 6፡- ጥያቄ የተጠየቁ ተማሪዎች

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ ዘጠኝ | | ምልከታ አስር | | ምልከታ አስራ አንድ | | ምልከታ አስራ ሁለት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 1. | መምህሯ (ሩ) ጥያቄ ጠየቀ | 7 | 10 | 8 | 12 | 3 | 11 | 4 | 13 |

በሠንጠረዥ 6 የተካተቱ የምልከታ ውጤቶች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተካሄዱ መስተጋብሮች ሴት ተማሪዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ ዝቅተኛ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ያመለክታሉ፡፡ ምንም እንኳ በየመማሪያ ክፍሉ እኩል (ተመጣጣኝ) የሆነ የፆታ ተዋጽኦ ቢኖርም ከአራቱ ምልከታዎች እንደተስተዋለው በተለይ በምልከታ 11ና 12 ሴት ተማሪዎች አነስተኛ የሆነ ተሳትፎ አሳይተዋል፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=3፡ወ=11 እና ሴ=4፡ወ=13)፡፡

የመምህራንን የጥያቄ አጠያየቅ በሚመለከት ለመምህራን ቃለ መጠይቅ ተደርጓል፡፡ በቃለ መጠይቁ የተገኘው ውጤት ደግሞ ከስድስቱ ተጠኝ መምህራን አራቱ በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የትምህርት አቀባበል ልዩነት አለመኖሩን ጠቅሰዋል፡፡ በተጨማሪም በመማር ማስተማር ሂደቱ እኩል ጠቃሚ የሆነ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ አመልክተዋል፡፡ ሆኖም ሁለት መምህራን (አንድ ሴትና አንድ ወንድ) በክፍል ውስጥ የወንድ ተማሪዎች ተሳትፎ ልቆ እንደሚታይና ሴት ተማሪዎች ዕውቀት አንሷቸው ሳይሆን ከማህበራዊ ሁኔታዎች አንፃር ያለው ጫና የፈጠረው ተፅዕኖ በመሆኑ በክፍል ተሳትፎ ወንድ ተማሪዎች እንደሚቀድሙ ገልፀዋል፡፡ (የቃል ጥያቄዎችን ዝርዝር አባሪ 5 ን ይመለከቷል)፡፡

መምህራን በክፍል ውስጥ ሁለቱንም ፆታዎች እኩል የሚያስተናግዱ ስለመሆናቸው ለቀረበው ጥያቄ ሁሉም ተጠኝ መምህራን ተማሪዎች በትምህርት ሂደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ እኩል

የተሳትፎ ዕድል በመስጠት ጥያቄ እንደሚጠይቁ ገልፀዋል፡፡ በተለይ አንድ ወንድ መምህር ለመመለስ እጅ ያላወጡ ተማሪዎችን ማሳተፍ እንደሚቻል ሲገልጹ አንዲት ሴት መምህር ደግሞ በሴቶች ላይ ያለውን ባህላዊ ተፅዕኖ መሠረት በማድረግ ሴት ተማሪዎች እንዲሳተፉ እንደሚያነሳሱ ተናግረዋል፡፡

ከላይ ከምልከታ የተገኘው ውጤት እንደሚያስገነዝበው መምህራን ተማሪዎችን በጥያቄ ሂደቱ እንዲሳተፉ የጠየቁት ከሁለቱ ፆታዎች አንፃር ልዩነት እንዳለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከመምህራን የቃል ጥያቄ የተገኘው መረጃ ተማሪዎችን በእኩል እንደሚያሳትፉ ከገለፁት ጋር ይጣረሳል፡፡

የተጠኝ መምህራኑን የጥያቄ አጠያየቅ በሚመለከት ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 7፡- የተማሪዎች የመጠየቅ ተነሳሽነት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6 | በማስተምርባቸው መማሪያ ክፍሎች ያሉ ሴትና ወንድ ተማሪዎች ጥያቄዎችን የመጠየቅ እኩል ተነሳሽነት የላቸውም፡፡ | ሴ | 2 | | - | 1 | |
| | | ወ | 1 | | 2 | - | |

ለሉታዊ ይዘት ካላቸው ጥያቄዎች መካከል በክፍል ውስጥ ሴትና ወንድ ተማሪዎች እኩል ተነሳሽነት እንደሌላቸው ለሚያመለክተው ጥያቄ ከስድስቱ መምህራን ሦስቱ ስምምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ ከእነዚህም ሁለት ሴት እና አንድ ወንድ መምህር ይገኛሉ፡፡ ከቀሪ ሦስት መምህራን መካከል ሁለት ወንድ መምህራን ለመወሰን መቸገራቸውን ሲገልፁ አንዲት ሴት መምህር ደግሞ የማይስማሙ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ መምህራን ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ የሚያነሳሱበት ሁኔታ ስለመኖሩ ለተማሪዎች የቀረቡ የመጠይቅ ውጤቶች ነጥብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 8፡- ለጥያቄዎች የመምህራን አነሳሽነት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 5 | መምህሬ ጥያቄ እንድጠይቅ ያበረታቱኛል፡፡ | ሴ | 22 | 16.7 | 43 | 32.6 | 43 | 32.6 | 24 | 18.2 |
| | | ወ | 8 | 6.1 | 38 | 28.8 | 48 | 36.4 | 38 | 28.8 |

ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ መምህራን ሁልጊዜ የሚያበረታቷቸው መሆኑን 24 (18.2 %) ሴት ተማሪዎች እና 38 (28.8 %) ወንዶች ገልፀዋል:: ሆኖም ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ መምህራን የሚያበረታቷቸው ስለመሆኑ ለቀረበው አወንታዊ የአጠያየቅ ብልሃት ፈፅሞ ሐሰት መሆኑን ከጠቆሙት ውስጥ 22 (16.7 %) ሴቶችና 8 (6.1 %) ወንዶች ይጠቀሳሉ::

የተጠኙ መምህራን የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ካላቸው ተነሳሽነት አንፃር ከተፈተሸው በተጨማሪ መምህራኑ የሚጠይቋቸው የጥያቄ አይነቶችን ለመዳሰስ ተሞክሯል:: ይህን በሚመለከት Sunderland (1992:88-89) መምህራን ተማሪዎቻቸውን በተለያየ መንገድ መያዛቸውን ከሚያመለክቱ ነጥቦች ውስጥ ጥያቄዎችን ማንን ልጠይቅ? ማን ይመልስ? ብሎ መምረጥ፣ የጥያቄዎችን ደረጃ (ክብደት) በማየት የመጠይቅ ሁኔታዎች ተጠቃሽ ናቸው:: ከዚህ ንድፈ ሐሳብ አንፃር ከተጠኙ መምህራን የተገኘው መረጃ የሚከተለውን ይመስላል::

ሠንጠረዥ 9:- በተደጋጋሚ ቀላል ጥያቄዎችን መጠይቅ

<table>
<tr><th rowspan="2">ተ.ቁ</th><th rowspan="2">ጥያቄ</th><th rowspan="2">ፆታ</th><th colspan="5">የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት</th></tr>
<tr><th>5</th><th>4</th><th>3</th><th>2</th><th>1</th></tr>
<tr><td rowspan="2">10</td><td rowspan="2">የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ለማጎልበት በተደጋጋሚ ቀላል ጥያቄዎችን መጠየቅ ተገቢ ነው::</td><td>ሴ</td><td colspan="2">1</td><td>2</td><td colspan="2">-</td></tr>
<tr><td>ወ</td><td colspan="2">1</td><td>1</td><td colspan="2">1</td></tr>
</table>

የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ለማጎልበት በተደጋጋሚ ቀላል ጥያቄዎችን መጠየቅ ተገቢ ስለመሆኑ ለሚጠይቀው አሉታዊ ጥያቄ ሁለት መምህራን (አንድ ወንድና አንድ ሴት) እንደሚስማሙ ገልፀዋል:: ቀሪ ሦስቱ መምህራን ደግሞ በጉዳዩ ላይ ለመወሰን መቸገራቸውን ጠቁመዋል:: ከእነዚህም ሁለት ወንድ እና አንዲት ሴት መምህር ተጠቃሽ ናቸው:: በተጨማሪም አንድ ወንድ መምህር የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ለማጎልበት በተደጋጋሚ ቀላል ጥያቄዎችን መጠየቁን እንደማይስማሙበት ገልፀዋል::

እንዲሁም ቀላል ጥያቄዎችን በሚመለከት ለተማሪዎች ከቀረቡ የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት የተገኙ መረጃዎች ደግሞ እንደሚከተለው ሰፍረዋል::

ሠንጠረዥ 10፡- ቀላል ጥያቄዎችን ብቻ ስለመጠየቅ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 2 | መምህሬ ቀላል ጥያቄዎችን ብቻ ይጠይቁኛል፡፡ | ሴ | 54 | 40.9 | 58 | 43.9 | 16 | 12.1 | 4 | 3 |
| | | ወ | 79 | 58.8 | 46 | 34.8 | 6 | 4.5 | 1 | 0.8 |

ከሠንጠረዥ 10፣ በጥያቄ ተራ ቁጥር 2 ላይ ለሰፈረው አሉታዊ የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት መምህራን አብዛኛውን ጊዜ ቀላል ጥያቄዎችን ብቻ የሚጠይቋቸው መሆኑን ከተጠኝ ተማሪዎች መካከል 16(12.1%) ሴት እና 6(4.5%) ወንድ ተማሪዎች ጠቅሰዋል፡፡ ትግበራው ሁልጊዜ እንደሚፈፀም 4(3%) ሴቶችና 1(0.8%) ወንዶች ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ውጤቱ እንደሚያሳየው በርካታ ወንድ ተማሪዎች 79(59.8%) እና 54(40.9%) ሴት ተማሪዎች መምህራን ቀላል ጥያቄዎችን ብቻ የሚጠይቋቸው መሆኑን ፈፅሞ ሐሰት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከ104 መላሾች መካከል 58(43.9%) ሴቶች እና 46(34.8%) ወንዶች አንዳንድ ጊዜ (አልፎ አልፎ) ቀላል ጥያቄዎችን እንደሚጠየቁ አመላክተዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የመምህራን የጥያቄ አጠያየቅ ከባድ ጥያቄዎችን ከመጠየቅ አንጻር የታየበት ሁኔታ አለ፡፡ በዚህ መሠረት ከተማሪዎች መጠይቅ ውጤት የተገኘው መረጃ በሚከተለው መንገድ ተገልጿል፡፡

ሠንጠረዥ 11፡- ከባድ ጥያቄዎችን ስለመጠየቅ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 12 | መምህሬ ከባድ ጥያቄዎችን ይጠይቁኛል | ሴ | 30 | 22.7 | 65 | 49.2 | 24 | 18.2 | 13 | 9.8 |
| | | ወ | 9 | 6.8 | 58 | 43.9 | 45 | 34.1 | 20 | 15.2 |

መምህራን ከበድ ያሉ ጥያቄዎችን ሁልጊዜ እንደሚጠየቁ 13 (9.8%) ሴቶችና 20(15.2%) ወንዶች ጠቅሰዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠይቋቸው መሆኑን ከገለጹ ተጠኝ ተማሪዎች መካከል 24(18.2%) ሴቶችና 45(34.1%) ወንዶች ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ 39 ከሚሆኑ መላሾች 30(22.7%) ሴቶችና 9(6.8%) ወንድ ተማሪዎች መምህራን ከባድ ጥያቄዎች የሚጠይቋቸው ስለመሆኑ ለሰፈረው አሉታዊ ጥያቄ ሐሰት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ጥያቄዎች አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠየቁ 65 (49.2%) ሴቶችና 58(43. 9%) ወንዶች ጠቁመዋል፡፡

ከጥያቄ ዓይነቶች ባሻገር የመምህራን የአጠያየቅ ብልሃት ስም ጠርቶ ከማሳፈፍ አንፃር ተፈትሿል፡፡ ይህን በሚመለከት Brophy (1993: 64) የመምህራን የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት መምህራን አወንታዊና አሉታዊ ገፅታ ሊኖረው ይችላል፡፡ አወንታዊ የሆነው አጠያየቅ መምህራን ተማሪዎችን በስም ከመጥራታቸው በፊት ጥያቄውን ሲጠይቁ ሲሆን አሉታዊ የጥያቄ አጠያየቅ

ብልሃት የሚባለው ደግሞ መምህራን የሚጠይቁትን ተማሪ ስም ከጠሩ በኋላ ሲጠይቁ እንደሆነ ጠቁሟል፡፡

ከዚህ ንድፈ ሃሳብ አንፃር የተጠኙ መምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ከጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት አንጻር አተገባበሩ በምልከታዎች ተፈትሿል፡፡ ከምልከታ የተገኙ ውጤቶች በሚከተለው መንገድ ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 12፡- ስም ጠርቶ መጠየቅ

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሦስት | | ምልከታ አራት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 9. | መምህሯ (ሩ) ተማሪዎችን በስም እየጠሩ ጠየቁ | 0 | 2 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 |

የምልከታ ቅጹ ውጤት የተጠኙ መምህራን ስም ተኮር የአጠያየቅ ስልት በምልከታ ሦስትና አራት አለመንፀባረቁን ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ በምልከታ አንድና ሁለት መምህራኑ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ስም የሚጠሩ ወንድ ተማሪዎችን እንደሆነ ያሳያል፡፡ አስረጅ፡- (ሴ=0፡ወ=2 እና ሴ=0፡ወ=1)፡፡

በመምህራን ስም ተኮር አጠያየቅ ላይ ያተኮሩ ከምልከታ አምስት እስከ ስምንት የተገኙ መረጃዎች ደግሞ በሠንጠረዥ 13 ውስጥ እንደሚከተለው ሠፍረዋል፡፡

ሠንጠረዥ 13፡- የመምህራን ስም ተኮር አጠያየቅ

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አምስት | | ምልከታ ስድስት | | ምልከታ ሰባት | | ምልከታ ስምንት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 9. | መምህሯ (ሩ) ተማሪዎችን በስም እየጠሩ ጠየቁ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |

ተጠኚ መምህራኑ በአራቱም ምልከታዎች ሴትና ወንድ ተማሪዎችን ጥያቄ የጠየቁበት ሁኔታ ከላይ ከሠንጠረዥ 4 ጀምሮ በቀረቡት ውጤቶች ላይ ተስተውሏል፡፡ ሆኖም በእነዚህ ምልከታዎች በየትኛውም ፆታ የሚገኙ ተማሪዎችን በስም እየጠሩ ከማሳተፍ አንጻር የተሞከረ

ነገር አለመኖሩን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ አስረጅ፡- (ሴ=0፡ ወ=0፣ ሴ=0፡ ወ=0፣ ሴ=0፡ ወ=0 እና ሴ=0፡ ወ=0)፡፡

በተመሣሣይ መልኩ የመምህራን ስም እየጠሩ የመጠየቅ አወንታዊ ብልሃት በመጨረሻዎቹ ምልከታዎች የተገኙ ውጤቶች እንደሚከተለው ተፈትሸዋል፡፡

ሠንጠረዥ 14፡- በስም እየጠሩ ማሳተፍ

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ ዘጠኝ | | ምልከታ አስር | | ምልከታ አስራ አንድ | | ምልከታ አስራ ሁለት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 9. | መምህሯ (ሩ) ተማሪዎችን በስም እየጠሩ ጠየቁ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |

ከምልከታ ዘጠኝ እስከ 12 የተካሄዱ መረጃዎች እንደሚያስገነዝቡት በክፍል ውስጥ መምህራን ተማሪዎችን በስም እየጠሩ እንዳላሳተፉ ያሳያሉ፡፡አስረጅ፡(ሴ=0፡ወ=0፣ሴ=0፡ወ=0፣ ሴ=0፡ወ=0 እና ሴ=0፡ወ=0)፡፡

ከምልከታዎቹ ውጤት በተጨማሪ መምህራን የተማሪዎችን ስም እየጠሩ ከማሳተፍ አንፃር የተፈተሹ የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት በሚከተለው ሁኔታ ተካቷል፡፡

ሠንጠረዥ 15፡- ከስም ጥሪ በፊት ጥያቄ ማቅረብ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 7 | ስም ጠርቶ ጥያቄ ከማስከተል ይልቅ ጥያቄዎችን ከጠየቁ በኋላ ተማሪዎችን በስም እየጠሩ ማሳተፍ ተገቢ ነው፡፡ | ሴ | 2 | | - | 1 | |
| | | ወ | 1 | | 1 | 1 | |

በሠንጠረዥ 15 ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ የመረጃ ውጤቶች እንደሚያስገነዝቡት በተራ ቁጥር 7 ላይ ለቀረበው አወንታዊ የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት ሦስት መምህራን መስማማታቸውን ገልፀዋል፡፡ ከእነዚህም ሁለት ሴቶች እና አንድ ወንድ መምህር ይገኛሉ፡፡ የተማሪዎችን ስም ከጠሩ በኋላ ጥያቄዎችን መጠየቅ ተገቢ ስለመሆኑ አንድ ወንድ መምህር ለመወሰን እንደተቸገሩ አመላክተዋል፡፡ ከተጠኙ መምህራን መካከል አንዲት ሴትና አንድ ወንድ በጉዳዩ ላይ እንደማይስማሙ ጠቁመዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መምህራን የተማሪዎችን ስም እየጠሩ የሚያሳትፉ ስለመሆኑ ለማወቅ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች አሉ፡፡ እነዚህ ውጤቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 16፡- የመምህራን ስም አጠራር

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 3 | መምህሬ በክፍል ውስጥ ጥያቄ ሲጠይቁኝ ስሜን በመጥራት ነው፡፡ | ሴ | 66 | 50 | 57 | 43.2 | 7 | 5.3 | 2 | 1.5 |
| | | ወ | 31 | 23.5 | 59 | 45 | 38 | 29 | 4 | 3 |

በሠንጠረዡ የተካተቱ የመረጃ ውጤቶች እንደሚያስገነዝቡት መምህራን የተማሪዎችን ስም እየጠሩ የሚያሳትፉ ስለመሆኑ ለቀረበው አወንታዊ ጥያቄ ከ97 ተማሪዎች ውስጥ 66 (50 %) ሴቶችና 31 (23.5 %) ወንዶች ስማቸው እንደማይጠራ ገልፀዋል፡፡ ስም የመጥራቱን ጉዳይ አብዛኛውን ጊዜ መምህራን እንደሚተገብሩ ከገለፁት ውስጥ 7 (5.3 %) ሴቶችና 38 (29 %) ወንድ ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም ሁል ጊዜ መሆኑን 2(1.5%) ሴቶችና 4(3%) ወንዶች ጠቅሰዋል፡፡

በተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ላይ መምህራን የተማሪዎችን ስም በመጥራት ከማሳተፍ አኳያ የቀረበ ጥያቄ በሠንጠረዥ 17 ሥር ውጤቱ እንደሚከተለው ይገኛል፡፡

ሠንጠረዥ 17፡- ስም ከጠሩ በኋላ ጥያቄ መጠየቅ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 9 | መምህሬ ጥያቄ የሚጠይቁት ስሜን ከጠሩ በኋላ ነው፡፡ | ሴ | 42 | 31.8 | 47 | 35.6 | 29 | 22 | 14 | 10.6 |
| | | ወ | 63 | 47.7 | 52 | 39.4 | 7 | 5.3 | 10 | 7.6 |

በተራ ቁጥር 9 ላይ ለሰፈረው አሉታዊ ጥያቄ 36 ከሚሆኑ መላሾች ውስጥ 29(22%) ሴት ተማሪዎች እና 7(5.3%) ወንዶች መምህራን ስማቸውን ከጠሩ በኋላ አብዛኛውን ጊዜ ጥያቄ የሚጠይቋቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም 14(10.6%) ሴቶችና 10 (7.6%) ወንዶች ሁል ጊዜ እንደሚተገበር አስገንዝበዋል፡፡ የተማሪዎች ውጤት እንደሚያሳየው ጥያቄ የሚጠይቁት ስም ከተጠሩ በኋላ የመሆኑን ጉዳይ 42(31.8%) ሴቶችና 63 (47.7%) ወንዶች እንደማይስማሙ ጠቁመዋል፡፡ ትግበራው አንዳንድ ጊዜ መሆኑን 47 (35.6%) ሴቶችና 52 (39.4%) ወንዶች ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም የመምህራኑን የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት ስም ከመጥራት አንፃር ሲፈተሽ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ አለ፡፡ ይህ መረጃ ደግሞ በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

ሠራጠረዥ 18፡- የመምህራን ከስም በፊት የጥያቄ አጠያየቅ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 19 | መምህሬ ጥያቄውን ካቀረቡ በኋላ ስሜን እየጠሩ ያሳትፉኛል፡፡ | ሴ | 47 | 35.6 | 44 | 33.3 | 22 | 16.7 | 19 | 14.4 |
| | | ወ | 21 | 15.9 | 57 | 43.2 | 34 | 25.8 | 20 | 15.2 |

መምህራን የተማሪዎችን ስም ስማቸውን ከመጥራታቸው በፊት ጥያቄውን የሚያቀርቡ ስለመሆኑ ለቀረበላቸው አወንታዊ ጥያቄ 47 (35.6%) ሴት ተማሪዎች እና 21 (15.9 %) ወንድ ተማሪዎች ፈፅሞ ሐሰት እንደሆነ አመላክተዋል፡፡ ይሁን እንጂ 44(33.3%) ሴቶችና 57 (43.2%) ወንዶች አንዳንዴ እንደሚሳተፉ ገልጸዋል፡፡ ከጥያቄ በኋላ ስም እየጠሩ ማሳተፍን በሚመለከት ሁልጊዜ የመምህራን ትግበራ መኖሩን የገለፁት 19 (14.4 %) ሴቶችና 20 (15.2 %) ወንዶች ናቸው፡፡ ትግበራው አብዛኛውን ጊዜ እንደሚፈጸም 22 (16.7%) ሴቶችና 34 (25.8%) ወንዶች ጠቁመዋል፡፡

በአጠቃላይ የመምህራንን የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት ለመፈተሽ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች የያዙትን ውጤት በቲ- ስሌት ለፈተሽ ተሞክሯል፡፡ ከስታትስቲክስ የተገኘው ውጤት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሠንጠረዥ 19፡- የጥያቄ አጠያየቅ መረጃ ከቲ-ስሌት አንፃር

| ተጠኝዎች | | አማካይ (Mean) | ቲ-ስሌት | p | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | ፆታ | | | | |
| 132 | ወ | 14.1136 | 3.483 | < 0.01 | አለው |
| 132 | ሴ | 12.9773 | | | |

የስድስቱን ተጠኝ መምህራን የክፍል ውስጥ የሥርዓተ ፆታ አተገባበር ለመፈተሽ ከወንድና ሴት ተማሪዎች የተገኘ የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት በሠንጠረዥ 19 ውስጥ ሰፍሯል፡፡ ከሠንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው 132 ተጠኝ ወንድ ተማሪዎች በመምህራን የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት ላይ 14.1136 የሆነ አማካይ ውጤት ሲያመጡ ቀሪ 132 ሴት ተማሪዎች ደግሞ 12.9773 አማካይ ነጥብ አስመዝግበዋል፡፡ ከዚህ መረጃ አንጻር የወንድና የሴት ተማሪዎች አማካይ ውጤት በቲ-ስሌት 3.483 የሆነ ነጥብ አስገኝቷል፡፡ ይህ ነጥብ ደግሞ $P<0.01$ የሆነ ውጤት ተገኝቷል፡፡ በዚህም ተጠኝ መምህራን ከሥርዓተ ፆታ አተገባበር አንፃር የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃታቸው በወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አረጋግጧል፡፡

ከላይ በተለያዩ ሠንጠረዥች የተገኙ የትንተና ውጤቶች እንደሚያስገነዝቡት በክፍል ውስጥ መስተጋብር ያልተመጣጠነ የሥርዓተ ፆታ አያያዝ መንፀባረቁን ነው፡፡ ያለመመጣጠኑ ሁኔታ

ደግሞ ጥያቄ እንዲመልሱ ከማሳተፍና ስም እየጠሩ ከመጠየቅ አንፃር ልቆ ተስተውሏል።ይህ ውጤት እነ Eckert and Mc Connell (2003:116) እና Cruickshank and et at (1995:34) በመማሪያ ክፍል ውስጥ ወንድ ተማሪዎች ዘወትር የተሳትፎ እድል ስለሚያገኙ የመናገር እድል ይፈጠርላቸዋል:: በአንፃሩ ሴት ተማሪዎች የንግግር ተሳትፏቸው አነስተኛ በመሆኑ በመስተጋብር ሂደቱ የወንድ ተማሪዎች ንግግር ከሴቶች ልቆ ተገኝቷል ከሚለው የጥናት ውጤት ጋር ይደጋገፋል:: በተመሳሳይ መልኩ እነ Elliott and et al (2000:146) እና Sunderland (1992: 88 – 89) ሲገልጹ በክፍል ውስጥ መስተጋብር ወንድ ተማሪዎች በተደጋጋሚ ከሴቶች የበለጠ የመምህራንን ትኩረት ስለሚያገኙ በበርካታ ጥያቄዎች ላይ ይሳተፋሉ:: በአውስትራሊያ እና ኒውዘርላንድ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን ለወንድ ተማሪዎች በርካታ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ እድል መስጠታቸውን ከሚያወሳው የጥናት ውጤት ጋር ውጤቱ ይደጋገፋል::

በሌላ በኩል ደግሞ Alexander (1997:77) የመምህራን ያታን መሠረት ያደረገ ልማዳዊ አድሏዊ ባህርያት በተለያዩ መንገዶች ሊገለጹ ይችላሉ:: ከእነዚህ ውስጥ መምህራን ለሴትና ወንድ ተማሪዎች የሚጠይቁት የጥያቄ ዓይነት ተጠቃሽ ነው:: ከዚህ የተነሳ መምህራን በርካታ ቀላል ጥያቄዎችን ሴት ተማሪዎችን እንደሚጠይቁ የሚያወሳውን ጽንሰ ሐሳብ አንፃራዊ በሆነ መልኩ እንደሚተገብሩ ከተጠኙ መምህራን መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች አመላክተዋል::ሆኖም ግን ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ ተጠኝ መምህራኑ ከወንዶች ተማሪዎች አኳያ ሲታይ በርከት ያሉ ቀላል ጥያቄዎች ለሴት ተማሪዎች እና ከበድ ያሉ ጥያቄዎች ደግሞ ለወንዶች እንደተሰጡ መረጃዎች በማስገንዘባቸው ከመጠይቁ ውጤት ጋር ይዛመዳል::

ከተለያዩ ሠንጠረገሮች ከተገኙ ውጤቶች በመነሳት ከአወንታዊ ጥያቄ አጠያየቅ መረጃ ውጤት አንፃር በመምህራን ጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት ላይ ህፀፆች መኖራቸውን ያሳያል:: ይህ ችግር ደግሞ በሥርዓተ ፆታ አተገባበራቸው ላይ መንፀባረቁን ያስገነዝባል::: ተጠኝ መምህራኑ ተማሪዎችን በስም እየጠሩ የመጠየቅ ልምዳቸው አነስተኛ እንደሆነ ተስተውሏል። በተለይ ስም ያለመጥራቱ ሁኔታ አብዛኛውን ጊዜ ወደ ሴቶች አመዝኗል:: በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎችን ጥያቄ እንዲጠይቁ የሚያበረታቱ መሆኑ ቢታይም በርከት ያሉ ሴት ተማሪዎች ግን ከመምህራን ማበረታቻ እንደማያገኙ ገልፀዋል:: በተመሣሣይ ሁኔታ መምህራን ሁልጊዜ ጥያቄዎችን ካቀረቡ በኋላ የተማሪዎችን ስም በመጥራት ከማሳተፍ አንፃር ያላቸው ትግበራ አነስተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል:: እነ Hatchell (1998:388)፣ Brophy (1993:64) እና Bennett (1982:88) መምህራን ተማሪዎችን ስም እየጠሩ በሚያሳትፉበት ጊዜ ተማሪዎች ለበለጠ ውጤትና ተሳትፎ እንደሚበረታቱ ካሰፈሩት ውጤት ጋር አይገናኝም:: በተጨማሪም

ከአወንታዊ ጥያቄ አጠያየቅ ንድፈ ሐሣብ አንፃር የመምህራን ስም እየጠሩ የመጠየቅ ትግበራቸው የተዳከመ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 4.2.2. የመምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ

መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለተማሪዎች አሉታዊ፣ አወንታዊ እና ምጋቤ ምላሾችን የማይሰጡበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ ይህን በሚመለከት እነ Bukatko and Daehler (1992: 524) እና Rhona and etal (1982: 678) መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ መለያየት (ለተወሰኑት ሙገሳ ለሌሎች ትችት መሆኑ) ተማሪዎች ስለራሳቸው ባላቸው ግምትና አጠቃላይ በትምህርት ችሎታቸው ላይ ተጽዕኖ ያደርሳል፡፡

ከዚህ ንድፈ ሐሳብ አንፃር በመምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ላይ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 20፡- አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሦስት | | ምልከታ አራት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 6. | መምህሯ(ሩ)ለተማሪዎች መልስ አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ ሰነዘሩ | 2 | 6 | 1 | 6 | 2 | 7 | 3 | 10 |

ከሠንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው አወንታዊ ምጋቤ ምላሾች በሁለቱም ፆታ ለሚገኙ ተማሪዎች መሰጠታቸውን ከአራቱ ምልከታዎች የተገኙ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይሁን እንጂ የመምህራን አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ከተማሪዎች ፆታ አንፃር ለወንዶች የተሰነዘሩት አመዝነው ታይተዋል፡፡ አስረጅ፡- (ሴ=2፡ወ=6፣ሴ=1፡ወ=6፣ሴ=2፡ወ=7 እና ሴ=3፡ወ=10)፡፡

የተጠኙ መምህራኑን የአወንታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በሚመለከት ከምልከታ አምስት እስከ ስምንት የተገኙ ውጤቶች ደግሞ በቀጣዩ ሠንጠረዥ ውስጥ ተካተዋል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ሠንጠረዥ 21፦ ለተማሪዎች መልስ የተሰነዘሩ አወንታዊ ምጋቤ ምላሾች

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አምስት | | ምልከታ ስድስት | | ምልከታ ሰባት | | ምልከታ ስምንት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 6. | መምህሯ(ሩ)ለተማሪዎች መልስ አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ ሰነዘሩ | 3 | 6 | 3 | 5 | 4 | 10 | 2 | 9 |

የተዘረዘሩት የምልከታ ውጤቶች እንደሚያስገነዝቡት በአራቱም ምልከታዎች ተጠኝ መምህራን ለተማሪዎቻቸው አወንታዊ ምጋቤ ምለሾችን እንደለገሱ ያሳያሉ። የአወንታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጡ ደግሞ ከፆታ ፆታ ልዩነት መኖሩን የመረጃ ውጤቶች ያመላክታሉ። ይኸውም ለሴት ተማሪዎች የተሰነዘሩት ከወንዶች አንጻር መጠነኛ ሆነው ተገኝተዋል። አስረጅ፦ (ሴ=3፡ወ=6፣ሴ=3፡ወ=5 ሴ=4፡ወ=10 እና ሴ=2፡ወ=9)።

ከዚህ በማስከተል የተካሄዱ የምልከታ መረጃዎች በመምህራን አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ላይ የያዙት ውጤት በሠንጠረዥ 22 ላይ ተካቷል።

ሠንጠረዥ 22፦ የመምህራን አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ ዘጠኝ | | ምልከታ አስር | | ምልከታ አስራ አንድ | | ምልከታ አስራ ሁለት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 6. | መምህሯ(ሩ)ለተማሪዎች መልስ አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ ሰነዘሩ | 5 | 7 | 4 | 7 | 1 | 5 | 1 | 6 |

በተራ ቁጥር ስድስት ለሰፈረው የመምህራን አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በምልከታ 9 ና 10 አንፃራዊ በሆነ መቀራረብ በወንድ ተማሪዎች ላይ ብልጫ አሳይቷል። አስረጅ፦ (ሴ=5፡ወ=7፣እና ሴ=4፡ወ=7)። በሌላ በኩል ደግሞ በቀሩት ሁለት ምልከታዎች ላይ ለሴት ተማሪዎች የተሰጠው አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል።አስረጅ፦(ሴ=1፡ወ=5 እና ሴ=1፡ወ=6)።

እንዲሁም የመምህራኑን አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ ከተማሪዎች ክፍት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በሚከተለው መልክ ተካቷል።

መምህሯ(ሩ) አበረታች አስተያየቶችን ሲሰነዝሩ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማቸው የሚጠይቅ ጥያቄ ለተማሪዎች ቀርቧል:: ለቀረበው ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በጣም እንደሚደሰቱ፣ ለበለጠ ሥራ እንደሚተጉ፣ ጥያቄ ለመጠየቅ እንደሚነሳሱ፣ በተረጋጋ መንፈስ መማር እንደሚያስችላቸው፣ የተፎካካሪነት ስሜት እንደሚሰማቸው፣ በራስ የመተማመን ስሜት እንደሚያድርባቸው ወዘተ የሚመለከቱ ምላሾችን በመጠይቁ ላይ አስፍረዋል::

በሌላ በኩል ደግሞ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያስገነዝቡት ከመምህራን የሚሠነዘሩ ምጋቤ ምላሾችን በተመለከተ ለቀረበው የቃል ጥያቄ ስድስቱም መምህራን ለተማሪዎቻቸው በእኩል ወይም ያለ ፆታዊ አድሎ የተሳትፎ ዕድል እንደሚሰጡ ጠቁመዋል:: የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ ደግሞ አድሎአዊ ቢሆን ተፅዕኖ ሊያመጣ እንደሚችል ገልፀዋል:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንዲት መምህር አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች ተፅዕኗቸው ሰፊ እንደሆነ አስገንዝበዋል:: ይኸውም አንድ ተማሪ "አንተ ተው"፣ "ሌላ"፣ "ተሳስተሃል" የሚባል ከሆነ ይሸማቀቃል:: ይሁን እንጂ ምጋቤ ምላሹ አወንታዊ ለምሳሌ "ጥሩ ሞክረሃል" ወዘተ የሚል ዓይነት ከሆነ ለነገ ሊበረታታ እንደሚችል ገልፀዋል:: ከተጠኝ መምህራን መካከል አንድ ወንድ መምህር ደግሞ ተማሪዎችን ማበረታታት ተገቢ እንደሆነና በተለይ ሴት ተማሪዎችን ትኩረት በመስጠት ማበረታታት ተገቢ መሆኑን የበኩላቸውን ሃሳብ ሰንዝረዋል::

ከቃለ መጠይቅ በተጨማሪ የመምህራንን አወንታዊ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ በጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች አሉ:: እነዚህ መረጃዎች ደግሞ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ውስጥ ውጤታቸው ተካቷል::

ሠንጠረዥ 23፡- የተሳሳተ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች የሚሰጥ ምጋቤ ምላሽ

<table>
<tr><th rowspan="2">ተ.ቁ</th><th rowspan="2">ጥያቄ</th><th rowspan="2">ፆታ</th><th colspan="5">የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት</th></tr>
<tr><th>5</th><th>4</th><th>3</th><th>2</th><th>1</th></tr>
<tr><td rowspan="2">1</td><td rowspan="2">የተሳሳተ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች አበረታች ምጋቤ ምላሾችን እሰጣለሁ::</td><td>ሴ</td><td colspan="2">2</td><td>-</td><td colspan="2">1</td></tr>
<tr><td>ወ</td><td colspan="2">3</td><td>-</td><td colspan="2">-</td></tr>
</table>

የተጠኝ መምህራኑን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በሚመለከት በተራ ቁጥር 1 የተሳሳተ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች አበረታች ምጋቤ ምላሽ አሰጣጣቸውን ለማወቅ ለሠፈረው አወንታዊ ጥያቄ ከስድስቱ ተጠኝ መምህራን መካከል አምስቱ በጉዳዩ ላይ እንደሚስማሙ ገልፀዋል:: ከእነዚህ ተጠኝ መምህራን መካከል ሁለት ሴቶች እና ሦስት ወንዶች ይገኛሉ:: ቀሪ አንዲት ሴት መምህር ደግሞ በጉዳዩ ላይ እንደማይስማሙ ጠቁመዋል::

በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች በሚሰጡት የተሳሳተ መልስ የመምህራኑን ምላሽ በሚመለከት የሰፈሩት የመጠይቅ ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው።

ሠንጠረዥ 24፡- ለተማሪዎች የተሳሳተ መልስ የሚሰጥ የመምህራን ትችት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 7 | መምህሬ ጥያቄ በምመልስበት ጊዜ ስሳሳት ይተቹኛል (ይገሰጹኛል)። | ሴ | 38 | 28.8 | 35 | 26.5 | 43 | 32.6 | 16 | 12.1 |
| | | ወ | 64 | 48.5 | 40 | 30.3 | 15 | 11.4 | 13 | 9.8 |

በተራ ቁጥር 7 ላይ የሠፈረው አሉታዊ መረጃ እንደሚያሳየው 16 (12.1%) ሴቶችና 13 (9.8%) ወንዶች ሁልጊዜ እንደሚተቹ ጠቁመዋል። 43 (32.6%) ሴት ተማሪዎች እና 15 (11.4%) ወንዶች አብዛኛውን ጊዜ መልስ በሚመልሱበት ወቅት ቢሳሳቱ መምህራን ትችት (ተግሳጽ) እንደሚሰነዝሩባቸው ያሳያሉ። ሆኖም ግን መልስ በሚመልሱበት ጊዜ ቢሳሳቱ መምህራን ትችት እንደማይሰነዝሩባቸው ከገለጹ ተማሪዎች ውስጥ 64 (48.5%) ወንዶችና 38 (28.8%) ሴት ተማሪዎች ይገኛሉ። ይሁን እንጂ 35 (26.5%) ሴቶችና 40 (30.3%) ወንዶች አንዳንድ ጊዜ እንደሚተገበር ገልጸዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ለተማሪዎች የቀረቡ ክፍት የጽሑፍ መጠይቆች አሉ (አባሪ ሦስትን ይመለከቷል)። ከጥያቄዎቹ መካከል በመምህርሽ(ህ) ወይም በሌላ ተማሪ ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ እንድትሰጪ(ጥ) ተጠይቀሽ(ህ) የተሳሳተ ምላሽ ብትሰጪ(ጥ) መምህርሽ(ህ) ምን ሊያደርጉ ይችላሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ? የሚል ይገኝበታል። ለዚህ ጥያቄ ከሴት ተማሪዎች የተገኙ አብዛኛዎቹ ምላሾች "አስበሽ ተናገሪ"፣ "ደደብ"፣ "እስከመቼ ያልፍልሻል"፣ "ትዳር የለሽ"፣ "አትንቀዥቀዢ"፣ "ደህና ነው"፣ "ትክክል አይደለም"፣ "ወሬኛ"፣ "አይ የአንቺ ነገር"፣ "እሽ እኔ ልመልሰው"፣ "ብዙ ጊዜ ይቆጣሉ"፣ "ይስቃሉ" የሚሉ ናቸው። ከወንድ ተማሪዎች ከተገኙ አብዛኛዎቹ ምላሾች መካከል "እረባሽ"፣ "ተረጋጋ"፣ "አንተም ተሳስተሃል"፣ "ጥሩ ነው"፣ "ከክፍል ያስወጣሉ"፣ "ደግመው ይጠይቃሉ"፣ "ስህተቴን እንዳስተካክል ያደርጋሉ" ወዘተ የሚሉት ይጠቀሳሉ።

ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ያለውን የመምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ከሚመለከተው በተጨማሪ ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልጹ የመምህራን ማበረታቻን በሚመለከት ከተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ አለ።

ሠንጠረዥ 25፡- ሐሳብን በነፃነት መግለጽ ስለመቻል

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 1 | በክፍል ውስጥ ሐሣቤን በነፃነት እንድገልጽ በመምህሬ እበረታታለሁ:: | ሴ | 15 | 11.4 | 62 | 47 | 38 | 28.8 | 17 | 12.9 |
| | | ወ | 3 | 23 | 30 | 22.7 | 59 | 44.7 | 40 | 30.3 |

ከላይ ከሠንጠረዡ የተገኙ የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች እንደሚያስገነዝቡት ከሁለቱ ፆታዎች መካከል ወንድ 40(30.3%) እና ሴት 17 (12.9%) የሚሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸው ሁልጊዜ በክፍል ውስጥ ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልጹ የሚያበረታቷቸው መሆኑን ጠቁመዋል:: ይህ አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጣቸው መሆኑን ከገለፁ ተማሪዎች መካከል 38 (28.8%) ሴቶች እና 59 (44.7%) ወንዶች ይገኛሉ:: ሌሎች ቀሪ 62 (47%) ሴቶች እና 30 (22.7%) ወንድ ተማሪዎች መምህራን ማበረታቻውን አንዳንድ ጊዜ (አልፎ አልፎ) እንደሚተገብሩ ገልፀዋል:: ሆኖም ሐሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ የሚደረገው የመምህራን ማበረታቻ ፈፅሞ ሐሰት መሆኑን ከጠቆሙት መካከል 15 (11.4%) ሴት እና 3 (2.3%) ወንድ ተማሪዎች ይገኛሉ::

ተማሪዎች ጥሩ በሚሠሩበት ጊዜ የመምህራንን ማበረታቻ በሚመለከት በሠንጠረዥ 26 ከተማሪዎች መጠይቅ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል::

ሠንጠረዥ 26፡- የመምህራን ማበረታቻ (ሙገሳ)

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 11 | ጥሩ ሥሠራ መምህሬ የማበረታቻ (ሙገሳ) ምጋቤ ምላሽ ይሰጡኛል:: | ሴ | 23 | 17.4 | 43 | 32.6 | 36 | 27.3 | 30 | 22.7 |
| | | ወ | 6 | 4.5 | 16 | 12.1 | 58 | 43.9 | 52 | 39.4 |

በተራ ቁጥር 11 ላይ ለሠፈረው አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ጥያቄ ተማሪዎች ጥሩ ሥራ በሚተገብሩበት ጊዜ መምህራን ማበረታቻ (ሙገሳ) የሚሰጧቸው አብዛኛውን ጊዜ መሆኑን 52 (39.4%) ወንዶችና 30 (22.7%) ሴት ተማሪዎች ገልፀዋል:: ለጥሩ ሥራዎቻቸው የመምህራን ማበረታቻ (ሙገሳ) አልፎ አልፎ (አንዳንድ ጊዜ) መሆኑን ከጠቆሙ ተማሪዎች ውስጥ 43 (32.6%) ሴቶች እና 16 (12.1%) ወንድ ተማሪዎች ይገኛሉ::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመምህራን አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ ከተማሪዎች ባህርይ አንፃር የታየበት ሁኔታ መኖሩን የሚዳስስ መረጃ በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 27፡- ለጥሩ ባህሪያት የመምህራን ማበረታቻ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 15 | መምህሬ ጥሩ ባህርይ ሳሳይ አበረታች ምጋቤ ምላሽ ይለግሱኛል። | ሴ | 4 | 3 | 22 | 16.7 | 41 | 31.1 | 65 | 49.2 |
| | | ወ | 13 | 9.8 | 37 | 28 | 42 | 31.8 | 40 | 30.3 |

ተማሪዎች ጥሩ ባህርይ በሚያሳዩበት ወቅት የመምህራቸው አበረታች ምጋቤ ምላሽ ምን ገፅታ እንዳለው እንዲገልጹ ለሰፈረላቸው ጥያቄ 65 (49.2%) ሴት ተማሪዎች እና 40 (30.3%) ወንዶች አብዛኛውን ጊዜ ትክክል መሆኑን ጠቁመዋል። ጥሩ ባህርይ ሲያሳዩ የመምህራን አበረታች ምጋቤ ምላሽ እንደማይሰጣቸው ደግሞ 4 (3%) ሴቶች እና 13 (9.8%) ወንዶች ገልፀዋል።

የተማሪዎችን ባህርይ ከተሳታፊቸው አንፃር ያለውን ሁኔታ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በሚከተለው መንገድ ሰፍሯል።

ሠንጠረዥ 28፡- ከተሳታፊ ይልቅ ለጥሩ በህርይ የሚሰጥ ማበረታቻ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4 | ሴት ተማሪዎችን የማበረታታው ከትምህርት ተሳትፏቸው ይልቅ ጥሩ ባህርይ ሲያሳዩ ነው። | ሴ | - | | - | 3 | |
| | | ወ | - | | 1 | 2 | |

በሌላ በኩል ደግሞ በተራ ቁጥር 4 ለቀረበው አሉታዊ ይዘት ላለው የምጋቤ ምላሽ ጥያቄ አምስቱ መምህራን ሴት ተማሪዎችን ከተሳትፏቸው ይልቅ ጥሩ ባህርይ ሲያሳዩ እንደሚያበረታቱ ገልፀዋል። ከእነዚህ ውስጥ ሦስት ሴት እና ሁለት ወንድ መምህራን ይገኛሉ። ሌላ ቀሪ አንድ ወንድ መምህር ደግሞ በጉዳዩ ላይ ለመወሰን መቸገራቸውን ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከመምህራን በምጋቤ ምላሽ መልክ የሚሰነዘሩ ማበረታቻዎች በክፍል ውስጥ መስጠት አለመስጠቱን በተመለከተ ከሴትና ወንድ ተማሪዎች የተገኘው ውጤት የሚከተለው ነው።

ሠንጠረዥ 29፡- የመምህራን አስተያየት በክፍል ውስጥ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 13 | መምህሩ አስተያየቶችን በክፍል ውስጥ ይነግሩኛል፡፡ | ሴ | 46 | 34.8 | 52 | 39.4 | 22 | 16.7 | 12 | 9.1 |
| | | ወ | 16 | 12.1 | 40 | 30.3 | 50 | 37.9 | 26 | 19.7 |

በመምህራን አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ላይ ተመሥርቶ ለቀረበው ጥያቄ 46(34.8%) ሴት ተማሪዎችና 16(12.1%) ወንዶች መምህራን አስተያየቶችን በመማሪያ ክፍል ውስጥ እንደማይገልፁላቸው አመላክተዋል፡፡ የመምህራን አስተያየት አብዛኛውን ጊዜ በክፍል ውስጥ እንደሚሰጣቸው ከጠቆሙት ውስጥ 50(37.9%) ወንድ ተማሪዎችና 22(16.7%)ሴቶች ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተለየ መንገድ የመምህራን አስተያየቶች ከክፍል ውጭ (በግል) የመስንዘሩ ሁኔታ ምን ገፅታ እንዳለው የተማሪዎች መጠይቅ ውጤት ያስገኘው ውጤት በሠንጠረዥ 30 ውስጥ ተካቷል፡፡

ሠንጠረዥ 30፡- በግል ተማሪዎችን በመጥራት አስተያየት መስጠት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 4 | መምህሩ አስተያየታቸውን በግል ጠርተው ይነግሩኛል፡፡ | ሴ | 44 | 33.3 | 51 | 38.6 | 26 | 19.7 | 14 | 10.6 |
| | | ወ | 83 | 62.9 | 35 | 26.5 | 10 | 7.6 | 4 | 3 |

የመምህራንን አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ ከተማሪዎች መጠይቅ የተሰበሰቡ የመረጃ ውጤቶች መምህራን አብዛኛውን ጊዜ ለሴት ተማሪዎች አስተያየቶችን በግል ጠርተው እንደሚናገሩ ያመለክታሉ፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=26(19.7%):ወ=10(7.6))፡፡ይህ ጉዳይ ፊፅሞ ሐሰት መሆኑን ከጠቆሙ ተማሪዎች ውስጥ 44(33.3%) ሴቶችና 83(62.9%) ወንድ ተማሪዎች ይጠቀሳሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከመምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ጋር የታየው ምንም ምጋቤ ምላሽ ያለመስጠት ሁኔታ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት በምልከታዎች የተስተዋለው ውጤት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሠንጠረዥ 31፡- ምንም ምጋቤ ምላሽ አለመስጠት

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሦስት | | ምልከታ አራት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 7. | መምህሯ (ሩ) ለተማሪዎች መልስ ምንም ምጋቤ ምላሽ አልሰጡም | 3 | 5 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 |

ከምልከታዎች መገንዘብ እንደሚቻለው መምህራን ምንም ምጋቤ ምላሽ ያለመስጠት ሁኔታ በሁለቱም ፆታ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ መንፀባረቁን ውጤቱ ያረጋግጣል፡፡ በምልከታ ሁለት ለሴትና ለወንድ ተማሪዎች በእኩል ደረጃ ምንም ምጋቤ ምላሽ እንዳልተሰጡ ታይቷል፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=3፡ወ=3)፡፡ ይህ ሁኔታ በቀሪ ሦስት ምልከታዎች ላይ ከፆታ አንጻር ልዩነት ተስተውሏል፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=3፡ወ=5፣ሴ=1፡ወ=3 እና ሴ=3፡ወ=1)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በሌሎች ምልከታዎች የተገኙ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ውጤቶች እንደሚከተለው ተገልፀዋል፡፡

ሠንጠረዥ 32፡- ለተማሪዎች መልስ የመምህራን ምጋቤ ምላሽ አለመኖር

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አምስት | | ምልከታ ስድስት | | ምልከታ ሰባት | | ምልከታ ስምንት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 7. | መምህሯ(ሩ)ለተማሪዎች መልስ ምንም ምጋቤ ምላሽ አልሰጡም | 4 | 6 | 4 | 7 | 4 | 5 | 3 | 4 |

የመምህራኑ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ውጤቶች እንደሚያሳዩት በአራቱም ምልከታዎች ምንም ምጋቤ ምላሽ ያልሰጡበት ሁኔታ መኖሩን ይጠቁማል፡፡ ምጋቤ ምላሽ ያለመስጠቱ ጉዳይ በሁለቱ ፆታ ተማሪዎች ላይ የተንፀባረቀ ቢሆንም የልዩነቱ ሁኔታ ደግሞ ከአንዱ ፆታ ወደ ሌላ ከፍተት መኖሩን ያመላክታሉ፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=4፡ወ=6፣ሴ=4፡ወ=7፣ ሴ=4፡ወ=5 እና ሴ=3፡ወ=4)፡፡

በተጨማሪም በመጨረሻዎቹ የምልከታ ምድቦች የተገኙ የመረጃ ውጤቶች በሠንጠረዥ 33 ላይ ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 33:- ምጋቤ ምላሽ ያልሰጡ ተማሪዎች

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አምስት | | ምልከታ ስድስት | | ምልከታ ሰባት | | ምልከታ ስምንት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 7. | መምህሯ(ሩ)ለተማሪዎች መልስ ምንም ምጋቤ ምላሽ አልሰጡም | 2 | 2 | 4 | 4 | 1 | 5 | 1 | 6 |

የምልከታ መረጃ ውጤቶች ተጠኚ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ምጋቤ ምላሽ ያልሰጡበት ሁኔታ መኖሩን ያሳያሉ። በመሆኑም በምልከታ ዘጠኝና አስር መምህራን ለሁለቱም ፆታዎች ምንም ምጋቤ ምላሽ አለመስጠታቸውን የመረጃዎች ተመሳሳይ ውጤት ያመላክታል። መምህራን ምንም ምጋቤ ምላሽ ያለመስጠቱ ጉዳይ ከፆታ ፆታ ልዩነት መኖሩን ከምልከታ 11 ና 12 የተገኙ መረጃዎች ያረጋግጣሉ። አስረጅ፦(ሴ=1፡ወ=5 እና ሴ=1፡ወ=6)።

ከላይ ከሰፈሩት ምልከታዎች በተጨማሪ የመምህራንን ምጋቤ ምላሽ ያለመስጠት ትግበራ በሚመለከት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ ተካተዋል።

ሠንጠረዥ 34:- ከመምህራን ምጋቤ ምላሽ አለማግኘት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 20 | መምህሬ ትክክለኛ መልስ ስሰጥ ከመምህሬ ምንም ዓይነት ምጋቤ ምላሽ አላገኝም። | ሴ | 52 | 39.4 | 21 | 15.9 | 7 | 5.3 | 5 | 3.8 |
| | | ወ | 73 | 55.3 | 36 | 27.3 | 14 | 10.6 | 9 | 6.8 |

ከመምህራን አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ጎራ ከሚመደበው ውስጥ አንዱ ተማሪዎች መልስ በሚመልሱበት ጊዜ መምህራን ምንም ምጋቤ ምላሽ የማይሰጡበት ሁኔታ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት የተካተቱ የክለሳ ድርሳናት መረጃዎች ያስገነዝባሉ። ከዚህ አንፃር ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ሲሰጡ መምህራን አንዳንድ ጊዜ ምንም ዓይነት ምጋቤ ምላሽ እንደማይሰጡ 21 (15.9 %) ሴት ተማሪዎችና 36 (27.3%) ወንዶች ሲገልፁ ምጋቤ ምላሽ ያለማግኘቱ ሁኔታ ፈፅሞ ሐሰት መሆኑን ደግሞ 52 (39.4 %) ሴት ተማሪዎችና 73 ( 55.3 %) ወንዶች ጠቁመዋል። አብዛኛውን ጊዜ የሚለውን ከመረጡ ተማሪዎች መካከል 7(5.3%) ሴቶችና 14(10.6%) ወንዶች ይገኛሉ።



ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

በሌላ በኩል ደግሞ መምህራን በክፍል ውስጥ መስተጋብር አሉታዊ ምጋቤ ምላሾችን የሚሰነዝሩበት አጋጣሚ ስለመኖሩ የሚያመለክቱ ከምልከታ የተገኙ ውጤቶች ይገኛሉ።

ሠንጠረዥ 35፡- ለተማሪዎች የተሰነዘሩ አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሦስት | | ምልከታ አራት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 8. | መምህሯ (ሩ) ለተማሪዎች መልስ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ ሰነዘሩ | 1 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 1 | 1 |

ተጠኚ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ከሰነዘሯቸው አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች መካከል በምልከታ አራት በሁለቱም ፆታዎች ተመሳስሎ ታይቷል። አስረጅ፡-(ሴ=1፡ወ=1)። እንዲሁም በቀሪዎቹ ሦስት ምልከታዎች ደግሞ የመምህራን አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች አንፃራዊ የሆነ ልዩነት ተንፀባርቋል።አስረጅ፡-(ሴ=1፡ወ=2፣ሴ=3፡ወ=1 እና ሴ=2፡ወ=3)።

ለተማሪዎች የተሰነዘሩ አሉታዊ ምጋቤ ምላሾችን በሚመለከት ከምልከታ አምስት እስከ ስምንት የተገኙ ውጤቶች በሠንጠረዥ 36 ውስጥ ይገኛል።

ሠንጠረዥ 36፡- ከመምህራን የተሰነዘሩ አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አምስት | | ምልከታ ስድስት | | ምልከታ ሰባት | | ምልከታ ስምንት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 8. | መምህሯ(ሩ)ለተማሪዎች መልስ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ ሰነዘሩ | 2 | 1 | 1 | 0 | 2 | 0 | 2 | 1 |

ከምልከታ አምስት እስከ ምልከታ ስምንት የተገኙ ውጤቶች መምህራን አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ ለተማሪዎች በመጠኑ የሰጡበት ሁኔታ መኖሩን ይጠቁማሉ። ለሴትና ለወንድ ተማሪዎች የሚሰነዘሩ የመምህራን ምጋቤ ምላሾች አሉታዊ ገጽታቸው በሁለቱም ፆታዎች ላይ አንፃራዊ የሆነ የውጤት መቀራረብ አስገኝቷል። አስረጅ፡-(ሴ=2፡ወ=1፣ሴ=1፡ወ=0፣ሴ=2፡ወ=0 እና ሴ=2፡ወ=1)።

ከዚህ በማስከተል በተካሄዱ ምልከታዎች የተስተዋለው የተጠኝ መምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 37፡- በመስተጋብር ወቅት የተሰነዘሩ አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ ዘጠኝ | | ምልከታ አሥር | | ምልከታ አሥራ አንድ | | ምልከታ አሥራ ሁለት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 8. | መምህሯ(ሩ)ለተማሪዎች መልስ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ ሰነዘሩ | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 |

ከምልከታ ዘጠኝ እስከ 12 የተገኙ የመረጃ ውጤቶች የመምህራን አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች መጠነኛ መሆናቸውን ያሳያሉ፡፡ በዚህም በሁሉም ምልከታዎች የመምህራን አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ለሁለቱም ፆታዎች ተመጣጣኝ መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡ አስረጅ፡- (ሴ=0፡ወ=1፣ሴ=1፡ወ=0፣ሴ=1፡ወ=1 እና ሴ=0፡ወ=0)፡፡

ከላይ በተለያዩ ሠንጠረዥች ከሠፈሩ የምልከታ ውጤቶች በተጨማሪ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች የሚያስገነዝቡት ውጤት በሚከተለው መልክ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 38፡- ተማሪዎች ሲሳሳቱ የሚሰጥ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8 | ተማሪዎች ጥያቄ ተጠይቀው ሲሳሳቱ አሉታዊ የሆኑ ምጋቤ ምላሾችን እሰጣለሁ፡፡ | ሴ | | - | | - | 3 |
| | | ወ | | - | | - | 3 |

በጥያቄ ተራ ቁጥር 8 ላይ ለሰፈረው አሉታዊ የምጋቤ ምላሽ ጥያቄ በሁለቱም ፆታ የሚገኙ መምህራን ተመሳሳይ የሆነ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይኸውም ስድስቱም ተጠኝ መምህራን ተማሪዎች ጥያቄ ተጠይቀው በሚመልሱበት ጊዜ ሲሳሳቱ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ እንደማይሰጡ አመላክተዋል፡፡

ከዚህ ባሻገር የመምህራንን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በሚመለከት ከቀረቡ የተማሪዎች መጠይቅ ውስጥ እጅ አውጥቶ ከመሳተፍ አንፃር ያለው ምላሽ ታይቷል፡፡ ይህን በሚመለከት የተጠኝ መምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ በሠንጠረዥ 39 ላይ ተንፀባርቋል፡፡

ሠንጠረዥ 39:- የመምህራን አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ እጅ ሳያወጡ ከመመለስ አንፃር

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 16 | መምህሬ እጅ ሳላወጣ ስመልስ ይሰድቡኛል (ይገስፁኛል):: | ሴ | 13 | 9.8 | 32 | 24.2 | 37 | 28 | 50 | 37.9 |
| | | ወ | 32 | 24.2 | 50 | 37.9 | 27 | 20.5 | 23 | 17.4 |

በሌላ በኩል ደግሞ የተማሪዎችን እጅ ሳያወጡ የመሳተፍ ሁኔታ የተመለከተ አሉታዊ ጥያቄ ቀርቧል:: ለዚህ ጥያቄ 50 (37.9%) ሴት ተማሪዎች እና 23 (17.4%) ወንዶች እጅ ሳያወጡ ቢመልሱ መምህራን እንደሚገስጿቸው (እንደሚሰድቧቸው) ጠቅሰዋል:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ (አልፎ አልፎ) እጅ ሳያወጡ በሚመልሱበት ጊዜ ከመምህራን ተግሳፅ እንደሚሠነዘር ካመለከቱ ተማሪዎች ውስጥ 32 (24.2%) ሴቶች እና 50 (37.9%) ወንድ ተማሪዎች ተጠቃሽ ናቸው::

የመምህራንን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች በቲ-ስሌት ተፈትሸዋል:: ከስታትስቲክሱ ውጤት የተገኘው መረጃ በሚከተለው መንገድ ቀርቧል::

ሠንጠረዥ 40:- የመምህራን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በt - ስሌት

| ተጠኝዎች | | አማካይ (Mean) | t - ስሌት | P | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | ፆታ | | | | |
| 132 | ወ | 24.0909 | 9.578 | < 0.00 | አለው |
| 132 | ሴ | 20.9242 | | | |

የመምህራንን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በሚመለከት በተጠኙ ተማሪዎች መካከል የምላሽ ልዩነት ተንፀባርቋል:: በዚህ መሠረት የወንድ ተማሪዎች አማካይ ነጥብ 24.0909 ሲሆን የሴት ተማሪዎች ደግሞ 20.9242 ሆኗል:: ይህ ልዩነት በt ስሌት ሲታይ 9.578 ውጤት ተገኝቷል::ይህ ውጤት ደግሞ $P<0.00$ የሆነ ውጤት አስገኝቷል:: የተገኘው ውጤት ሙሉ በሙሉ አስተማማማኝ መሆኑን ያመለክታል:: የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለወንድና ሴት ተማሪዎቻቸው በሚሰጡት አሉታዊ፣ አወንታዊም ሆነ ምንም ምጋቤ ምላሽ ያለመስጠት ሁኔታዎች ላይ ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያስገነዝባል::

ከተገኙት መረጃዎች አንፃር ተጠኝ መምህራኑ በምጋቤ ምላሽ አሰጣጣቸው ላይ የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ችግር መኖሩን ውጤቶች አረጋግጠዋል፡፡በመሆኑም በክፍል ውስጥ መስተጋብር ተማሪዎች ሐሳባቸውን በነፃነት እንዲገልጹ ተጠኝ መምህራን የሚያበረታቱ ቢሆንም የሚሰጡት አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ ግን ከአንዱ ፆታ ወደ ሌላው ልዩነት መኖሩ ተንፀባርቋል፡፡ ይኸውም አብዛኛውን ጊዜ ማበረታቻ የሚሰጡ ለወንድ ተማሪዎች እንደሆነ ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም ሴት ተማሪዎች ጥሩ ሥራ በሚሠሩበት ጊዜ የሚሰጣቸው ምጋቤ ምላሽ ከወንዶች አንፃር አነስተኛ ሆኖ ሲገኝ መልካም ባህርያትን ሲያሳዩ ደግሞ የሚሰጣቸው አበረታች ምጋቤ ምላሽ ከወንዶች በልጦ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ባሻገር መምህራን ለሴት ተማሪዎች አስተያየቶችን በክፍል ውስጥ ብዙ ጊዜ እንደማይነግሯቸው ሲያመለክቱ ወንዶች ግን የመምህራን አስተያየት በክፍል ውስጥ እንደሚሰጡ አሳይቷል፡፡

በተጨማሪም ሴት ተማሪዎች ጥያቄ በሚመልሱበት ወቅት ቢሳሳቱ አብዛኛውን ጊዜ ተግሳጽ (ስድብ) እንደሚሰነዘርባቸውና እጅ ሳያወጡ በሚመልሱበት ወቅት ወንድ ተማሪዎች ከሴቶች ያነሰ ተግሳጽ መሰጠታቸውን ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ሴቶችም ሆኑ ወንድ ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ አብዛኛውን ጊዜ ከመምህራን ምንም ዓይነት ምጋቤ ምላሽ እንደማይሰጣቸው ውጤቶቹ አመላክተዋል፡፡ በዚህም ተማሪዎች በትምህርት ይዘቱ ላይ ሊይዙ የሚገባቸውን ዕውቀት ካለማስጨበጣቸውም በተጨማሪ ተማሪዎች ለሚያከናውኗቸው ተግባራት አፀፋዊ ምላሽ ሲሰጡ አልታዩም፡፡

ይህን በሚመለከት እነ Cruickshank and et al (1995:34– 35) መምህራን ለተማሪዎቻቸው በሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ ላይ የሥርዓተ ፆታ ልዩነት ታይቷል፡፡ ልዩነቱም ለሴት ተማሪዎች በርካታ የማያበረታታና ግልጽ ያልሆነ ትርጉም የለሽ ምጋቤ ምላሾችን ሲሠነዝሩ በአንፃሩ ደግሞ ለወንድ ተማሪዎች አበረታችና ውሱን ምጋቤ ምላሾችን ይለግሳሉ ከሚለው ንድፈ ሐሣብ ጋር የተገኘው ውጤት ይደጋገፋል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ Elliott and et al (2000: 140)፣ Feldman (1996: 358) እና Ayim and Houston (1996: 52) በበኩላቸው እንዳስገነዘቡት በመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ላይ ልዩነት መኖሩን የሚያንፀባርቁ ማህበራዊ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለሥርዓተ ፆታ የሚሰጥ ልማዳዊ አድሏዊ አመለካከት ነው፡፡ በዚህም ወንድ ተማሪዎች ለሠሯቸው ጥሩ ሥራዎች በማበረታቻ መልክ በርካታ ሽልማቶችን ሲሰጡ ሴት ተማሪዎች ደግሞ ጥሩ ባህርይ ሲያሳዩ እንደሚበረታቱ ካሠፈሩት ጥናት ጋር ይዛመዳል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ Olson (2000: 274) እና Delamont (1994:42) ሲገልፁ ሁለቱ ፆታዎች በሚገኙበት መማሪያ ክፍል ውስጥ በርካታ ቃላዊ የሆኑ ማበረታቻዎችንና አስተያየቶችን



ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

መምህራን ለወንድ ተማሪዎች እንደሚለግሱ ካሰፈሩት ጥናት ጋር የመረጃዎች ውጤት ተያያዥነት አለው፡፡

እነ Bukatko and Daehler (1992: 526) ደግሞ በመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን ለወንድ ተማሪዎች የሚሰነዝሩት ትችት ትምህርት ነክ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ያነጣጠሩ እንደሆነ በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡በጥናቱም ሴት ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ በሚሰጡበትና እጅ ሳያወጡ በሚመልሱበት ጊዜ ከመምህራን በርከት ያሉ ትችቶችን እንዳገኙ ከጠቆሙት ውጤት ጋር የተገኙት የመረጃ ውጤቶች ተዛምዶ አላቸው፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር (1990:33) እንዳሠፈረው ተማሪዎች በሚጠየቁበት፣ መልስ በሚመልሱበት ወይም በሚሳሳቱበት ጊዜ ተገቢውን እርምት በአግባቡ ማድረግ እንጂ ተማሪዎችን መገሰጽ፣ ማንቋሸሽ፣ መስደብ፣ መምታት፣ ማስፈራራት፣ ትምህርቱን እንዲጠሉት ያደርጋል፡፡ ከዚህ ንድፈ ሐሣብ አንፃር መምህራን ሲተገብሩ እንዳልተስተዋሉ መረጃዎች ያጠናክራሉ፡፡ በተጨማሪም እነ Sadker and et al (1999: 136) ያሰፈሩት ጥናት እንደሚያስገነዝበው በክፍል ውስጥ መስተጋብር ሁለቱም ፆታዎች እጃቸውን ሳያወጡ በሚመልሱበት ወቅት ወንዶችን ችላ በማለት ምላሾቻቸውን እንደተቀበሉና ለሴት ተማሪዎች ግን የማያበረታታ ምላሽ እንደሰነዘሩ ከጠቆሙት ጥናት ጋር የተጠኘ መምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ መረጃ ውጤት ተዛምዷል፡፡

### 4.2.3 የመምህራን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ

የመምህራንን የሥርዓተ-ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበራቸውን ለመፈተሽ ከሚረዱ ተላውጦዎች ውስጥ አንዱ የተሳትፎ ዕድል አሰጣጣቸው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ለተማሪዎች የተሳትፎ ዕድል መስጠት በትምህርት መስክ ሁለንተናዊ የሆነ ፋይዳ ያስገኛል፤ እኩል ዕድል አለመስጠት ደግሞ ፆታን መሠረት ባደረገው ለሥርዓተ ፆታ ሚና ከሚኖረን አመለካከት ጋር ይያያዛል፡፡ በክፍል ውስጥ መስተጋብር መምህራን ለሴትና ለወንድ ተማሪዎች እኩል የተሳትፎ ዕድል ቢሰጡ በትምህርት መስክ የሚንፀባረቀውን ያልተመጣጠነ የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ለማስወገድ ሰፊ ድርሻ ይኖረዋል (Ascroft and Foreman-Peck 1994:154)፡፡

ከዚህ ንድፈ ሃሳብ አኳያ የመምህራንን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ የተመለከቱ የምልከታ መረጃዎች ውጤት በሚከተለው መንገድ በሠንጠረዥ 41 ላይ ሰፍሯል፡፡

ሠንጠረዥ 41፡- በተማሪዎች ተሳትፎ የመምህራን ጣልቃ ገብነት

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሦስት | | ምልከታ አራት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 2. | መምህሩ በተማሪዎች ምላሽ ጣልቃ ገቡ | 2 | 2 | 1 | 1 | 3 | 0 | 2 | 1 |

ተጠኝ መምህራኑ በክፍል ውስጥ መስተጋብር ለተማሪዎች የተሳትፎ እድል መስጠታቸውን ከምልከታ አንድ እስከ አራት ያሉ የመረጃ ውጤቶች ያመላክታሉ፡፡ በመሆኑም በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ የመምህራን ጣልቃ መግባት ከፆታ አንፃር በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምልከታዎች ተመሳሳይ ውጤት ተስተውሏል፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=2፡ወ=2 እና ሴ=1፡ወ=1)፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በምልከታዎች ውጤት ላይ እንደሰፈረው በምልከታ ሦስትና አራት ተጠኝ መምህራን በተማሪዎቻቸው ተሳትፎ ላይ ጣልቃ የመግባታቸው ሁኔታ በሴት ተማሪዎች ላይ ጎልቶ ታይቷል፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=3፡ወ=0 እና ሴ=2፡ወ=1)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በተማሪዎች ምላሽ የመምህራንን ጣልቃ መግባት የተፈተሸበት ሁኔታ አለ፡፡ የቀጣይ ምልከታዎች ውጤትም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 42፡- የመምህራን ጣልቃ መግባት በተማሪዎች ምላሽ

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አምስት | | ምልከታ ስድስት | | ምልከታ ሰባት | | ምልከታ ስምንት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 2. | መምህሯ(ሩ) በተማሪዎች ምላሽ ጣልቃ ገቡ | 3 | 2 | 2 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 |

በአራቱም የምልከታ ምድቦች የተገኙ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ተማሪዎች ምላሽ በሚሰጡበት ሰዓት ተጠኝ መምህራን በንግግራቸው ጣልቃ መግባታቸውን ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ከተማሪዎች ፆታ አንፃር በምልከታ ሰባት ተመሣሣይ የሆነ ውጤት ታይቷል፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=3፡ወ=3)፡፡ ይሁን እንጂ በቀሩት ሦስት ምልከታዎች አንፃራዊ የሆነ የውጤት ልዩነት ተስተውሏል፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=3፡ወ=2፣ ሴ=2፡ወ=1 እና ሴ=2፡ወ=3)፡፡

ሠንጠረዥ 43፡- በተማሪዎች ምላሽ የመምህራን ጣልቃ መግባት

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ ዘጠኝ | | ምልከታ አስር | | ምልከታ አስራ አንድ | | ምልከታ አስራ ሁለት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 2. | መምህሩ በተማሪዎች ምላሽ ጣልቃ ገቡ | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 0 | 2 | 1 |

በመጨረሻዎቹ የምልከታ ምድቦች የተገኙ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በተማሪዎች መልስ አሰጣጥ ወቅት የመምህራን ጣልቃ ገብነት የተንፀባረቀበት ሁኔታ መኖሩን ነው፡፡ በዚህም በምልከታ ዘጠኝ የመምህር ጣልቃ መግባት በሁለቱም ፆታዎች ተመሳሳይ ውጤት ታይቷል፡፡ አስረጅ፡- (ሴ=2፡ወ=2)፡፡ በተማሪዎች ምላሽ የመምህራን ጣልቃ ገብነት ደግሞ በሌሎች ሦስት ምልከታዎች ላይ አንፃራዊ የሆነ ልዩነት ተስተውሏል፡፡ በመሆኑም የመምህራን ጣልቃ ገብነት በሴት ተማሪዎች ላይ አመዝኖ እንደታየ የምልከታ ውጤቱ ያረጋግጣል፡፡ አስረጅ፡- (ሴ=1፡ወ=2፣ ሴ=2፡ወ=0 እና ሴ=2፡ወ=1)፡፡

ከላይ የመምህራንን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ በተመለከተ በቀረቡ ምልከታዎች ያልተገኙ ነጥቦችን ለመፈተሽ ከተማሪዎች ክፍት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች አሉ፡፡ ከክፍት ጥያቄዎች መካከል በትምህርት ሂደቱ ሐሳብሽ(ህ)ን ለመግለጽ ስትቸገሪ(ር) መምህርሽ(ህ) ምን ያርጋሉ? የሚለው ጥያቄ ተጠቃሽ ነው፡፡ ከጥያቄው የተገኙ አብዛኞዎቹ ምላሾች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ በተገኙ ምላሾች መሠረት ተማሪዎች ሐሳባቸውን ለመግለጽ ሲቸገሩ መምህራን "ጥያቄውን ደግመው እንደሚናገሩ"፣ "በንግግራቸው ጣልቃ በመግባት እንደሚያቋርጡ"፣ "ትችት(ሒስ) እንደሚሰነዝሩ"፣ "ዕድሉን ለሌላ ተማሪ እንደሚሰጡ" ገልፀዋል፡፡

ከክፍት መጠይቁ ውጤት በተገኘው መረጃ መሠረት በሌሎች ተማሪዎች ያልተመለሱ ያቂዎችን እንዲመልሱ ዕድል የሚሰጣቸው መሆኑን ለማወቅ ዝግ መጠይቅ ቀርቧል፡፡ በዚህም የተገኘው ውጤት በሠንጠረዥ 44 ውስጥ እንደሚከተለው ተካቷል፡፡

ሠንጠረዥ 44፡- በሌሎች ተማሪዎች ያልተመለሱ ጥያቄዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 8 | መምህሬ ሌሎች ተማሪዎች ያልመለሱትን ጥያቄ እንድመልስ ዕድል ይሰጡኛል | ሴ | 13 | 9.8 | 35 | 26.5 | 34 | 25.8 | 50 | 37.9 |
| | | ወ | 5 | 3.8 | 28 | 21.2 | 41 | 31.1 | 58 | 43.9 |

በተራ ቁጥር 8 ለሰፈረው አወንታዊ ጥያቄ 13(9.8%) ሴቶች እና 5(3.8%) ወንዶች በሌሎች ተማሪዎች ያልተመለሱ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ዕድል የማይሰጣቸው መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ያልተመለሱ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ዕድል እንደሚሰጣቸው ከጠቅሙ ተማሪዎች ውስጥ 34 (25.8%) ሴቶችና 41 (31.1%) ወንዶች ይገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በመምህራን አሳታፊነት ለተጠየቁ ጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሽ የሰጡ ተማሪዎችን የተመለከቱ ምልከታዎች ይገኛሉ፡፡

ሠንጠረዠ 45፡- የተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሦስት | | ምልከታ አራት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 3. | ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሰጡ | 5 | 11 | 4 | 8 | 4 | 11 | 7 | 11 |

በመምህራን ለቀረቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች ምላሽ መስጠታቸውን በጥያቄ ተራ ቁጥር 3 ውስጥ ያለው መረጃ ያስገነዝባል፡፡ ከምልከታዎች እንደታየው መልስ ከሰጡ ተማሪዎች ውስጥ በሰጡት ትክክለኛ ምላሽ ከፆታ አንፃር ልዩነት ተንፀባርቋል፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=5፡ወ=11፣ ሴ=4፡ወ=8፣ ሴ=4፡ወ=11 እና ሴ=7፡ወ=11)፡፡ ይህ ሁኔታ በሌሎች ምልከታዎች ላይ ያስገኘው ውጤት በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ ሰፍሯል፡፡

ሠንጠረዥ 46፡- በመምህራን አሳታፊነት የተሰጡ ትክክለኛ ምላሾች

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አምስት | | ምልከታ ስድስት | | ምልከታ ሰባት | | ምልከታ ስምንት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 3. | ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሰጡ | 7 | 12 | 6 | 10 | 6 | 12 | 7 | 12 |

በመምህራን አሳታፊነት ትክክለኛ ምላሾች በሁለቱም ፆታ ተማሪዎች እንደተስነዘሩ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ እነዚህ መረጃዎች ደግሞ ከተማሪዎች ፆታ አንፃር ሲታዩ ወንድ ተማሪዎች ለጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሽ የሰጡበት ሁኔታ ጎላ ብሎ ተንፀባርቋል፡፡ አስረጅ፡- (ሴ=7፡ወ=12፣ ሴ=6፡ወ=10፣ሴ=6፡ወ=12 እና ሴ=7፡ወ=12)፡፡

የተማሪዎችን ትክክለኛ ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ ከምልከታ ዘጠኝ እስከ አስራ ሁለት የተገኙ ውጤቶች በሚከተለው መልክ ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 47፡- ትክክለኛ መልስ የሰጡ ተማሪዎች

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ ዘጠኝ | | ምልከታ አስር | | ምልከታ አስራ አንድ | | ምልከታ አስራ ሁለት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 3. | ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሰጡ | 5 | 9 | 7 | 9 | 3 | 9 | 3 | 11 |

በጥያቄ ተራ ቁጥር 3 የሰፈረው የምልከታ የትኩረት ነጥብ በሁለቱም ፆታ የሚገኙ ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ መስጠታቸውን ያንፀባርቃል፡፡ ተማሪዎች የሰጡት ትክክለኛ ምላሽ ግን በፆታዎች መካከል ልዩነት ሊታይ መቻሉን የምልከታዎቹ ውጤት ያረጋግጣሉ፡፡ አስረጅ፡- (ሴ=5፡ወ=9፣ ሴ=7፡ወ=9፣ሴ=3፡ወ=9 እና ሴ=3፡ወ=11)፡፡

ከእነዚህ ምልከታዎች በተቃራኒ የተማሪዎችን የተሳሳተ መልስ አሰጣጥ የሚመለከቱ የምልከታ ውጤቶች ደግሞ በሠንጠረዥ 48 ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ሠንጠረዥ 48፡- የተማሪዎች የተሳሳተ ምላሽ

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሦስት | | ምልከታ አራት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 4. | ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ሰጡ | 1 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 0 | 1 |

የአራቱም ምልከታ ውጤት እንደሚያስገነዝበው ተማሪዎች መልስ በሚሰጡበት ጊዜ የተሳሳተ ምላሽ የሰጡበት ሁኔታ መንፀባረቁን ነው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎች የተሳሳተ ምላሽ አሰጣጥ

ከሁለቱም ፆታ ተማሪዎች አንፃር ሲታይ መጠነኛ የሆነ ልዩነት ሊታይ ችሏል። አስረጅ:-(ሴ=1፡ወ=2፣ ሴ=3፡ወ=2፣ሴ=1፡ወ=2 እና ሴ=0፡ወ=1)።

ከዚህ በተጨማሪ በተካሄዱ ምልከታዎች የተገኘው የምልከታ ውጤት ደግሞ እንደሚከተለው ሠፍሯል።

ሠንጠረዥ 49:- ከተማሪዎች የተሰነዘሩ የተሳሳቱ ምላሾች

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አምስት | | ምልከታ ስድስት | | ምልከታ ሰባት | | ምልከታ ስምንት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 4. | ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ሰጡ | 2 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 |

ከምልከታ አምስት እስከ ምልከታ ስምንት የተገኙ የመረጃ ውጤቶች በመምህራን ለተጠየቁ ጥያቄዎች ተማሪዎች የተሳሳተ ምላሽ መስጠታቸውን ያሳያሉ። በሁለቱም ፆታ የሚገኙ ተማሪዎች የተሳሳተ ምላሽ አሰጣጥ ደግሞ በሴትና በወንድ ተማሪዎች ውጤት ላይ ቅርርቦሽ ታይቷል። አስረጅ:-(ሴ=2፡ወ=1፣ ሴ=2፡ወ=2፣ሴ=3፡ወ=3 እና ሴ=1፡ወ=2)።

እንዲሁም በመጨረሻዎቹ ምልከታዎች ላይ የተገኙ ውጤቶች በሠንጠረዥ 50 ውስጥ ተካተዋል።

ሠንጠረዥ 50:- በመምህራን አሳታፊነት የተገኙ የተሳሳቱ ምላሾች

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ ዘጠኝ | | ምልከታ አስር | | ምልከታ አስራ አንድ | | ምልከታ አስራ ሁለት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 4. | ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ሰጡ | 2 | 1 | 1 | 3 | 0 | 2 | 1 | 2 |

በመምህራን ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ከተሳተፉ ተማሪዎች ውስጥ የተሳሳተ ምላሽ የሰጡ በሁለቱም ፆታ የሚገኙ ተማሪዎች እንደሆኑ ምልከታዎች ያሳያሉ። እነዚህ ምልከታዎች የተሳሳተ ምላሽ ከመስጠት አንፃር አንዱ ፆታ ወደ ሌላው ልዩነት እንዳለ ያመላክታሉ። አስረጅ:-(ሴ=2፡ወ=1፣ ሴ=1፡ወ=3፣ሴ=0፡ወ=2 እና ሴ=1፡ወ=2)።

የተማሪዎችን ትክክለኛና የተሳሳተ ምላሽ ከሚዳስሱ የምልከታ ውጤቶች በተጨማሪ እጅ ሳያወጡ የመለሱ ተማሪዎች ውጤት በምልከታ የትኩረት ነጥቦች ውስጥ ተካተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 51፡- እጅ ሳያወጡ የመለሱ ተማሪዎች

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሦስት | | ምልከታ አራት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 10. | ተማሪዎች እጅ ሳያወጡ መለሱ | 1 | 6 | 2 | 7 | 1 | 5 | 2 | 6 |

ተማሪዎች በመምህራን ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ መስጠታቸውን በጥያቄ ተራ ቁጥር 10 ሥር የሰፈሩ መረጃዎች እማኝ ናቸው፡፡ እነዚህ ምላሾች እጅ አውጥቶ ከመመለስ አንፃር ሲታዩ ወንድ ተማሪዎች እጅ ሳያወጡ የተሳተፉበት ሁኔታ አመዝኖ ታይቷል፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=1፡ወ=6፣ ሴ=2፡ወ=7፣ሴ=1፡ወ=5 እና ሴ=2፡ወ=6)፡፡

የተማሪዎች ምላሽ እጅ ከማውጣት አንፃር የተፈተሸበት ውጤት ደግሞ ከምልከታ አምስት እስከ ስምንት የሚገኙት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 52፡- እጅ ሳያወጡ የተሳተፉ ተማሪዎች

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አምስት | | ምልከታ ስድስት | | ምልከታ ሰባት | | ምልከታ ስምንት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 10. | ተማሪዎች እጅ ሳያወጡ መለሱ | 3 | 8 | 2 | 6 | 3 | 7 | 2 | 8 |

በመምህራን አነሳሽነት ለቀረቡ ጥያቄዎች እጅ ሳያወጡ መልስ የሰጡ ሴትና ወንድ ተማሪዎች እንደሆኑ የምልከታ ውጤቱ ያስገነዝባል፡፡ ተማሪዎች እጅ ሳያወጡ ምላሽ የሰጡበት ሁኔታ ከፆታ አንፃር ልዩነት መኖሩ ተንፀባርቋል፡፡ ለዚህም ለጥያቄዎች መልስ ከሰጡ ተማሪዎች መካከል እጅ ሳያወጡ የመለሱ ሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶች አንፃር አንሶ መገኘቱን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=3፡ወ=8፣ሴ=2፡ወ=6፣ሴ=3፡ወ=7 እና ሴ=2፡ወ=8)፡፡

በመጨረሻም ከምልከታ ዘጠኝ እስከ አስራ ሁለት ተማሪዎች እጅ ሳያወጡ የተሳተፉበት ሁኔታ ስለመኖሩ የተገኘው ውጤት በሚከተለው መልክ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 53፡- ተማሪዎች እጅ ሳያወጡ ተሳተፉ

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ ዘጠኝ | | ምልከታ አስር | | ምልከታ አስራ አንድ | | ምልከታ አስራ ሁለት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 10. | ተማሪዎች እጅ ሳያወጡ መለሱ | 3 | 5 | 2 | 5 | 1 | 8 | 2 | 7 |

የተጠኝ መምህራንን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ እጅ አውጥቶ ከመሳተፍ አኳያ ሲታይ እጅ ሳያወጡ የተሳተፎ ዕድል ያገኙ ሴትና ወንድ ተማሪዎች መኖራቸውን ያመላክታል፡፡ ይሁን እንጂ ከመምህራኑ ለቀረበላቸው ጥያቄ እጅ ሳያወጡ የመለሱ ወንድ ተማሪዎች ቁጥር የላቀ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=3፡ወ=5፣ ሴ=2፡ወ=5፣ሴ=1፡ወ=8 እና ሴ=2፡ወ=7)፡፡

የተማሪዎች ተሳትፎ እጅ አውጥቶ ከማሳተፍ አንፃር በምልከታዎች ከታየው በተጨማሪ ለመምህራን በቀረቡ የጽሑፍ መጠይቆች የተስተዋሉ ውጤቶች አሉ፡፡

ሠንጠረዥ 54፡- እጅ ሳያወጡ ተጠይቀው ትክክለኛ መልስ የሚሰጡ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 2. | ብዙ ጊዜ እጅ ሳያወጡ ተጠይቀው ትክክለኛውን መልስ የሚመልሱ ወንድ ተማሪዎች ናቸው፡፡ | ሴ | 1 | | - | | 2 |
| | | ወ | - | | - | | 3 |

እጅ ሳያወጡ ተጠይቀው ትክክለኛ ምላሽ የሚሰጡ ወንድ ተማሪዎች ስለመሆናቸው ለማወቅ ለቀረበው አሉታዊ ጥያቄ አምስቱ መምህራን (ሁለት ሴቶች እና ሦስት ወንዶች) አለመስማማታቸውን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ አንዷት መምህር በጉዳዩ ላይ እንደሚስማሙ ጠቁመዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የተማሪዎችን ተሳትፎ ከፈቃደኝነታቸው አንፃር ማሳተፍ መቻላቸውን ለመምህራን መጠይቅ ቀርቧል፡፡ ከመጠይቅ ውጤቱ የተገኙ መረጃዎች እንዲሚከተለው ሠፍረዋል፡፡

ሠንጠረዥ 55፡- በተማሪዎች ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ተሳትፎ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3. | በክፍል ተሳትፎ ውስጥ ጥያቄ ስጠይቅ ፈቃደኛ ካልሆኑ ተማሪዎች ይልቅ ብዙጊዜ ፈቃደኛ ለሆኑት ቅድሚያ እሰጣለሁ፡፡ | ሴ | - | | 2 | 1 | |
| | | ወ | 3 | | - | - | |

በክፍል ውስጥ ተሳትፎ በራሳቸው ተነሳሽነት ከማይሳተፉ ተማሪዎች ይልቅ ብዙ ጊዜ በፈቃደኝነት ለሚሳተፉ ተማሪዎች ቅድሚያ ይሰጡ እንደሆነ ለመምህራን ለቀረበው አሉታዊ ጥያቄ ሦስት ወንድ መምህራን እንደሚስማሙ ሲገልጹ አንዷት መምህር ደግሞ አለመስማማታቸውን ጠቁመዋል፡፡ እንዲሁም ሌሎች ቀሪ ሁለት ሴት መምህራን ለመወሰን መቸገራቸውን አመላክተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የተጠኙ መምህራኑ የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ ተማሪዎችን በቡድን ከማሳተፍ አንፃር የተገኙ መረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 56፡- የሁለቱንም ፆታ ተማሪዎች በቡድን ማሳተፍ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9 | ተማሪዎችን በተመሣሣይ ፆታ በቡድን ሥራ ከማሳተፍ ይልቅ ሁለቱም ፆታዎች በጋራ ቢሠሩ ይመረጣል፡፡ | ሴ | 2 | | 1 | - | |
| | | ወ | 3 | | - | - | |

የተጠኙ መምህራን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ ምን መልክ እንዳለው ለማወቅ ለቀረበው አወንታዊ ይዘት ያለው ጥያቄ በሠንጠረዡ ውስጥ ውጤቱ ሰፍሯል፡፡ መረጃዎች በሁለቱም ፆታ የሚገኙ ተማሪዎች በጋራ ቢሠሩ ተመራጭነት እንዳለው ከተጠኙ መምህራን መካከል አምስቱ መስማማታቸውን አመልክተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ሁለት ሴቶች እና ሦስት ወንድ መምህራን ይገኛሉ፡፡ ከአጠቃላይ ተጠኙ መምህራን ውስጥ አንዷት ሴት መምህር በጉዳዩ ላይ ለመወሰን መቸገራቸውን ጠቁመዋል፡፡

ከጽሑፍ መጠይቁ በተጨማሪ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ እንደሚያስገነዝበው በክፍል ውስጥ ተግባራት ለሁለቱም ፆታዎች እኩል የሃላፊነት ድርሻ የሚሰጡ ስለመሆኑ

ለቀረበው ጥያቄ ሁሉም ተጠኝ መምህራን በክፍል ውስጥ ተግባራት ሴትና ወንድ ተማሪዎችን እኩል የሃላፊነት ድርሻ እንደሚሰጡ ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡

እንዲሁም የመምህራንን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ በሚመለከት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በሠንጠረዥ 57 ውስጥ ተካቷል፡፡

ሠንጠረዥ 57፡- ተማሪዎችን በቡድን ሥራ እንዲሳተፉ ማድረግ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 14 | መምህሬ ሴትና ወንድ ተማሪዎችን በቡድን ሥራ እንዲሳተፉ ያደርጋሉ | ሴ | 4 | 3 | 12 | 9.1 | 26 | 19.7 | 90 | 68.2 |
| | | ወ | 6 | 4.5 | 13 | 9.8 | 33 | 25 | 80 | 60.6 |

መምህራን ሴትና ወንድ ተማሪዎች በቡድን ሥራ እንዲሳተፉ የማድረጋቸውን ሁኔታ ብዙ ጊዜ እንደሚተገብሩ 90 (68.2%) ሴት ተማሪዎችና 80 (60.6%) ወንዶች አመልክተዋል፡፡ ተማሪዎች በቡድን ሥራ ላይ እንዲሳተፉ የሚደረገው የመምህራን ትግበራ አብዛኛውን ጊዜ መሆኑን ከጠቆሙ ተማሪዎች ውስጥ 26(19.7%) ሴቶችና 33(25%) ወንዶች ይገኛሉ፡፡

ከዚህ በተቃራኒ መምህራን ተማሪዎችን በግል እንዲሠሩ የሚያደርጉ ስለመሆኑ ለተማሪዎች የቀረበ መጠይቅ ይገኛል፡፡ የመጠይቅ ውጤቱ ደግሞ የሚከተለው ነው፡፡

ሠንጠረዥ 58፡- ተማሪዎችን በግል እንዲሠሩ ማድረግ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 21 | መምህሬ ተግባራትን በተፎካካሪነት (በግል) እንድሠራ ያደርጋሉ | ሴ | 55 | 41.7 | 40 | 30.3 | 25 | 18.9 | 12 | 9.1 |
| | | ወ | 17 | 12.9 | 36 | 27.3 | 56 | 42.4 | 23 | 17.4 |

በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን በግል እንዲተገብሩ የማያሳትፉ መሆኑን 55(41.7%) ሴቶች እና 17(12.9%) ወንዶች አስገንዝበዋል፡፡ ይሁን እንጂ ለዚህ አሉታዊ የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ ጥያቄ 25 (18.9%) ሴት ተማሪዎችና 56(42.4%)ወንዶች ተግባራትን በግል (በተፎካካሪነት) እንዲሠሩ አብዛኛውን ጊዜ መምህራን የተሳትፎ ዕድል እንደሚሰጧቸው ገልፀዋል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ... LIBRARY

እንዲሁም የመምህራን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ ከተማሪዎች አቀማመጥ አንጻር የታየበት ሁኔታ አለ:: ይህን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች በሠንጠረዥ 59 ውስጥ ተካተዋል::

ሠንጠረዥ 59፡- ፊትም ሆነ ኋላ የተቀመጡ ተማሪዎችን ማሳተፍ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 6 | መምህሬ ካሉት ወንድ ተማሪዎች አንፃር | ሴ | 23 | 17.4 | 19 | 14.4 | 41 | 31.1 | 49 | 37.1 |
| | ፊትም ሆነ ኋላ የተቀመጡትን ያሳትፋሉ | ወ | 6 | 4.5 | 26 | 19.7 | 46 | 34.8 | 54 | 40.9 |

የመምህራን አወንታዊ የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥን በሚመለከት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያስገነዝበው በየትኛውም ሥፍራ (ፊትም ሆነ ኋላ) የተቀመጡ ወንድ ተማሪዎችን መምህራን ሁል ጊዜ እንደሚያሳትፉ ከ103 መላሾች ውስጥ 49(37.1%) ሴቶችና 54(40.9%) ወንዶች ገልፀዋል:: የተሳትፎ ዕድል አሰጣጡን ጉዳይ መምህራን ፈጽሞ እንደማይተገብሩት ከገለጹ ተማሪዎች ውስጥ 23(17.4%) ሴቶችና 6(4.5%) ወንድ ተማሪዎች ይገኛሉ::

ከተማሪዎች አቀማመጥ አንፃር የመምህራኑን የማሳተፍ ሁኔታ የሚዳስስ የመጠይቅ ውጤት በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ ይገኛል::

ሠንጠረዥ 60- የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 18 | መምህሬ ካሉት ሴት ተማሪዎች አንፃር ፊት ለተቀመጡት ብቻ የተሳትፎ ዕድል ይሰጣሉ:: | ሴ | 54 | 40.9 | 47 | 35.6 | 17 | 12.9 | 14 | 10.6 |
| | | ወ | 55 | 44.7 | 40 | 30.3 | 29 | 22 | 8 | 6.1 |

የተማሪዎች መጠይቅ ውጤት እንደሚያመላክተው መምህራን በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ሴት ተማሪዎች አንፃር ፊት ለተቀመጡት ብቻ ሁልጊዜ የተሳትፎ ዕድል እንደሚሰጡ 14(10.6%) ሴት እና 8(6.1%) ወንድ ተማሪዎች ጠቁመዋል:: ለዚህ አሉታዊ ጥያቄ ሁኔታው አብዛኛውን ጊዜ እንደሚተገበር ደግሞ 17(12.9%) ሴት ተማሪዎች እና 29(22%) ወንዶች ገልፀዋል::

በመጨረሻም ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ውጤት ከቲ-ስሌት አንፃር ታይቷል።

ሠንጠረዥ 61፡- የመምህራን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ ውጤት በቲ-ስሌት

| ተጠኝዎች | | አማካይ (Mean) | ቲ-ስሌት | p | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | ፆታ | | | | |
| 132 | ወንድ | 17.1061 | 1.489 | >0.05 | የለውም |
| 132 | ሴት | 16.6515 | | | |

የመምህራንን አወንታዊም ሆነ አሉታዊ የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ በሚመለከት ከተማሪዎች መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረት ወንድ ተማሪዎች 17.1061 የሆነ ውጤት አስመዝግበዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የሴት ተማሪዎች ውጤት 16.6515 መሆኑን ሠንጠረዡ ያሳያል። ይህ አማካይ ነጥብ በሁለቱ ፆታዎች ላይ የመምህራንን የተሳተፎ እድል አሰጣጥ ልዩነት መኖሩን ያመለክታል። የተገኘው ልዩነት ደግሞ 1.489 የሆነ ውጤት በስታትስቲካዊ ስሌት አስገኝቷል። ይህ ስሌት ደግሞ P > 0.05 የሚሆን ውጤት በማስገኘቱ ከሁለቱ ተማሪዎች ፆታ የተገኘው መረጃ ግን ጉልህ የሆነ ልዩነት አለመገኘቱን ያረጋግጣል።

በአጠቃላይ የተጠኝ መምህራንን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ ለመፈተሽ የዋሉ የመረጃ ውጤቶች እንደሚያሳዩት መምህራን እጅ ሳያወጡ ከማሳተፍና በንግግር ጣልቃ ከመግባት አንፃር ችግር መኖሩ ተንፀባርቋል። እጅ ሳያወጡ የሚሳተፉ ሴት ተማሪዎች ብዛት አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ይህን ሁኔታ ትምህርት ሚኒስቴር (1990:33) በክፍል ውስጥ እጃቸውን የሚያወጡ ተማሪዎች ብቻ ትክክለኛውን መልስ ይመልሳሉ ማለት አይደለም። ሆኖም ተማሪዎች መምህራን ካልጠየቋቸው በስተቀር አስተያየት የማይሰጡ ወይም ሐሳብ ለመስጠት የማይፈልጉ፣ የሚፈሩ ተማሪዎች አሉ። ይህ በብዙ ሴት ተማሪዎች ላይ ይታያል። ስለዚህ መምህራን በስም እየጠሩ ተማሪዎች እንዲሳተፉ፣ ጥያቄ እንዲመልሱ ወይም እንዲጠይቁ ማደፋፈር እንደሚጠበቅባቸው የሚያትተውን ንድፈ ሐሣብ ተጠኝ መምህራኑ ተግባራዊ ሲያደርጉ አልተስተዋለም።

በተመሳሳይ ሁኔታ Delamont (1994: 42) በክፍል ውስጥ መስተጋብር በቃላዊ ንግግር ወቅት የመምህራን ጣልቃ ገብነት በሴት ተማሪዎች ላይ እንደሚያመዝን ካስገነዘበው ንድፈ ሐሣብ ጋር የጥናቱ ውጤቶች ተደጋጋፊነት አላቸው። እንዲሁም Valian (1998:65) ስትገልጽ በመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ላይ ክፍተት መኖሩን ከሚያመላክቱ ነጥቦች ውስጥ አንዱ የመምህራን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ ነው። ይኸውም ወንድ ተማሪዎች ከመምህራን ፈቃድ

ሳያገኙ (እጅ ሳያወጡ) መልስ በሚመልሱበት ጊዜ ተቀባይነት እንደሚያገኙ ካሠፈረችው የጥናት ውጤት ጋር መረጃዎች ተዛምዶ አላቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የመምህራንን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ የሚፈትሹ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ለተማሪዎች ተሳትፎ ዕድል የሚሰጡ መሆኑን ያሳያሉ፡፡ ይህ የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ ከሥርዓተ ፆታ አተገባበር አንፃር መጠነኛ የሆነ ክፍተት ተንፀባርቋል፡፡በመሆኑም በአብዛኛው ወንድ ተማሪዎችን በተፎካካሪነት እንዲሰሩ የሚጋብዝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሴቶች ተማሪዎችን ብዙ ጊዜ የሚያሳትፉ ፊት መቀመጫ አካባቢ የተቀመጡትን እንደሆነ መረጃዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ይህን የሚመለከት እነ Bukatko and Daehler (1992:524) እና Rhona (1982:678) ሲገልጹ የመምህራን ትኩረት የተማሪዎችን አቀማመጥ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም ይበልጥ ትኩረት የሚሰጡ ፊት በፀጥታ ለተቀመጡ ሴት ተማሪዎች ሲሆን ወንድ ተማሪዎች ግን በየትኛውም ቦታ ቢቀመጡ የመምህራን ትኩረት እንደሚያገኙ ካሠፈሩት የጥናት ውጤት ጋር የመረጃ ውጤቶች ይዛመዳሉ፡፡

### 4.2.4. የመምህራን የቆይታ ጊዜ አሰጣጥ

በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚኖር መስተጋብር የቆይታ ጊዜ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ጥያቄ እስኪመልሱ ድረስ ያለው ቆይታ በጣም ጥቂት ከሆነ ተማሪዎች ስለጥያቄው እንዳያስቡ ያደርጋል፡፡ ሆኖም ተመጣጣኝ የሆነ የቆይታ ጊዜ ጠቀሜታው የጎላ ነው Nunan and Lamb (1996:84–87)፡፡ ከዚህ ንድፈ ሃሳብ አንጻር በምልከታ የተገኙ ውጤቶች በሚከተለው መልክ ሰፍረዋል፡፡

ሠንጠረዥ 62፡- የጥያቄ መመለሻ ረዘም ያለ ጊዜ

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሦስት | | ምልከታ አራት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 5 | መምህሯ(ሩ) ለጥያቄ መመለሻ ረዘም ያለ ጊዜ ሰጡ | 2 | 4 | 1 | 3 | 0 | 2 | 2 | 5 |

አራቱ የምልከታ ውጤቶች ተጠኚ መምህራን በጥያቄ መመለሻ ጊዜ አንፃራዊ የሆነ ርዝመት ለወንድ ተማሪዎች እንደሰጡ ያረጋግጣሉ፡፡ አስረጅ፡-(ሴ=2፡ወ=4፣ሴ=1፡ወ=3፣ሴ=0፡ወ=2 እና ሴ=2፡ወ=5)፡፡

ከምልከታ አምስት እስከ ስምንት የመምህራንን የቆይታ ጊዜ አሰጣጥ የተመለከቱ መረጃዎች በሠንጠረዥ 63 ውስጥ ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 63፦ የተማሪዎች መልስ መስጫ ጊዜ

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ አምስት | | ምልከታ ስድስት | | ምልከታ ሰባት | | ምልከታ ስምንት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 5 | መምህሯ(ሩ) ለጥያቄ መመለሻ ረዘም ያለ ጊዜ ሰጡ | 3 | 6 | 1 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 |

በተራ ቁጥር 5 ሥር የቆይታ ጊዜ አመዳደብን የተመለከተው ጥያቄ ውጤቶች እንደሚያሳዩት በሁለቱም ጾታ ተማሪዎች መካከል የውጤት ልዩነት መኖሩን ያረጋግጣሉ። አስረጅ፦ (ሴ=3፡ወ=6፣ሴ=1፡ወ=3፣ሴ=2፡ወ=3 እና ሴ=1፡ወ=2)።

በመጨረሻዎቹ ምልከታዎች የተገኙ ውጤቶች ደግሞ ከምልከታ ዘጠኝ እስከ አስራ ሁለት ባሉት ውስጥ በሚከተለው ሁኔታ ተካተዋል።

ሠንጠረዥ 64፦ የመምህራን ረዘም ያለ መመለሻ ጊዜ አሰጣጥ

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ተግባራት | ምልከታ ዘጠኝ | | ምልከታ አሥር | | ምልከታ አሥራ አንድ | | ምልከታ አሥራ ሁለት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ |
| 5 | መምህሯ(ሩ) ለጥያቄ መመለሻ ረዘም ያለ ጊዜ ሰጡ | 3 | 3 | 1 | 2 | 0 | 3 | 1 | 4 |

ከምልከታ ዘጠኝ እስከ አሥራ ሁለት ያሉ የመረጃ ውጤቶች እንደሚያስገነዝቡት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምልከታዎች የመምህራን የቆይታ ጊዜ አሰጣጥ በሁለቱም ፆታዎች ላይ ቅርርቦሽ ተስተውሏል። አስረጅ፦(ሴ=3፡ወ=3 እና ሴ=1፡ወ=2)። በምልከታ 11ና 12 የተካተቱ የምልከታ ውጤቶች ደግሞ ለወንድ ተማሪዎች የተሰጠው የቆይታ ጊዜ ከሴቶች አንፃር ረዘም ያለ መሆኑን ያመለክታሉ።አስረጅ፦(ሴ=0፡ወ=3 እና ሴ=1፡ወ=4)።

ከምልከታ መረጃዎች በተጨማሪ ለመምህራን በቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ አለ። የመረጃው ውጤት ደግሞ በሠንጠረዥ 65 ውስጥ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 65፡- መልስ ለመስጠት ለተቸገሩ ተማሪዎች የሚሠጥ ጊዜ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5 | ተማሪዎች ጥያቄ ተጠይቀው መመለስ ሲቸገሩ የማሰቢያ ጊዜ መስጠት ተገቢ ነው:: | ሴ | 1 | | 1 | 1 | |
| | | ወ | 2 | | 1 | - | |

ተማሪዎች መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ለመመለስ ሲቸገሩ የማሰቢያ ጊዜ መስጠት ተገቢ መሆኑን ከስድስቱ ተጠኝ መምህራን ውስጥ ሦስቱ(አንድ ሴትና ሁለት ወንዶች) እንደሚስማሙ ለመላከቷል። የማሰቢያ ጊዜ መሰጠቱ ተገቢነት ያለው መሆኑን ለመወሰን መቸገራቸውን ደግሞ ሁለት መምህራን (አንድ ሴትና አንድ ወንድ) ጠቁመዋል። በተመጨረሻም ቀሪ አንዲት ሴት መምህር በጉዳዩ ላይ እንደማይስማሙ ገልጸዋል።

ከዚህ በተጨማሪ የመምህራን የቆይታ ጊዜ አሰጣጥ የሚፈትሹ ጥያቄዎች በተማሪዎች መጠይቅ ላይ ይገኛሉ። በመሆኑም ከመጠይቆቹ የተገኙ ውጤቶችን በሚከተለው መንገድ ለማቅረብ ተሞክሯል።

ሠንጠረዥ 66፡- የመምህራን ረዘም ያለ ጊዜ አሰጣጥ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 10 | መምህሬ ጥያቄ ሲጠይቁኝ ለመልስ መስጫ ረዥም ጊዜ ይሰጡኛል:: | ሴ | 56 | 42.4 | 56 | 42.4 | 13 | 9.8 | 7 | 5.3 |
| | | ወ | 26 | 19.7 | 59 | 44.7 | 37 | 28 | 10 | 7.6 |

ከሠንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው መምህራን የጥያቄ መመለሻ ረዥም ጊዜ መስጠታቸው ትክክል እንዳልሆነ 56(42.4%) ሴቶችና 26(19.7%) ወንዶች ጠቁመዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ለጥያቄ መመለሻ ረዘም ያለ ጊዜ በአብዛኛው ከሚሰጣቸው ውስጥ 13(9.8%) ሴት ተማሪዎች እና 37(28%) ወንዶች ይገኛሉ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ለተማሪዎች ተጠኝ መምህራን ረዘም ያለ ጊዜ ለመልስ መመለሻ የሚሰጧቸው ስለመሆኑ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘው መረጃ በሚከተለው መልኩ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 67፡- ለመመለሻ ረዥም ጊዜ ያለመሰጠት ሁኔታ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 22 | መምህሬ ለጥያቄ መመለሻ ረዥም ጊዜ አይሰጡኝም፡፡ | ሴ | 27 | 20.5 | 41 | 31.4 | 29 | 22 | 35 | 26.5 |
| | | ወ | 47 | 35.6 | 50 | 37.9 | 17 | 12.9 | 18 | 13.6 |

ከላይ ከሰፈረው ጥያቄ በተቃራኒው ደግሞ ተጠኝ መምህራን ሁል ጊዜ ለመልስ መመለሻ ረዘም ያለ ጊዜ እንደማይሰጡ 35(26.5%) ሴቶችና 18(13.6%) ወንዶች ሲጠቁሙ 27(20.5%) ሴት ተማሪዎችና 47 (35.6%) ወንዶች ረዘም ያለ ጊዜ አለመስጣቸውን ፈጽሞ ሐሰት መሆኑ አስገንዝበዋል፡፡

በመጨረሻም የመምህራኑን የቆይታ ጊዜ አሰጣጥ ተመጣጣኝነት በሚመለከት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 68፡- የተመጣጣኝ ጊዜ አመዳደብ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ፆታ | የመልስ ቁጥሮችና የመላሾች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | % | 2 | % | 3 | % | 4 | % |
| 17 | መምህሬ ለጠየቁኝ ጥያቄ ተመጣጣኝ የመመለሻ ጊዜ ይመድባሉ | ሴ | 38 | 28.8 | 48 | 36.4 | 33 | 25 | 13 | 9.8 |
| | | ወ | 15 | 11.4 | 37 | 28 | 51 | 38.6 | 29 | 22 |

መምህራን ለጥያቄ መመለሻ ተመጣጣኝ ጊዜ እንደሚሰጧቸው ከጠቆሙ 52 ተማሪዎች ውስጥ 13(9.8%) ሴቶችና 29(22%) ወንዶች ይገኛሉ፡፡ መምህራን የመመለሻ የተመጣጠነ ጊዜ እንደማይሰጣቸው ከገለጹ ተማሪዎች ውስጥ 38(28.8%) ሴትና 15(11.4%) ወንድ ተማሪዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ በተገኘው የመረጃ ውጤት መሠረት በሴትና ወንድ መላሾች መካከል ያለውን ልዩነት በቲ-ስሌት ለማየት ተችሏል፡፡

ሠንጠረዥ 69፡- የመምህራን የቆይታ ጊዜ አሰጣጥ በቲ-ስሌት

| ተጠኝዎች | | አማካይ (Mean) | ቲ-ስሌት | P | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | ፆታ | | | | |
| 132 | ወ | 8.9848 | 3.068 | <0.03 | አለው |
| 132 | ሴ | 7.5985 | | | |

ከወንድና ሴት ተማሪዎች የተገኘው የቆይታ ጊዜ አሰጣጥ ውጤት በሠንጠረዡ ውስጥ ሰፍሯል። በዚህ መሰረት የተጠኝ ወንድ ተማሪዎች አማካይ ውጤት 8.9848 ሲሆን የሴቶች ደግሞ 7.5985 ሆኗል። ይህ በወንዶችና በሴት ተማሪዎች መካከል ያለው አማካይ ውጤት 3.068 የሆነ የስታትስቲክስ ስሌት መረጃ ተገኝቷል። ይህ ደግሞ P<0.03 የሆነ ውጤት አስገኝቷል። የስታትስቲክሱ ነጥብ በወንዶችና በሴት ተማሪዎች ላይ የመምህራን የቆይታ ጊዜ አሰጣጥ ጉልህ የሆነ ልዩነት መስተዋሉን ያስገነዝባል።

የመምህራንን የቆይታ ጊዜ አሰጣጥ ከተመለከቱ መረጃዎች አንጻር ተጠኝ መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው ተመጣጣኝ የሆነ የቆይታ ጊዜ አለመስጠታቸውን ነው። የዚህ ዓይነቱን ወንድ ፆታ ተኮር ትግበራዎችን ማከናወናቸው ደግሞ በመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ላይ ቁልፍ ችግር መኖሩን ያመላክታሉ። እነ Nunan and Lamb (1996:84–87) በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በፈረንሳይኛና ጀርመንኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል መምህራን ተመጣጣኝ የሆነ የቆይታ ጊዜ መጠቀም በመቻላቸው ውጤታማ ሲሆኑ መቻላቸውን ከሚያሳዩት የጥናት ውጤት ጋር አልተጣጣመም።

እንዲሁም ከመረጃዎች ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው መምህራን ለተማሪዎች መልስ መመለሻ ጊዜ የሚመድቡ ቢሆንም የቆይታ ጊዜው ከአንዱ ፆታ ወደ ሌላ ፆታ ልዩነት መንፀባረቁን አመላክቷል። ይኸውም መምህራን ለወንድ ተማሪዎች ረዘም ያለ ጊዜ እንደሚሰጡ መረጃዎች ጠቁመዋል። እነ Santrock (2001:188)፣ Riley (1997:7) እና Rowe (1986:44-48) የቆይታ ጊዜ ለመማር ማስተማር ሂደት የሚያበረክተው ጠቀሜታ የጎላ ነው። ይኸውም የመምህራን አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች የተመጠኑ እንዲሆኑና ተማሪዎች ተሳትፎ እንዲኖራቸው የማድረግ ሃይል አለው። ይሁን እንጂ በስፔን በተካሄዱ ጥናቶች የተገኘው ውጤት መምህራን ተማሪዎቻቸውን ጥያቄ ሲጠይቁ ለወንድ ተማሪዎች የበለጠ የቆይታ ጊዜ መስጠታቸውን ካረጋገጡት የጥናት ውጤት ጋር ይደጋገፋል።

በአጠቃላይ ከምልከታ፣ ከጽሑፍ መጠይቅና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሴትና ወንድ ተማሪዎቻቸውን የሚያስተናግዱበት መንገድ የተለያየ መሆኑን ያስገነዝባሉ። ለዚህም ከአሥራ ሁለቱ ምልከታዎች ማረጋገጥ እንደተቻለው ተጠኝ መምህራኑ የበለጠ ትኩረት የሚያደርጉት ወደ ወንድ ተማሪዎች እንደሆነ ያሳያሉ። እነዚህ ትኩረቶች ደግሞ ከምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ፣ ከጥያቄ አጠያየቅ፣ ከቆይታ ጊዜና ከተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ አንፃር ተፈትሸዋል። ለመምህራን በቀረቡ የጽሑፍና የቃል ጥያቄዎች ተማሪዎቻቸውን በእኩል መንገድ እንደሚይዙ የገለጹበት ሁኔታ በምልከታዎች ሲተገበሩ አልተስተዋለም። የተጠኝ መምህራን ምላሽ ከአተገባበራቸው ጋር ያለመዛመዱ ሁኔታ የግንዛቤ ክፍተት መኖሩን ፍንጭ ይሰጣል። በተጨማሪም በሁለቱ ፆታዎች የሚገኙ ተጠኝ ተማሪዎች የመምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ፣ የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት፣ የቆይታ ጊዜ አመዳደብና የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ ከቱ-ስሌት አንጻር ተፈትሿል።

ከዚህ በመነሳት ከምጋቤ ምላሽ፣ የጥያቄ አጠያየቅ፣ የቆይታ ጊዜ አመዳደብ አኳያ ከስታትስቲካዊ ስሌት ጉልህ ልዩነት መኖሩ ታይቷል። ከዚህ ባሻገር ደግሞ ከተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ አንፃር በሴትና በወንድ ተማሪዎች ምላሽ ላይ ልዩነት መኖሩ ቢረጋገጥም በቱ- ስሌት ግን ልዩነቱ የጎላ አለመሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል። እነዚህ ውጤቶች ደግሞ በመምህራን ለሴትና ለወንድ ተማሪዎቻቸው የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ላይ ልዩነት መኖሩን አመላካች ናቸው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበራቸውን መፈተሽ ነው። በዚህ መሠረት ጥናቱ እንዲመልሳቸው በመጀመሪያ የተነሱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ቀጥሎ የሰፈሩት ነበሩ።

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ ፆታ ግንዛቤ ምን ያህል ነው?
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝና የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን ይመስላል?
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለሴትና ለወንድ ተማሪዎቻቸው ያላቸው ትኩረት ምን ያህል ይመሳሰላል? ምን ያህልስ ይለያያል?
4. ልዩነት ካለ ልዩነቱ (ከምጋቤ ምላሽ፣ከጥያቄ አጠያየቅ፣ከተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ፣ ከቆይታ ጊዜ አመዳደብ ወዘተ አንፃር) ምን ይመስላል?
5. የተስተዋለው የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ልዩነት በተራ ቁጥር 4 ከተዘረዘሩት ተላውጦዎች ውስጥ በየትኛው ላይ ጉልቶ ይታያል?

የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ምንነትና የክፍል ውስጥ አተገባበርን በሚመለከት የመስኩ ምሁራን በጥናት ያረጋገጧቸው ንድፈ ሐሳቦች በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ተካተዋል። በዓላማው ሥር የሠፈሩትን ጥያቄዎች በአግባቡ መመለስ እንዲቻል በመጀመሪያ ተጠኝዎችና የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተመርጠዋል። ተጠኝዎቹ ባህር ዳር ከተማ በጣና ሐይቅ፣ ግዮን እና ፋሲሎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል በ1999 ዓ.ም የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው፤ ብዛታቸውም ስድስት ነው። ተጠኝ መምህራኑ የሚያስተምሩባቸው 12 ክፍሎች ለምልከታ ተመርጠዋል። በተጨማሪም 264 የሚሆኑ ተማሪዎች በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል። ከተጠኝዎቹ መረጃ ለመሰብሰብ ምቹ ሆነው የተመረጡ መሣሪያዎች ምልከታ፣ የጽሑፍ መጠይቅ (የተማሪዎችና የመምህራን) እና ቃለ መጠየቅ ናቸው። ምልከታው መጠናዊ (Quantitative) ወይም ቀደም ብሎ የተዘጋጀ የምልከታ ቅፅ (Observation Checklist)ነው። በምልከታ ቅፁ ውስጥ ትኩረት የተሰጠባቸው ጉዳዮች አስቀድመው በፈታሽ ጥናት (Pilot Study)

ወቀት ተለይተዋል። ከምልከታው በኋላ ለመምህራን ቃለ መጠይቅ ተደርጓል። በተጨማሪም የጽሑፍ መጠይቅ በተማሪዎችና በመምህራን ተሞልቷል።

ለጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ትንተና ተካሂዷል። ትንተናውም ዓይነታዊና መጠናዊ (Qualitative and Quantitative) ዘዴዎችን ተጠቅሟል። በጥናቱ የተካተቱ ተማሪዎች ቁጥር ወደ መቶኛ ለውጦ ለማቅረብ በቂ በመሆኑ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በመቶኛ እየተለወጠ ቀርቧል። እንዲሁም ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኙ ውጤቶችን ከፆታቸው አንፃር ለማየት ተሞክሯል። በዚህም በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የተገኘው ውጤት ጉልህ ልዩነት ያለው ስለመሆኑ በስታትስቲካዊ ቲ-ስሌት ተፈትሿል። ሌሎች በምልከታና ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ ተገኝተው ለስሌት አመቺ የሆኑ መረጃዎችም በመጣኝ ትንተና ዘዴ ተተንትነዋል። በክፍት የጽሑፍና የቃል ጥያቄዎች ለተገኙ መረጃዎች ደግሞ ዓይነታዊ ትንተና ዘዴ ተግባር ላይ ውሏል።

በአጠቃላይ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በምልከታ፣ በጽሑፍ በመጠይቅ እና በቃለ መጠይቅ አማካይነት ተሰብስበው አስፈላጊው ትንተናና ማብራሪያ ከተደረገባቸው በኋላ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል።

### 5.1.1 የመምህራንን የጥያቄ አጠያየቅ ብልሃት በሚመለከት

ሀ. መምህራን በርካታ ጥያቄዎችን ለወንድ ተማሪዎች ሲሰጡ ታይተዋል።

ለ. መምህራን የተማሪዎችን ስም እየጠሩ የመጠየቅ ልምዳቸው አነስተኛ መሆኑ ተንፀባርቋል፤ስም ያለመጥራቱ ሁኔታ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ወደ ሴቶች አመዝኖ ታይቷል።

ሐ. መምህራን ጥያቄውን ካቀረቡ በኋላ የተማሪዎችን ስም እየጠሩ የማስተናገድ አወንታዊ የአጠያየቅ ስልት በአብዛኛው እንደማይተገብሩ ተረጋግጧል። በዚህም የሴት ተማሪዎችን ስም ከጥያቄ በፊት አስቀድሞ የመጥራት ሁኔታ መኖሩን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል።

### 5.1.2 የመምህራንን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በሚመለከት

ሀ. መምህራኑ ምንም ምጋቤ ምላሽና አልፎ አልፎ ግን አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች በተለይ ለሴት ተማሪዎች መስጠታቸውን ለማወቅ ተችሏል።

ለ. መምህራን ለወንድ ተማሪዎች በአብዛኛው የሰነዘሩት ማበረታቻ የሠሩትን ተግባራት መሠረት ያደረገ ሲሆን የሴት ተማሪዎች ደግሞ ሥነ-ምግባራቸውን መሠረት ያደረገ ነበር።

ሐ. መምህራን አወንታዊ ምጋቤ ምላሾችን ለወንድ ተማሪዎች በተደጋጋሚ ሲሰጡ ታይተዋል።

መ. መምህራን አስተያየቶችን ለወንድ ተማሪዎች በአብዛኛው በክፍል ውስጥ ሲናገሩ፣ ለሴት ተማሪዎች ደግሞ በግል የመንገር ሁኔታ አሳይተዋል።

### 5.1.3 የመምህራንን የቆይታ ጊዜ አመዳደብ በሚመለከት

ሀ. መምህራን ለተማሪዎች መልስ መመለሻ የተመጣጠነ ጊዜ አይሰጡም።

ለ. መምህራን ለወንድ ተማሪዎች ረዘም ያለ የማሰቢያ ጊዜ ሲሰጡ ለሴቶቹ ግን ይህንን ይነፍጋሉ።

### 5.1.4 የመምህራንን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ በሚመለከት

ሀ. መምህራን በተማሪዎቻቸው ምላሽ ላይ ጣልቃ ይገባሉ። ሁኔታው አንፃራዊ በሆነ መልኩ በሴቶች ተሳትፎ ላይ ጐልቶ ተንፀባርቋል።

ለ. የመምህራን የተሳትፎ ዕድል አሰጣጥ የተማሪዎችን አቀማመጥ መሠረት ያደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፤ መምህራን ፊት ለተቀመጡ ሴት ተማሪዎችና ፊትም ሆነ ኋላ ለተቀመጡ ወንድ ተማሪዎች የተሳትፎ ዕድል በአብዛኛው ይሰጣሉ።

ሐ. መምህራን እጅ ለማያወጡ ወንድ ተማሪዎች በርከት ያለ የተሳትፎ ዕድል ይሰጣሉ።

መ. መምህራን ሴትና ወንድ ተማሪዎችን በቡድን ሥራ ያሳትፋሉ።

ጠቅለል ባለ መንገድ ተጠኚ መምህራን ሥርዓተ ፆታን ተገንዝበው በክፍል ተግባራዊ ማድረግ ላይ ደካማ ናቸው። ለዚህም መምህራን ሴትና ወንድ ተማሪዎችን የሚይዙበት መንገድ የተለያየ ሊሆን ችሏል። በመሆኑም የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ልዩነት ከአራቱ ተላውጦዎች አኳያ ከምጋቤ ምላሽ አንፃር ጉልህ ችግር አለበት።

## 5.2 አስተያየት

ከጥናቱ ውጤት፣ማብራሪያና መደምደሚያ መረዳት እንደተቻለው የመምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝና በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚታይ አተገባበር በዘመኑ የፆታ እኩልነትን ለማምጣት የሚደረገውን እንቅስቃሴ የተከተለ አይመስልም።

በአጠቃላይ የቋንቋ መምህራን የሥርዓተ ፆታ አያያዝ ግንዛቤ መኖር በመማሪያ ክፍል ትግበራ ላይ ውጤታማነቱ ወሳኝ በመሆኑ አጥኝዋ የሚከተሉትን አስተያየቶች በመፍትሔነት አቅርባለች፡፡

ሀ. መምህራን አበረታች የሆኑ ምጋቤ ምላሾችን በሁለቱም ፆታ ለሚገኙ ተማሪዎች በእኩል ቢሰነዝሩ፤

ለ. መምህራን የተማሪዎችን ስም ከመጥራታቸው በፊት ጥያቄ የመጠየቅ ልምድ ቢያዳብሩ፤

ሐ. መምህራን ለተማሪዎቻቸው የመልስ መመለሻ ተመጣጣኝ የሆነ ጊዜ ቢመድቡ፤

መ. መምህራን ለሴትና ለወንድ ተማሪዎቻቸው እኩል የሆነ የተሳትፎ ዕድል ቢሰጡ፤

ሠ. መምህራን ስለ ሥርዓተ ፆታ አያያዝ ያላቸውን ግንዛቤ ለማዳበር የሥራ ላይ ሥልጠና የሚኖርበት ሁኔታ ቢመቻች፤

ረ. ሥርዓተ ፆታን በሚመለከት በየትምህርት ቤቶች ያለውን እንቅስቃሴ በመከታተል የሚመለከታቸው ክፍሎች እገዛ ቢያደርጉ፡፡

## ሙዳየ ቃላት

Awareness = ግንዛቤ

Sex bias = የፆታ አድልዎ

Biological = ሥነ ፍጥረታዊ

Body language = አካላዊ ቋንቋ

Comment = አስተያየት

Consciously = ሆነ ተብሎ

Encouragement = ማበረታቻ

Feed back = ምጋቤ ምላሽ

Frequency = ድግግሞሽ

Gaze = በአትኩሮት መመልከት

Hormone = ህብለ-በራሄ

Personality = ስብዕና

Reciprocal = ተራክቧዊ

Roles = ሚናዎች

Self-esteem = ለራስ የሚሰጥ ግምት

Socio-cultural = ማህበረ-ባህላዊ

Static = የማይለወጥ (ቋሚ)

Stereotype = ልማዳዊ አድሏዊ ባህርያት

Symbolic = ትዕምርታዊ

Variables = ተላውጦዎች

Verbal interaction = ቃላዊ መስተጋብር

Universal = ሁለንተናዊ

# ዋቢ ጽሑፎች


ሂሩት ካሣው (1997) "አዲስ አበባ ክልላዊ መስተዳድር በሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሴትና የወንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።

በላይ ሰይድ (1992) "የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተዛሄደ ጥናት" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።

ሰብለወንጌል ታደሰ (አርታዒ።)። (1997) <u>የሴቶች ማኒፌስቶ።</u> አዲስ አበባ፣ በኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር።

ትምህርት ሚኒስቴር፣ (1990) "የጀንደር መግለጫዎች በመጻሕፍትና በመማር ማስተማር ሂደት፣ ለአሰልጣኞችና ለመጽሐፍት አዘጋጆች የተዘጋጀ ማኑዋል"። ሚያዚያ 1990 (ያልታተመ)።

<u>የመምህራን ሚና በትምህርት ሥልጠና ሂደት</u> (1998) አዲስ አበባ። (አሳታሚ ያልተጠቀሰ)

የትምህርት ልማት አካዳሚ (ዓ.ም ያልተጠቀሰ) <u>ሥርዓተ ፆታን ያገናዘበ የክፍል ውስጥ መስተጋብር</u>። አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ማተሚያ ድርጅት።

ፋንቱ ደምሴ (1989) "የፆታ ልዩነት አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና፣ በእንጦጦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች አጠቃላይ የቋንቋ ብቃት ላይ የተካሄደ ጥናት" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።

Alem Habtu (2003) "Gender Gap in Ethiopian Education." <u>The Annual Journal of Ethiopian Women Lawyers Association.</u> Issue 4, Addis Ababa: Ethiopia Women Lawyers Association.

Alexander, R.(1997) <u>Policy and Practice in Primary</u> Education. Second Edition. London: Florence type.

Allwright, D.(1988) <u>Observation in The Language Classroom</u>. London: Longman.

Andersen, M.L.(1988) <u>Thinking About Women: Sociological Perspective on Sex and Gender</u>. Second Edition. London: Mmillan Publishing Company.

Anderson, M.L. and Collins,H. (1998) Race, Class And Gender. Third Edition. Washingto: An International Thomson Publishing Company.

Anker, R. (1998) Difference Between Sex and Gender. In Gender and Jobs. Oxford International Labour Organization.

Annan-Yao,E. and et al (2004)Gender, Economics and Entitlements in Africa. Dakar: CODESRIA.

Arnold, J. (Ed.). (1999) Affect In Language Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

Ashcroft, K. and Foreman-Peck, L. (1994) Managing Teaching and Learning In Further and Higher Education. London: Biddles Ltd.

Ayim, M. and Hauston, B. (1996) "A Conceptual Analysis of Sexist Education." In Diller, A. and Houston, B. The Gender Question in Education: Theory, Pedagogy and Politics. Colorado: West view Press, Inc.

Bailey, K .D. (1994)Methods of Social Research. Singapor: The Free press.

Bennett, S.K. (1982) "Students Perceptions and Expectation For Male and Female Instructors: Evidence Relating to The Question of Gender Bias in Teaching Evaluation." Journal of Educational Psychology. Vol 74, No 1, Feb 1982 PP 170-176. The American Psychological Association.

Birch, A. and Malim, T. (1988) Developmental Psychology. New-Delhi: Macmillan.

Blood, P. et al. (1998) "Understanding and Fighting Sexism: A Call to Men." In Anderson, M.L. and Collins, P.H. Race, Class and Gender. p.181. Washington: Thomson Publishing Company.

Borich, G.D. and Tombari, M.L. (1995) "Gender Difference And Schooling." In Educational Psychology: A Contemporary Approach: Oxford: Harper Collins College Publishers.

Brainard, E. (2002) "Classroom Management: Seventy Three Suggestions For Secondary School Teachers." In Schultz, F. (Ed.). Education.. Guilford: Mc Graw-Hill.

Brophy, J.E. (1983) "Research on The Self –Fulfilling Prophecy and Teachers Exportations." Journal of Educational Psychology. Vol. 75, No. 1, Feb 1983. The American Psychological Association.

Brown, H.D. (1994) Principle of Language Learning and Teaching. New York: Prentice Hall.

Bukatko,D. and Daehler, M.W. (1992) "Sex Roles". Child Development. New Jesse:. Houghton Mifflin Company.

Byrne, D. (1987) Techniques for Classroom Interaction. New York: Longman.

Callaham, J.F. and Clark, L.H. (1988) Teaching In The Middle And Secondary Schools Planning For Competence. New York. Mc Millen publishers Company.

Clark, A. and Trafford, J. (1996) "Return To Gender: Boys' and Girls' Attitudes and Achievements." Language Learning Journal. No 14 Cambridge: Cambridge University Press.

Clegg,S. (1998) "Equity in the Classroom. Towards Effective Pedagogy for Girls and Boys." Gender and Education. Australia: Carfax . Vol 10, No4, PP 465-468.

Clifton, R. et al. (1986) "Teachers' Expectations of Junior High School Students." Sociology of Education. Vol 59, No 1, Jan. 1986 Washington Dc: The American Sociological Association.

Coates, J. (1993) Women, Men and Language. New York: Longman.

Cole, P.G. and Chan, L.K.S. (1994) Teaching Principles and Practice. Second Edition. New York: Prentice Hall.

Connolly, P. (1998) Racism, Gender Identities And Young Children: Social Relation In A Multi-Ethic, Inner-City Primary School. London: Antony Rowe Ltd.

Coultas, A. (2003) Language and Social Contexts. London. Taylor & Francis Group.

Cruickshank, D.R. et al. (1995) The Act of Teaching. Toronto: Mc Graw-Hill, Inc.

Danayt Belay (2006) "A Study on Gender Differences in Teacher-Student Interaction in EFL Classrooms: With Special Reference to Four Private High Schools In Addis Ababa." Department of Foreign Language and Literature (Unpublished) MA Thesis.

Datnow, A. and Hubbard, L. (Eds.). (2002) Gender In Policy And Practice: Perspectives on Single-Sex And Coeducational Schooling. New York: Routledge Flamer.

Delamont, S. (1994) "Sex Roles In The Formative Years." In Pollard, A. and Bourne, J. Teaching And Learning In The Primary School. London: Taylor & Francis Group.

Dheram, P.K. (1995) "Feedback As a Two- Bullock Cart." ELT Journal. Vol 49/2 April 1995 London: Oxford University Press.

Diller, A. and Hoston, B (1996) A Conceptual Analysis of Sexism and Sexist Education. Clorado:West view Press, Inc.

Disch, E. (1997) Reconstructing Gender: A Multi Cultural Anthology. Toronto: Mayfield Publishing.

Eckert, P. and Mc Connell-Ginet, S. (2003) Language and Gender. Cambridge: Cambridge University Press.

Elliott, S.N. and et al (2000) Educational Psychology: Effective Teaching, Effective Learning. New York: Mc Graw-Hill Companies.

Fackson, D. and Salisbury, F. (1996) "The Historical Foundations of Gender and Education Work." Gender And Education. Vol 8, No PP 105-114. Australia: Car fax.

Feldman, R. S. (1996) "Gender and Sex." In Understanding Psychology. New York: Longman.

Feldman, R.S. and Anderw, J.T. (1982) "The Teacher And The Student As Pygmalion's: Joint Effects Of Teacher and Student Expectations." Journal of Education. Vol 74, P217. The American psychological Association

Flanders, N.A. (1971) "Intent, Action and Feedback. A Preparation for Teaching." In Storm, R.D. (Ed.). Teachers and The Learning Process. New Jersey: Prentice-Hall, Inc.

Fontana, D. (1995) Psychology For Teachers.. Chatham, Mc Milan.

Galloway, C.(1971) "Non Verbal Communication." In Strom, R.D. (Ed.). Teachers and The Learning Process. New Jersey : Prentice-Hail, Inc.

Genet Zewdie(1998) Women In Education: A study of The Academic performance and participation of Female students In the High Schools of Addis Ababa Region. Vol 6, No1. Addis Ababa: IER Flabeau.

Ghosh, R. and Tarrow, N. (1993) "Multiculturalism and Teacher Educators:" Comparative Education. Vol 29, No1. Abingdon: Carfax Publishing Company.

Grant, C.A. and Sleeted, C.E. (1999) "Race, Class, Gender and Disability in the Classroom." In Banks, J.A. and Banks, C.A. (Eds.). Multicultural Education. Issues and perspectives. Third Edition. PP 61-81. Toronto: John Wiley & Sons, Inc.

Greenberg, J.S. (1996) "Communication," In Comprehensive Stress Management. Sydney: Brown & Benchmark.

Habtamu Wondimu and et al (2004) Gender and Cross cultural Dynamics In Ethiopia: The Case of Eleven Ethnic Groups. Addis Ababa: CERTWID.

Hatchell, H. (1998) "Girls' Entry into Higher Secondary Sciences." Gender and Education. Vol 10, No 4, PP 375-388. Australia: Carfax.

Hayes, N. (1993)A First Course In Psychology. Croatia: Thoman Nelson and Sons Ltd.

Hirut Tefere (2002) "Violence Against women From Gender and cultural perspectives." Reflections: No 7 Documentation of Panos Ehtiopia: Master printing press.

Jabre, B. (1988) Women's Education in Africa. Paris: Unesco-Unicef.

Kagan, C. and Tindall, C. (2003) Feminist Approaches To Counselling Psychology. New Delhi: SAGE Publications.

Katapa, R.S and Swilla, I.N. (1999) "Factors Contributing To Girls' Poor Performance." Eastern Africa Social Science Research Review. Vol, XV, No1, Jan 1999 OSSREA.

Kenneth,G.T.and William,C. (1982) "Relationship Between Classroom Process Variables And Middle School Science Achievement." Journal of Education. Vol 74, P 414.

Kramer, K. (Ed.). (1991) The Sociology of Gender, New York: St. Martin's Press.

Lindsey, L.L. (2005) Gender Roles: A Sociological Perspective.. New Jersey: Prentice Hall.

Lynch, T. (1996) Communication In The Language Classroom. Hong Kong: Oxford University Press.

Makhubu, L.P. (2000) The Right to Higher Education and Equal Opportunity Particularly for Women: The Challenge of Our Time. Dakar: UNESCO BREDA.

Malamah- Thomas, A. (1991) Classroom Interaction. Oxford: Oxford University Press.

Markos Ezra and Seyoum Gebre Selasssie (Eds.). (1998) "Hand Book on population And Family Life Education For Secondary School Teachers In Ethiopia." Addis Ababa: Institute of Curriculum Development and Research.

Matlin, M.W. (1996) The Psychology of Women: Third Edition. Tokyo: Harcourt Brace College Publishers.

Mortimore, P. (Ed.). (1999) "Teachers' Beliefs About Learners." Understanding Psychology and Its Impact on Learning. Gateshead: Ath Enaeum Press.

Naiman, N. and et al (1996) "Differential Teacher Treatment." The Good Language Learner. PP 180-182.Canada: Multilingual Matters Ltd.

Nunan, D. and Lamb, C. (1996) The Self –Directed Teacher Managing The Learning Process. Cambridge: Cambridge University Press.

Odaga, A. and Henveld, W. (1995) Girls and Schools in sub-Saharan Africa: From Analysis to Action. Washington Dc: World Bank.

Olson, D.H, (2000) Gender Roles. In Marriage and The Family Diversity and Strengths. Third Edition. Toronto: May field Publishing Company.

Papalia, D.E. and et al (1999) A Child's World. Toronto: Mc Graw- Hill.

Perrott, E. (1982) Effective Teaching: A Practical Guide To Improving Your Teaching. Malaysia: Longman.

Plessis,D.J. et al. (2002) In My Classroom A Guide To Reflective Practice. American Institutes for Research. USAID.

Plewis, I. (1997) "Inference About Teacher Expectations From National Assessment At Key Stage one." Journal of Educational Psychology. Vol 67, Part 2, June, 1997 Glasgow: Bell and Bain.

Rhona, S. and et al (1982) "Student Perceptions of Differential Teacher Treatment In Open and Traditional Classroom." Journal of Educational Psychology. Vol 74, No1, PP 678-680. The American Psychological Association.

Rich, E. and Brown, D. (2002) "Gender Positioning As Pedagogical Practice In Teaching Physical Education." In Penner, D. (Ed.). Gender and Physical Education. New York: Routledg.

Richards,J.C. and et al (1992) "Dictionary of Language Teaching and Applied Linguistics." Journal of Educational Psychology. Vol 73, No 5, PP 681-691. London: Longman.

Riley, N.E .(1997) "Gender, Power and Population Change." Population Bulletin. Vol.57,No1. Washing ton Dc: Reference Bureau, Inc.

Rivers,S. (1989) Teaching Foreign Language Skills. Chicago: Chicago University Press.

Rosenthal, R. (1971) "Teacher Expectation and Pupil Learning." In Strom, R,D. (Ed.). Teachers and The Learning Process. New Jersey: Prentice –Hall, Inc.

Rowe, M.B. (1986) "Wait Time: Slowing Down May Be A way of Speeding up!." In Lasley, T. Journal of Teacher Education. Vol xxxvll, No 1. California: American Association of Colleges For Teachers Education.

Sadker, M. and et al (1999) "Gender and Educational Equality." In Banks, J.A. And Banks, C.A. (Eds.). Multicultural Education. PP 131-147 Toronto: John Wiley & Sons, Inc..

Salisbury, J. and Riddell, S. (2000) Gender Policy and Educational Change. London: Taylor & Francis.

Santrock, J.W. (2001) Educational Psychology. California: Mc Graw Hill Companies.

Schultz, F. (Ed.). (1997) The AAUW Report: How Schools Shortchange Girls Overview. Guilford: Brown & Benchmark.

Schumck, P. et al. (2002) "Studying Gender Consciousness In Single-sex And Coeducational High Schools." Gender, Policy And Practice. PP 196-210 New York: Rouhedge Flame.

Shaffer, D.R. (1994) Social and Personality Development. California: Brooks/Cole Publishing Company.

Shuell,T.J. (1993) "Teaching and Learning In a Classroom Context." In Berliner, D.C. and Calfee, R.C. (Eds.).Handbook of Educational Psychology. Toronto: Prentice Hall International.

Stein, J. et al. (1994) "The Influence of Schools on Gender Roles." Psychology Science, Behavior and Life. Third Edition. Tokyo: Harcourt Brace College Publishers.

Subbo, W. (2002) "The Conceptualization Of Gender." Perspectives on Gender Discourse: Gender and Constitutions Making in Kenya. Nairobi: Heinirch Boll Foundation.

Sullivan, P. and Kramsch, C. (1996) "Appropriate Pedagogy." ELT Journal. Vol. 50, No. 3, July 1996. London: Oxford University Press.

Sunderland, J. (1992) "Gender in The EFL Classroom." ELT Journal. Vol 461, January 1992. Oxford: Oxford University Press PP 81-91.

______(Ed.). (1994) Exploring Gender: Questions And Implications For English Language Education. Cambridge. Prentice-Hall.

______(1994) "Differential Teacher Treatment-By Gender In The Classroom: Using Ex-Participants Perspectives." In Exploring Gender: Questions And Implications For English Language Education. Cambridge. Prentice-Hall.

Suzanne, W. (2002) The Oxfam Gender Training Manual. Tokyo: Oxfam Print Unit.

Thorndury, S. (1996) Teachers Research Teacher Talk. Vol 50, No 4, Oct 1996. London: Oxford University Press.

UNESCO (2003) Gender and Education for All: The Leap To Quality. France: Grapho Print.

Valian, V. (1998) Why So Slow?: The Advancement of Women: England: MTI Press.

Wilson, H.T. (1989) Sex and Gender: Making Cultural Sense of Civilization. Netherlands: E.J.Brill.

Wood, S.E. and et al (2005) The World of Psychology. Sydney: Pearson Education, Inc.

Yonas Admassu (Ed.).(2003) "Understanding Gender." Reflections: Documentation of the Forum on Gender. sNumber 9. Addis Ababa: Master printing Press.

# አባሪዎች

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# አባሪ 1

## የመቅረፀ - ምስል ቀረጻ አንድ

መ = ባለፉት ክፍለ ጊዜያት «የመንደሩ መርፌ ወጊ» የሚለውን ምንባብ አጠናቀናል፤ ዛሬ ደግሞ ስለ ግጥም እንነጋገራለን። ግጥም ምንድን ነው?

ተወ$_1$ = አጭር የሆነ ፍሬ ሃሳብ ያለው ፣ በትንሽ ነገር ብዙ ማስተላለፍ የሚችል።

መ = (የተማሪውን መልስ ደግመው ተናገሩ)

ተሴ = በስንኝ የሚቋጠር ፣ ሙዚቃዊ ቃና ያለው አነባበብ ነው።

መ = (እሽ!በማለት ደግመው ተናገሩ)

ተወ$_2$ = ስሜታዊ የሆነ አነጋገር ነው።

መ = ስሜት ሰጪ የሆነው ቁጥብና

ተወ = ቤት የሚመታ

መ = ቤት መምቻ፣ ቤት መድፊያና ሐረግ ያለው። የግጥም ዓይነቶችን የሚነግረኝ ?

ተወ$_3$ = የወል ቤት ፣ ሰንጎ መገን ... ምናምን

መ = ምናምን ይባላል? በቋንቋችን ምናምን አይባልም ፤ ፀያፍ ነገር ፣ ማምታቻ ነው።

ተወ = ቡሄ በሉ።

መ = አዎ ! ቡሄ በሉ.... እሽ እነዚህን በምንድን እንለያቸዋለን ?

ተወ = በዜማውና በአነባበቡ

መ = መለያ ሊሆን ይችላል ፤ ነገር ግን ዋና መለያቸው ምንድን ነው ?

ተወ$_4$ = የሐረጉ ወይም የስንኙ ብዛት ማለት ባለ 12 ፣ ባለ 6

መ = ምንድን ነው ያ ታዲያ ?

ተወ$_5$ = የስንኙ ብዛት

መ = ተቃርባችኋል ፤ቀለም የሚባል ነገር ታውቃላችሁ ? ...ቅድም ልጁ ማንሳት ሞክሮ ነበር። እያንዳንዱ የወል ቤት ግጥም በስንኝ ፣ በሐረግ ስንት ቀለም አለው ?

ተወ$_6$ = በስንኝ 12 በሐረግ 24

መ = በስንኝ 12 በሐረግ 6 አለው። በዝርዝር ባናይም ሰንጎ መገን ስንት ቀለም አለው ?

ተወ$_7$ = ስድስት

መ = ሌላ ተማሪ

ተወ = አምስት

መ =አምስት አምስት አሥር የቡሄ በሉ ቤት ግምጥ ደግሞ 3(4)ቀለም አለው፡፡ ስለዚህ ቀለም ማለት ምንድን ነው ? አረንጓዴ ፣ቢጫ ፣ ቀይ ነው ?

ተወ =አዎ!

መ =ያ በሌላ ነገር ነው፡፡ በግጥም ቀለም ምን ማለት ነው?

ተወ =በፊደል ውስጥ የመጨረሻው ሆሄ አንድ ዓይነት ሲሆኑ ይመስለኛል፡፡

መ =አጠራጣሪ ሃሳብ ነው? ... ለማንኛውም ጥሩ አንተ የራስህን ሞክረሃል ሌላ?

$ተወ_8$ =ሐረጎች ላይ ተደራራቢ ፊደላት አንድ ዓይነት ሲሆን ነው፡፡

መ =ጥሩ ሙከራችሁ ጥሩ ነው፡፡ ... ተረግጠው የሚነበቡ ተነባቢ ድምጾች ናቸው፡፡... በተለይ ሳድስት ፊደላት ... ለመሆኑ ስንተኛው ፊደላት ናቸው?

ተወ =ስድስተኛ

መ =ሳድስ ፊደሎች በቃል ውስጥ እንደአገባባቸው ተጭነው በሚነበቡበት ጊዜ ቀለም ሆነው ይቆጠራሉ፡፡ በቀለም ቆጠራ ጊዜ አደናጋሪ ሁኔታ ያለ ከነማን ላይ ነው?

ተወ =ሳድስ ፊደላት ላይ

መ =አዎ! ... የስንኝ እኩሌታ ምን በመባል ይታወቃል ? እኩሌታ ምን ማለት ነው?

$ተወ_9$ =ግማሽ

መ =ያ ማለት ደግሞ

ተወ =ሐረግ ነው፡፡

መ =መነሻ ሐረግ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ግጥም ስንት ስንኞች አሉት ? አንቺ !

ተሴ =የመጀመሪያው መስመር ነው? ሁለት ስንኞች አሉት፡፡

መ =ሁኔታችሁን ስለተረዳሁት ነው፤ ... ሌላ! እዚያ ኋላ አንቺ!

ተሴ =ሁለት

መ =የትኛውና የትኛው ?

ተሴ =አርበኞች ... የሚለው መስመርና የሚቀጥለው መስመር

መ =ልክ ነው፡፡ሁለት ስንኞች አሉት፡፡ ለማታውቁት ስንኝ የሚባለው አንድ የግጥም መስመር ነው፡፡ አንድ ግጥም ቢያንስ ስንት ስንኞች አሉት? እጅሽን አወጣሽ! መልሽ?

ተሴ = ሁለት

መ =እንደ ግጥሙ ከዚያ በላይ ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ አንድ ግጥም ስንት ሐረጎች አሉት? እሽ አንተ እራስህ አይዞህ ! መካከል ላይ ያለሽው

ተወ =ሁለት

መ =አንድ ግጥም ለምሳሌ የወል ግጥም ቢያንስ ሁለት ሐረግ ይኖሩታል እንዴ? ሌላ

ተወ =አራት

መ =ሁለቱ መነሻ ሲሆኑ ሁለቱ መድረሻ ሐረግ ይሆናሉ። ከግጥሙ የትኞቹ ናቸው ሐረጎች?

ተሴ =አርበኞች መሞትን /ማን አስተማራቸው ፣

ታላቁ ጴጥሮስ ነው / ባርኮ የሰጣቸው።

መ =በአንድ ትንፋሽ የሚወጣ ሐረግ ነው። የሰንኀ መገን ቤት ምንድነው ?

ተወ =ሰምና ወርቅ ፣ ደራሲው የሚፅፈውን ነገር የማይጨርሰው ከሆነ…

መ =ጥሩ አንተ! የራስህን ሞክረሃል። ሌሎች… አንቺ! ሌላ ነገር ነው የምታወሩ ?

ተወ =ሰንኀ መገን ግጥም የምንጠቀመው አንድ አጋጣሚ ሲኖር ነው።

መ = ጥሩ! ምን ዓይነት አጋጣሚ ነው?

ተወ =አንድ ስሜት ሲሰማ

መ =ምን ዓይነት ስሜት ?

ተወ =ደስታ፣ አዲስ ነገር ሲፈጠር

መ =ከአንድ ነገር ጋር በአብዛኛው የተያያዘ ነው።… ከወኔ ጋር… ፉከራ የሚያውቅ?

ተወ =አባትየው ነው ዳጉሳ ዘሪ ፣

ልጅየው ደርሷል ጥይት መንዛሪ።

መ =ጥሩ ነው! ቡሄ ግጥምስ?

ተወ =የባህል ጭፈራ

መ =እነማን ናቸው ጭፈራዎች?

ተወ =የልጆች ግጥም

መ =አዎ!… እስኪ የልጆች ግጥም የሚነግረኝ ?

ተወ =ሆያ ሆየ ፣ ሙሻ ሙሽ ፣…

መ = አዎ! (ጭፈራውን ተናገሩ) ብዙ ጊዜ ቡሄ በሉ ግጥም ባለ 4 ቀለም ነው። ይህን መሠረት አድርጋችሁ መጽሐፋችሁ ላይ የምትሰሩት ልንገራችሁ ገጽ 133

ተማሪዎች በጋራ = ጻፍልን አሉ

መ =እንደገና ቁጥር መማር እንግባ እንዴ? ገጽ 133 ግጥሙን በማንበብ ገጽ 134 አንብቦ መረዳት ተራ ቁጥር 2 (እንዲህ ዓይነቷ ነች ፪) ፣ ክፍል ሁለት ገጽ 135 ስዋስውን የቤት ሥራ ስሩ። እስካሁን ከተነጋገርነው ጥያቄ ያለው?

ተወ =የወል ቤት ግጥም በሐረግ 6 ፣ በስንኝ 12 የሚለው ግልጽ አይደለም?

መ = የሚነግረው ? ግልጽ አልሆነላችሁም? ዝም ብዬ ስጯጯህ ነው የቆየሁት?

ተወ =በስንኝ 12 ቀለም ያለው ነው።

መ =ተረግጠው የሚነበቡ ድምጾች ናቸው። ግልጽ ነው?

ተወ =አዎ !

መ =ችግር ፈጣሪዎች እነማን ናቸው ነው ያልን?

ተወ =ሳድስ ፊደላት

መ =ሳድስ ፊደሎች በቃል መጀመሪያ ከመጡ ይቆጠራሉ። ለምንድን ነው የሚቆጠሩ?

ተወ =ተረግጠው የሚነበቡ በመሆናቸው።

መ =በቃል መሐል ከተረገጡ ይቆጠራሉ። በቃል መጨረሻ ሲመጡ ምን ይሆናሉ ?

ተወ =አይቆጠሩም፤ሙሉ በሙሉ ነካ ተደርገው ነው የሚታለፉ።

መ =አዎ!

ተወ =ከቀረበው ግጥም የሚቆጠሩት የትኞቹ ናቸው? አሳየን !

መ =ወደ ቆጠራው ልታስገባን ነው። እሽ ማነው የሚነግረኝ ?

ተወ$_{10}$ = አርበኞች (አ፣በ እና ኞ ይቆጠራሉ)

መ ="ር" ለምን አይቆጠርም ?

ተወ$_{11}$ =በቃል መካከል መጥቶ ስለማይረገጥ ፣ "ች"ን ደግሞ ተወው

መ ="ተወው !" ይቆጠራል ነው ?

ተወ$_{12}$ = አይቆጠርም።

መ =እሽ ቀጥል!

ተወ$_{13}$ =መሞትን (መ ፣ ሞ እና ት ይቆጠራሉ)

መ =እሽ ሌሎችን እንጨርሳቸው ሌላ ተማሪ

ተወ ="ት" ሳድስ ፊደል ናት ለምን ተቆጠረች ?

መ =መልሱለት!

ተወ =ተረግጦ የሚነበብ ስለሆነ ነው።

መ =ቅድም ተናግሬዋለሁ አሁን ግልጽ ሆነልህ ?

ተወ =አዎ !

መ =ለሳም ቀንዷ አይከብዳትምና በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ መጽሐፋችሁን ይዛችሁ ኑ !

## የመቅረፀ - ምስል ቀረጻ ሁለት

መ = ባለፈው ክፍለ ጊዜ እንድታዛምዱ የታዘዛችሁትን ጥያቄ እንሰራለን። እሽ አንቺ !

ተሴ = ተዋዋለ

መ = አዎ ! ተዋዋለ የሚለው ተራ ቁጥር 3 ነው።

ተወ = አምስት ቁጥር

መ = ቀፎ ቆረጠ ለሚለው ማር ወሰደ የሚለው ነው። "መ"ን ደግሞ እሽ ከኋላ

ተሴ = ተስፋ አጣ

መ = ተስፋ ቆረጠ፣ ተስፋ አጣ የሚለው ተ.ቁ 1 ነው። ደሞወዝ ቆረጠ ለሚለው

ተወ = ስድስት ቁጥር

መ = ደረሠኝ ቆረጠ

ተሴ = ማስረጃ ሰጠ "4" ቁጥር

መ = ለዓይን ያዘ ለሚለው ዐረፍተ ነገር የሚመሠርት ?

ተሴ = ጊዜው ስለመሸ ዓይን ያዘ ።

መ = ለማየት አስቸገረ ፣... ማለት ሲሆን መግል ያዘ ለሚለው ማን ይመልሳል ?

ተወ = ...እግሩ ስላበጠ መግል ያዘ።

መ = ውስጥ ላይ የተቋጠረ ፈሳሽ ነገር መኖሩን ያሳያል። ሥራ ያዘ የሚለው...

ተወ = አቶ ዓለሙ በመምህርነት ተወዳድሮ ሥራ ያዘ።

መ = እሽ ያስኬዳል ! ግጥም ምን ማለት ነው ?

ተወ = ግጥም ማለት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ... የሥነ ጽሑፍ ዓይነት ነው።

መ = ሌላ የሚሞክር

ተሴ = የተለያዩ መልዕክቶችን ሊያስተላልፍ የሚችል

መ = ሐሳቡ ሲጠቃለል ግጥም ከሥነ ጽሑፍ አካል ውስጥ አንዱ ሆኖ መልዕክቶቻችንን በቃል(በጽሑፍ)... መልዕክት የሚያስተላልፍ ጽሑፍ ነው። ሐረግ ምንድን ነው ?

ተሴ = ጅምር ዐረፍተ ነገር።

መ = ሌላ

ተወ = ሐሳባችን ወይም ንባባችንን የምናቆምበት ቦታ።

መ = እሽ ሌላ

ተወ = በአንድ ስንኝ ውስጥ የስንኙ ግማሽ ነው።

መ = ስንኝ በአንድ ግጥም፣በአንድ መስመር የሚገኝ ድምፅ ማውጣት ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ነው። ስለዚህ ቃላትን መራርጦ የሚለው ምንድን ነው ?

ተማሪዎች በጋራ = ሐረግ

መ = ሐረግ ነው ፣ ሙሉ ስንኙ ላይ በመጀመሪያ የሚገኘው ቤት መድፊያ ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ ቤት መምቻ ይገኛል። በግጥም አርኬ(አንጓ) ምን ይመስላችኋል ?

ተሴ = እያንዳንዱ ግጥም የሚጻፍበት።

መ = እሽ ሌላ

ተወ$_1$ = ተመሣሣይ ቃላትን የያዙ ስንኞች።

መ = አስተካክል እስኪ

ተወ$_2$ = እያንዳንዱ ተመሣሣይ ቃል የያዘ ስንኝ።

መ = ተመሣሣይ ቃል ከምንል

ተወ$_3$ = ሆሄያት

መ = እሽ ! ሌላ

ተወ = ተመሣሣይ የጽሑፍ ዓይነቶች

መ = ሌላ የሚሞክር

ተወ = በግጥም ውስጥ ሁለቱ ስንኞች በተመሣሣይ ሆሄያት ሲጨርሱ ነው።

መ =አርኬ(አንጓ) ስንኞች ተከታትለው በመምጣት በተመሣሣይ ሆሄ ሲጨርሱ አንድ(ሁለት) አንጓ ይሆናል። በጥቁር ሰሌዳ ከተጻፈው አርኬውን የሚያሳየኝ ?

ተወ = (በማክበብ አመለከተ)

መ = በስንኙ ውስጥ ሐረጋትን ለይቶ የሚያሳይኝ ?

ተሴ = (ተነስታ አመለከተች)

መ = በግጥሙ ውስጥ በጥቅሉ 8 ሐረጋት አሉ። ስንት ስንኞች ይኖራሉ?

ተወ = አራት

መ = በአጠቃላይ 2 አርኬ ፣ 4 ስንኝ እና 8 ሐረጋት አሉት።

ተወ = እንደአጋጣሚ ሦስት ስንኞች ቢኖሩ አርኬው እንዴት ይከፋፈላል ?

መ = አይወሰንም። በተመሣሣይ ሆሄ የቀረቡ ስንኞች ካሉ በአንድ አርኬ ይጠቃለላሉ። ስለዚህ ግጥም በሚፃፍበት ጊዜ ምን እናደርጋለን ?

ተወ = ቃላት መምረጥ።

መ = ግጥም በምንጽፍበት ጊዜ ምርጥ ቃላት የምንጠቀም ለምን ይመስላችኋል ?

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ተወ =ሰውን እንዲስብ፡፡

መ =አዎ ! ሰውን በመሳብ ተነባቢነት እንዲኖረው ፣ ሌላው

ተወ = ግጥሙን ስንጽፍ አንድን ነገር ያካተተ የሐገርን ባህል ያገናዘብ ቢሆን

ተሴ[1] =በትክክል "አንደርስታንድ" እንዲያደርጉ

መ = "አንደርስታንድ"¡

ተሴ$_2$ =እንዲረዳ እንዲያደርግ

መ =እሽ

ተሴ =...ሰዎች አንብበው በቀላሉ እንዲገነዘቡ ማራኪ የሆኑ ቃላትን መጠቀም ይገባል፡፡

መ =እሽ ያላችሁት ነገር ለግጥሙ አስፈላጊነትና ተቀባይነት አለው፤ ጥያቄ ያለው?

ተወ =አርኬዎች ሦስት ሲሆኑ ወይም ቢለያዩ እንዴት ነው ?

መ =አንድ ዓይነት ሆሄዎችን ነው አርኬ የምንለው፡፡

ተወ =አርኬ (አንጓ)ልዩነቱ ሁሌ በሆሄያት ብቻ ነው?

መ =አርኬ ማለት አንጓ ሲሆን ልዩነቱ በሆሄያት ተመሳስሎ ነው፡፡

ተሴ = "በልቶ" ከሚለው ሥር በ"ሎ" ወይም "ጽጌሬዳ" በሚለው ሥር በ"ላ" የሚጨርስ ቢኖር "ዳ" ና "ላ" በሆሄ አሰፋፈር አራተኛ ፊደላት ናቸው...(ጣልቃ ገቡ)

መ = ያልሆነ ነገር ውስጥ እየገባን ነው፡፡ በጥቅሉ አርኬ በስንኝ መጨረሻ የሆሄያትን ተመሳስሎ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የግጥም ዓይነቶች እንማን ናቸው?

ተሴ =የወል ፣ ሰንጎ መገን እና ቡሄ በሉ

መ =እነዚህን በሚመለከት በሌላ ክፍል ጊዜ በስፋት እናያለን፡፡

## የመቅረፀ - ምስል ቀረጻ ሦስት

መ =በተውኔቱ ውስጥ ያሉትን ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ ንግግሮች ለይታችሁ አውጡ፡፡

ተወ =ከምንባቡ ውስጥ ነው ?

መ =አዎ ! ምንባቡ ወይም ከተውኔቱ ውስጥ ...

ተወ =የመንደሩ መርፌ ወጊ ከሚለው ነው ? (ተማሪዎች በቡድን ሰሩ)

መ =አዎ ! እሽ አሁን ወደጋራ እንመለስና ያገኛችሁትን ንገሩኝ፡፡

$ተወ_1$ = ሰው ቢበዛም ለአንድ ያሉት ለሁለት ይበቃል፡፡

መ =(ደግመው ተናገሩ) ይህ ምንድን ነው ?

ተማሪዎች በጋራ= ምሳሌያዊ ፣ ፈሊጣዊ ብለው መለሱ

መ =ምን ማለት ነው ?

$ተወ_2$ = በምንባቡ መሠረት በአንድ መርፌ እንጨርሳቸው ማለት ነው(ሳቅ)

መ = እሽ ሌላ

ተወ =ሰው ቢበዛም ለአንድ ያልኩትን ለሁለት አካፍየ አዳርሳችኋለሁ ለማለት ነው፡፡

መ =ሌላ ተማሪ

ተወ =አትስገብገቡ አዳርሳችኋለሁ...

መ =ስለዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው ወይስ ፈሊጣዊ ?

ተማማዎች በጋራ =(ምሳሌያዊ አነጋገር)

ተሴ =የሽመታ ዕቃ

መ =ምንድን ነው ይህ ?

ተወ =የባህል መድሐኒት የሚገዛ አይደለም፡፡

መ =ትንሽ አለመሆኑን... ለመግለጽ ነው፡፡ ሌላ አላገኛችሁም እንዴ?

ተወ = ፈታ ፈታ በሉ

መ =ፈታ ፈታ በሉ ምን ማለት ነው?

ተሴ=ከፈት ከፈት በሉ (ሳቅ)

መ =ሌላ

ተወ =ተደሰቱ

መ =ሌላ

ተወ =ሐሳብ ውስጥ አትግቡ፡፡

መ =አትጨናነቁ ፈካ በሉ ይደርሳችኋል፡፡

ተወ = መቀመጫየ ላይ

መ = ይህ ምንድን ነው?

ተወ = ከቂጤ ላይ (ሳቅ)

መ = አሁን የምንነጋገረው ስለ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች ነው፡፡ መቀመጫ የሚለው ሰውየው ነውረኛ እንዳይባል የተጠቀመበት ቃል ነው፡፡

ተሴ = እሱ ከሆነስ ፍቱን የሆነ መድሃኒት ነው፡፡

መ = ምንድን ነው ፍቱን?

ተወ = ታዋቂ የሆነ

መ = ሌላ

ተሴ = መፍትሄ ያለው መድሃኒት፡፡

መ = ስለዚህ ፍቱን ነው ካለ ፈዋሽ ነው፣ ለመዳኑ አጠራጣሪ አይደለም፡፡

ተሴ = ታሞ የመጣ አይጣው

መ = እስኪ ድምፅሽን ከፍ አድርጊው " ታሞ የመጣ አይጣው" ምንድን ነው?

ተወ = ምርቃን ነው፡፡

መ = ምርቃን ነው? ሌላ

ተወ = የሥጋ መጉደል

መ=የሥጋ መጉደል! (ሳቅ)

ተሴ = ንቅሳት

መ = እሽ

ተወ = በረካ ሁንልኝ

መ = አዎ! በረካ ሁኑ ማለት ከምርቃን ውጭ ምን ማለት ነው?

ተማሪዎች በጋራ = (የቡና ሦስተኛ ነው)

ተወ = እጅዎን ያውጡ

መ = ይህ ምንድን ነው?

ተወ =ፈሊጥ ነው?

መ = ምን ማለት ነው?

ተሴ = በምንባቡ መሠረት ራስህን አሳይ ማለት ነው፡፡

መ = ሽሪ! .... ሌላ

ተሴ = እራስህሬ አድን፡፡

መ= አዎ፡፡ ራስን ተከላከል፣ አምልጥ፣ ፖሊስ መጥቷል፡፡

ተሴ= በዚህኛው ታፋየ…

መ = ምን ማለት ነው? ታፋ ይባላል እኮ!

ተወ = ያንተያለህ

መ = ያንተያለህ?

ተወ = ቆይ ቆይ (ሳቅ)

መ =ሌላ

ተወ = እሰይ ነፍሴ መለስ አለች፡፡

መ = ነፍሴ መለስ አለች ማለት ተሻለኝ ህመሙ ታገሰልኝ…

ተሴ=መቼም ያጅሬ መድሃኒት ፍቱን ነው

መ = አጅሬ እዚህ ላይ ምኑን ያሳያል?

ተመ = ታዋቂነቱን፣

መ = ዝነኛነቱን በጣም ጎበዝ መሆኑን ያሳያል እሽ ምሣሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግር ሁለቱም

የቋንቋ ፈርጦች ናቸው፡፡ ልዩነታቸው ምንድን ነው?

ተወ = ፈሊጣዊ ንግግር በአንድ ቃል ሊገለጽ ይችላል፡፡ ምሣሌያዊ ግን ከሁለትና ከዚያ በላይ

በሆነ ቃላት ይገለፃል፡፡

መ = እሽ ሌላ

ተሴ = ፈሊጥ ሲባል የሚሞካሽ ነገረ፣ ምሣሌያዊ ንግግር ግን ለምናልባት

ይሆናል(ቢሆንስ)የሚለውን ያያል?

መ = ሌላ፣ሌላ

ተወ = ምሣሌያዊ አነጋገር ማለት በአንድ ነገር ላይ አተኩሮ የሚቀርብ ንግግር ሲሆን

ፈሊጣዊ አነጋገር ደግሞ ተዘውታሪ ያልሆነ

መ = ለምንድን ነው ጨርሰው እንጂ ?

ተወ = ምሳሌያዊ አነጋገር ቀጥተኛ ትርጉም ላይ ጥሬ ትርጉም መስጠት ሲሆን ፈሊጣዊ

አነጋገር ደግሞ በነገሮች በማስመሰል ፍቺን ማውጣት ነው፡፡

መ = እሽ ! እዚያ

ተወ = ምሳሌያዊ አነጋገር ከአንድ ነገር ጋር በማመሳሰል ፍች መስጠት ሲሆን ፈሊጣዊ

አነጋገር ግን … አስመስለን የምንናገረው…

መ = ከቅርጻቸው አንፃር ፣ ከአጻጻፋቸው አንፃር መናገር ትችላላችሁ፡፡

ተሴ = ምሳሌያዊ አነጋገር በዐረፍተ ነገር ወይም በሐረግ ሊቀርብ ሲችል፣ፈሊጣዊ ንግግር ደግሞ ግሦች ናቸው፡፡

መ = በእርግጥ ከግሶች የሚመሰረቱ ፈሊጣዊ ንግግሮች አሉ፡፡ እሽ ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ ንግግሮች "ፈርስት ሴሚስተር" ተምራችሁ ነበር ዘንግታችሁ ነው እንጂ፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ግጥማዊ ባህርይ አላቸው፡፡አመሰራረታቸውም ዐረፍተ ነገራዊ ናቸው፡፡ ለፈሊጣዊ አነጋገሮች አብዛኛውን ጊዜ በቃል አልፎ አልፎ በሐረግ ደረጃ ይቀርባሉ፡፡... እሽ ሌላ የሚነግረኝ?

ተወ = እንደ ሽመታ ዕቃ

መ = እሽ ! ይህ ምን ዓይነት ዘይቤ ነው? ተነፃፃሪ ዘይቤ ነው አይደል? ... ስለዚህ የቤት ሥራ ምንባቡን እንደገና በማንበብ በውስጡ ያሉትን ዘይቤዎች ፣ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ለይታችሁ ፃፉ፡፡... እዚህ ላይ ግልጽ ያልሆነ ነገር ካለ?

ተወ = ዘይቤዎችን ከምሳሌያዊ አነጋገሮች ውስጥ ከነፍቻቸው ነው የምናወጣቸው?

መ = ከነፍቻቸው ብትለያቸው ቀንጆ ነው፡፡ ዘይቤዎች ምን ዓይነት እንደሆኑ መለየት ተገቢ ነው፡፡ እሽ! በቤት ሥራ መልክ እንድታዘጋጁ የተነገረውን ተውኔት አቅርቡ፡፡

ተማሪዎች = (ተውኔት አቀረቡ)

መ = እሽ! ከናንተ የቤት ሥራ በመነሳት አንዳንድ ነገሮችን እንነጋገር፡፡ አዘጋጅ ምን ማለት ነው?

ተወ = መሪ ፀሐፊ፡፡

መ = መሪ ፀሐፊ ነው?

ተወ = መሪ ተውኔት፡፡

መ = እሽ ሌላ

ተወ = አቅራቢ

መ = ስንት ሰው ነው ያቀረበው ?

ተወ = አራት

መ = እና እነሱ አዘጋጅ ነው የሚባሉ ?

ተማሪዎች በጋራ = ተዋናይ

መ = እሽ! አዘጋጅ መሪ ተውኔት ነው ብሎናል... አዘጋጅ ምን ማለት ነው ትላላችሁ?

ተሴ = በመድረክ ላይ ተርጉሞ የሚያቀርብ፡፡

መ = ባየነው ድራማ አዘጋጁ እስቲበል ነው፡፡ ፀሐፊ ተውኔትና አዘጋጅ ሆኗል፡፡ እሽ ቃለ ተውኔት ምንድን ነው?

ተወ = ተውኔቱን የሚያቀርበው

መ = እስኪ እሱያውቃል ሞክር!

ተወ = በቃል የሚቀርብ ልብ ወለድ

መ = ሀገመንግስት ቃለ ተውኔት ምንድን ነው ? ሞክር!

ተወ = አላውቀውም

መ = አላገኘሽውም? እሽ ሌላ

ተሌ = በጽሑፍ ተደግፎ መድረክ ላይ የሚቀርብ

መ = እሽ ቃለ ተውኔት ይባላል? ሌላ እነዚህን ነገሮች ፈልጓቸው ብያለሁ!

ተወ = ከእኛ መጽሐፍ ላይ አለ ?

መ = አዎ!የቤት ሥራውን ቤተ መጽሐፍት ሄዳችሁ በማንበብ በጽሑፍ ማብራሪያ ስጡ ብያለሁ፡፡

ተወ = በዐረፍተ ነገሮች ሊገለጽ የሚችል፡፡

መ = ያ ማለት ነው? ተማሪዎች ባቀረበት ተውኔት ላይ ፀሐፊ ተውኔቱ እስኪበል ነው ብለናል፡፡ ስለዚህ ምንባቡን በማንበብ ምሳሊያዊ ፣ፈልጣዊ አነጋገሮችና ዘይቤዎችን ለይታችሁ አውጡ፡፡

## የመቅረፀ - ምስል ቀረጻ አራት

መ =አስተዋጽኦ ባለፈው ጽፋችሁ እንድትመጡ ተናግሬያለሁ። ማነው የጻፈ?

ተሴ =(በደብተሯ "ሱስ" በሚል ርዕስ የፃፈችውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ)

መ = እሷ ዝምብላ "ሱስ" የሚያስይዙ ነገሮች ብቻ ያለችው የሚያስከትሉት ሁኔታዎች በሚል ተስተካክሏል። አስተዋጽኦ ስናወጣ አብይ ነገሮችን እንለያለን።

ተወ =ይህም ለወሰን ይረዳናል

መ =ሐሳብን ለማጥበብ ይረዳናል። እስኪ አንቺ የፃፍሽውን አንብቢ።

ተሴ =የሱስ ዓይነቶችና ጉዳታቸው የሚል ነው።

መ =እንደ እሷ ነው? በአስተዋጽኦ (ቢጋር) መልክ ነው የሠራሺው?

ተሴ =አዎ! በአስተዋጽኦ መልክ (በንግግሯ ጣልቃ ገቡ)

መ =ግን መጀመሪያ አስተዋጽኦ ከመፃፋችን በፊት ምን ማድረግ አለብን?

ተማሪዎች በጋራ =ርዕስ መምረጥ።

መ = ርዕስ መምረጥማ ዋናው የሚቀድም ነው። ከዚያ በኋላስ ?

ተወ = አስተዋጽኦ መንደፍ።

መ =ወደ አስተዋጽኦ ቀጥታ አንሄድም! ከዚያ በፊትስ?

ተወ =ማሰብ

መ =ዋና ዋና ሐሳቦችን በርዕሱ ዙሪያ እንዘረዝራለን። ገጽ 106 - 107 ላይ ተመልከቱ። አስተዋጽኦ ስንነድፍ ለምሳሌ እሷ ሱስ ... ብቻ ነው ያለችው።

ተወ =የውሃ ሙላት ሰዎችን ያራርቃል ሲባል እንዴት ነው?

መ =መስከረም ሲጠባ የውሃው ሙላት ሲቀንስ የመገናኘቱ ሁኔታ ይሰፋል፤

ተወ =እንደልብ አለመገናኘታቸው ነው እንጂ ይገናኛሉ?

መ =የመገናኘት ዕድሉ ሰፊ መሆኑን ለማሳየት ነው።... ዋናው ድርሰት ጽሑፍ መሆኑን በአንደኛው ሴሚስተር የድርሰት ብያኔ (ትርጉም) ምንድን ነው ብለናል?

ተሴ =ደረሰ ከሚለው የአማርኛ ቃል የመጣ።

መ =(መልሷን በድጋሚ ተናገሩ) ያ ከየትኛው የቃል ክፍል ውስጥ ይመደባል?

ተወ =ከግስ

መ =ከቃል ክፍል ውስጥ ግስ ሆኖ ድርሰት የሚለው ደግሞ ምንድን ነው?

ተወ =ስም

መ =... መጠሪያ ነው ማለት ነው ፤ ስለዚህ ትርጉሙ ምንድን ነው?

ተወ =በዓይን ያየነውን በጆሮ የሰማነውን ነገር በጽሑፍ የምናሰፍርበት ነው፡፡

መ =አዎ ! ስለዚህ ድርሰት ለመጻፍ ምን ማድረግ አለብን?

ተማሪዎች በጋራ= ርዕስ መምረጥ

ተወ₁ =… ደራሲው እንዴት ከአእምሮው አመንጭቶ ጻፈ ልንል እንችላለን?

መ =ድርሰት ልቦለድ እና ኢ- ልቦለድ ድርሰት ይባላል፡፡ አሽ ሃሳብህን ጨርስ !

ተወ₂ =ያየውንና የሰማውን ከሆነ እንዴት ከአእምሮው አመንጭቶ ጻፈ ማለት ያስችላል?

መ =… እሱ ባየበት ሌሎች እንዲያዩት ማድረግ ነው፡፡ ባለፈው ዓመት አልነበርክም ?

ተወ₃ =ነበርኩ

መ =… የድርሰት ብያኔ ያለውን መሠረት በማድረግ የሚጻፍ ነው፡፡ ግልጽ አይደለም ?

ተወ₄ =ግልጽ ነው፡፡

ተሴ =በድራማ፣ትረካ ደራሲው ተዋንያንን ይወክላል፡፡ አስተዋጽኦ ላይ (በንግግሯ ጣልቃ ገቡ)

መ =ያ ና ይህ ይለያያል፡፡ ይበልጥ በቀጣይ ጊዜ ናሙና ተውኔት ስለሚኖር እናየዋለን፡፡

ተሴ =በአስተዋጽኦ ላይ ገቢ እያሽቆለቆለ ይሄዳል የሚለው (በንግግሯ ጣልቃ ገቡ)

መ = ህዝቦች ሱስ ከተጠመዱ ገቢ ይቀንሳል፡፡ እሷ ዝምብላ ስላቀረበችው ነው እንጂ ትክክል ነው ማለት አይደለም፡፡ ገጽ 110 አውጡ አያያዥ ምንድን ነው ?

ተወ =ቃልን ከቃል ዐረፍተ ነገርን ከዐረፍተ ነገር የሚያያይዝ ነው፡፡

መ =አዎ ! (ደግመው የተማሪውን መልስ ተናገሩ) ሌላ ?

ተወ =አንድ ግስ እንዳያስር ያደርጋሉ፡፡

መ =አያያዦች ሌላ ተግባራቸው ግስ እንዳያስርና ቀጣይ ግስ እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡

ተወ =እንዳያስር የተደረገ ግስ ፍዝ ግስ አይደለም የሚባል ?

መ =ፍዝ ግስ አይደለም፡፡ ፍዝ ግስ የሚባል ከግስ ዓይነቶች ውስጥ የለም፡፡

ተወ = በልቶ፣ጠጥቶ…የሚሉትን ፍዝ ግሶች ናቸው ተብዬ ታች ክፍል ተምሬአለሁ፡፡

መ = እነሱ ቦዝ አንቀጽ ይባላሉ፡፡ ለሚቀጥለው ጊዜ በጻፋችሁት አስተዋጽኦ ድርሰት ጻፉ!

## የመቅረፀ - ምስል ቀረጻ አምስት

መ = ባለፈው ሳምንት የተማርነው ስለምን እንደሆነ የሚነግረኝ ?

ተሴ = በግጥም ውስጥ ስንት ስንኝና ሐረግ እንዳሉ።

መ = ጥሩ ! ግጥም በባህርይው መዝሙራዊ ፣ሙዚቃዊ ቃና ያለው ሌላስ ?

ተወ = በስንኝ የቀረበ

መ = ሌላ

ተሴ = ቤት መምቻና መድፊያ ያለው

መ = እሽ

ተወ = በሐረግ የተከፋፈለ

መ = (ደግመው መልሱን ተናገሩ)

ተወ = ምርጥ በሆኑ ቃላት የሚቀርብ

መ = በምርጥና ቁጥብ ቃላት በዘይቤዎች ፣ በምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚቀርብ እሽ

ተወ = የሰውን ስሜት መሳቡ።

መ = የግጥም ዓይነቶችን በምንድን ነው የምንለያቸው ?

ተማሪዎች በጋራ = በቀለማቸው

መ = ቀለም ምንድን ነው ያልነው ?

ተሴ = ተረግጠው የሚነበቡ

መ = አዎ !... ስለ ሳድስ ፊደሎች ምንድን ነው ያልን ?

ተወ = በመሀል ከመጡ ይቆጠራሉ።

መ = አዎ ! ሌላ

ተወ = በመጨረሻ ከመጡ አይቆጠሩም።

መ = በመጀመሪያ ከመጡ ይቆጠራሉ። የቤት ሥራውን የሚሠራ?

ተወ = ተስፋ ለሚለው ትዝታ።

መ = "መ" ትዝታ ትክክል።

ተወ = ሽቅብ ለሚለው ቃል ቁልቁል።

መ = "ሀ" ቁልቁል ጥሩ።

ተሴ = መፍዘዝ = መተከዝ

መ = እ... እና ማን ነው ? "ለ" መተከዝ ቀጥይ እንቺ !

ተሴ = መፍዘዝ ለሚለው "ሠ" መሳት

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

መ = እሽ ድምጽህን ከፍ አድርገህ

ተወ = መፍዘዝ ለሚለው...

መ = ይህማ ተመለሰ። አየለ ለሚለው

ተወ = አየለ = ደከመ።

መ = አየለ "ሐ" ደከመ። እሽ አሁን ሁለተኛውን የቤት ሥራ አንደኛውን የሚመልስ ?

ተሴ = እንቡጥ አበባ ለሚለው ትንሽ።

መ = እንቡጥ ማለት ትንሽ ነው ? ትክክል አይደለም። ሌላ ?

ተወ = አንቡጥ ለሚለው ለጋ።

መ = በእርግጥ ለጋ ነው።

ተሴ = ያልፈነዳ አበባ

መ = ያልፈነደቀ አበባ ወይም ያላበበች ገና ለማበብ የተዘጋጀ አበባ እሽ "ለ"

ተወ = ውበት ሲፈነዳ = ውበት መጣ

መ = እሽ !

ተወ = ውበት አየለ

መ = አበበ ፤አማረ ማለት ነው። የተሰመረበት ማነው ? የቃል ክፍሉ ምንድን ነው ?

ተመሪዎች በጋራ = ወደ የሚለው ነው።

ተወ = መስተዋድድ

መ = ይህን ወደ የሚል መስተዋድድ በምን እንተካው ?

ተወ = ከ አዘቅት

መ = ይባላል ? ጥሩ !

ተወ = ስለ አዘቅት።

መ = እነዚህን መተካት እንችላለን "መ"ን የሚሠራ

ተሴ = ፍላጎት አየለ የሚለው ምኞት አየለ

መ = ተስፋ አየለ እሽ "ሰ" ጽጌረዳ ለሚለው

ተወ = ስለ ጽጌረዳ

መ = አዎ !ከጽጌረዳ ማለት ይቻላል። ሰሚ አጣ ለሚለው

ተወ = ሰሚ አላገኘም።

መ = አዎ !በወሬ ተፈታ ለሚለው

ተሴ = በወሬ ተገለፀ።

መ = ተገለፀ ¡ ሌላ

ተወ = በወሬ ተለቀቀ

መ = ሌላ

ተሴ = በወሬ ተግባባ

መ = ተግባባ ¡ ሌላ

ተወ = በዋስ ተፈታ

መ = የተሰመረበት ተፈታ ነው።

ተወ = በወሬ ተጋደለ

መ = በወሬ ተሸበረ በወሬው ምክንያት ተረበሸ ጀግና ተረበሸ ማለትስ ?

ተወ = ነበዝ ሆነ

መ = አዎ ! በሀሳብ ጦርነት የሚለውን የሚመልስ ?

ተሴ = በሐሳብ አለመስማማት።

መ = አለመስማማት ¡ ጦርነት ምን ባህርይ እንዳለው ታውቃላችሁ ?

ተወ = በሐሳብ ግጭት

መ = ... በሐሳብ አዘቅት። እሽ ዕድገት ተሰናከለ የተሰመረበት "ዕድገት" ነው።

ተወ = ብልጽግና ተሰናከለ።

መ = (መልሱን ደገሙ) እሽ በስንኝ ቋጠሮ የሚለውን ግጥም እናነባለን። በቅድሚያ በፈቃደኝነት የሚያነብ ?

ተሴ = ( ያለ ቃላት ስህተት ማንበብ ጀመረች)

መ = አንድ አፍ ሁለት ሥራ አይሰራም አሏት (ማስቲካዋን አወጣች)

በቃ ! ጥሩ ነበር ምንድን ነው የእሷ ችግር ? ፍጥነት። ሰምተሻል? እንደባቡር ነው ድ...ድ...ድ... ያልሽ ፤ ረጋ ብታደርጊው ጥሩ ነበር። የስነ ጽሑፍ ውበቱ ተደማጭነቱ ነው። እንደው ዝም ብሎ አያይዘው ከሄዱ ችግር አለው። ሌላ?

ተወ = (መምህሩ እርማት ሰጡ)

| | |
|---|---|
| አሉባባታ =አሉባልታ | ሲሸናገል = ሲሸነጋገል |
| ሲፈታ = ሲፈታ(ጥብቀት) | ሕይወት = ሕይወትን |
| ሲገዛ = ሲገዛ | መዘዛ = መዘዛ (መዝጊያ) |
| ሕይወትን አጥሮ = ሕይወትን አንጥሮ | ሰደራ = ሰደራ |

መ = እሽ መሰደር ማለት ምን ማለት ነው ?

ተወ = መደርደር

መ = ማሰለፍ ፣ ማስተካከል ማለት ነው። እሽ ሌላ

ተሴ = (አነበበች እርማት ስጡ) ስንኞች መዞ = ስንኞችን መዝዞ

መ = ና አንተ አንብብ ! (ማን ፈቀደ? ያልታዘዘ ተማሪ ማንበብ ጀመረ) (ማስተካከያውን

ተማሪው እንዲሰጥ አደረገ)

ስንጠልቅና ስናወርድ = ስንጥልና

ፈሪ አንገት ሲደፋ = ፈሪ አንገት ደፍቷል (ሌላ የሚያነብ?)

ተወ = (አነበበ)

መ = ጥሩ ነው ! ሌላ አንቺ ነይ ! አሉ

ተሴ = (አነበበች)

መ = ድምፅ ጨምሪ! ይህን እንደቀላል እንዳታዩት። ፍርሐት አስወግዱ ! በቃሽ ሌላ?

ተወ = (አነበበ)

መ = ድምፅህ ምንድን ነው?(ሳቀ) ለወደፊቱ ጨመር አድርገህ አንብብ እንጂ ጥሩ ነው!

ተወ = (አነበበ) (እርማት እራሱ እንዲሰጥ አደረገ)

ሲመነጥቅ = ሲመነጠቅ ስንኞችን = ስንኝ

አንገት ደፍቶ = አንገት ሲደፋ ሲደላቀቅ = ሲንደላቀቅ

መ = ነይ አንቺ !

ተሴ = (አነበበች) ማስተካከያ እርማት ሰጡ

ግጥምን = ግጥም ሲመነጥቅ = ሲመነጠቅ

ሃይሉ = አይሎ ደፍቶ = ሲደፋ

መ = በቃ ቁጭ በይ ! ሌላ

ተወ = (አነበበ) ስህተቱን እራሱ አረመ

መ = ጥሩ ነው ! ሌላ

ተሴ = (አነበበች)

መ = ሌላ

ተወ = (አነበበ) ስህተቱን እራሱ አስተካከለ

መ = ድምጽህን እዚያ ሆነህ ሰምቼዋለሁ።

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

## የመቅረፀ - ምስል ቀረጻ ስድስት

መ = ምንባብ ከማንበባችን በፊት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች አሉ፡፡ እነሱን እንነጋገር፡፡ ተዋናይ ማለት ምን ማለት ነው?

ተወ =በመድረክ ላይ የሚካሄደውን ድርጊት የሚሠራ፡፡

መ = አዎ ! በመድረክ ላይ የሐዘንም ሆነ የደስታ ድባብ በመፍጠር የሚያከናውን ነው፡፡ እሽ ! መድረክ ማለት ምንድን ነው? "የስ"

ተወ = ተዋናዩ የሚሠራበት ቦታ

መ = … ተመልካቹና ታዳሚ የሚታዩበት ተውኔት ማለትስ?

ተወ = በአጠቃላይ ተዋናዩና በመድረኩ ላይ ሲቀርብ የሚያሳይ ነው፡፡

መ = ተውኔት በመድረክ ላይ ለተመልቾች የሚቀርቡበት ሂደት በመሆኑ በዓይናችን በተግባር የምናየው ነው፡፡ እሽ! ከምታደንቋቸው ተወናዩች ውስጥ ጥቀሱ?

ተወ = ክበበው ገዳ

መ = ለምን?

ተወ = በጣም አስመስሎ ስለሚጫወት፡፡

መ = "የመንደሩን መርፌ ወጊ" የሚለው ርዕስ ስለምን የሚያወራ ይመስላችኋል?

ተወ = ባህላዊ የሆነ ሕክምና፡፡

መ = ሌላ?

ተወ = በመንደር ውስጥ ያሉ የመርፌ አወጋግ፡፡

መ = ሌላ ?

ተወ= አካካቢያዊ የሆነ እምነት ፣ … ህብረተሰቡን ማሳመኛ ነው፡፡

መ = "ኦኬ" እንግዲህ ይህን ካልን በቀጥታ ወደ ምንባቡ እንሄዳለን የሚያነብ ?

ተወ = (አነበበ)

መ = ሌላ ?

ተወ = (ቀጣዩን አንብቦ ጨረሰ)

መ = ሰዎቹ እየመጡ ነው ያምልጡ ያለበት ምክንያት ምን ይምስላችኋል?

ተወ = ምክንያቱም የሚከናወነው ተግባር ሕጋዊ ስላልሆነ?

መ = እሽ !

ተወ = መርፌ የወጋት ሴትዮ በመሞቷ ምክንያት ነው፡፡

መ = ሌላ ሰው?

ተወ = የተሰለፉት ሰዎች እኛንም መርፌ ውጋን ብለው

መ = እሽ ሌላ?

$ተወ_1$ = ሰውየው ሳይዘጋጁ እንደመጡ ለማሳወቅ ተዘጋጅ ለማለት ነው።

መ = የትኞቹ ሰዎች?

$ተወ_2$ = በሽተኞች።

መ = እስኪ አንተ ግልጽ አድርገው!

$ተወ_3$ = የሚሠሩት ነገር እንዳይታወቅ ለማድረግ ነው።

መ = እንደ መርፌ ወጊው ዓይነት ሰው ብታገኙ ምን ታደርጋላችሁ?

ተወ = ሕጋዊ ያልሆኑትን በማጋለጥ ለማህበረሰቡ ለማሳወቅ ቃል እገባለሁ።

መ = ሌላ?

ተወ = ሕገወጥ ሥራ ወደ ሚሠራው አለመሄድና ለሚመለከተው አካል መጠቆም ራስንም ማስተማር ነው።

መ = ጥሩ ብላችኋል ! ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ የቤት ሥራ ሠርታችሁ እንድትመጡ።

# አባሪ 2

## የመምህር ተማሪ መስተጋብር ማመሳከሪያ ሰነድ (Checklist)

| ተ.ቁ | የምልከታ የትኩረት ነጥቦች | ፆታ | |
|---|---|---|---|
| | | ሴት | ወንድ |
| 1 | መምህሯ(ሩ) ጥያቄ ጠየቁ | | |
| 2 | መምህሯ (ሩ) በተማሪዎች ምላሽ ጣልቃ ገቡ | | |
| 3 | ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሰጡ | | |
| 4 | ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ መለሱ | | |
| 5 | መምህሯ(ሩ) ለጥያቄ መመለሻ ረዘም ያለ ጊዜ ሰጡ | | |
| 6 | መምህሯ(ሩ) ለተማሪዎች መልስ አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ ሰነዘሩ | | |
| 7 | መምህሯ(ሩ) ለተማሪዎች መልስ ምንም ምጋቤ ምላሽ አልሰጡም | | |
| 8 | መምህሯ(ሩ) ለተማሪዎች መልስ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ ሰነዘሩ | | |
| 9 | መምህሯ(ሩ) ተማሪዎችን በስም እየጠሩ ጠየቁ | | |
| 10 | ተማሪዎች እጅ ሳያወጡ መለሱ | | |

### ሀ. ከምልከታ አንድ እስከ ምልከታ አራት

ቀን:- 29 እና 30/8/፣ 2 እና 6/9/99 ዓ.ም.

የትምህርት ቤት ስም:- ፋሲሎ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ክፍለ ጊዜ:- 3ኛ (ከሰዓት በኋላ) ፣ 5ኛ (ከጠዋት)፣ 2ኛ (ከጠዋት)እና 3ኛ (ከሰዓት በኋላ)፣

ሰዓት:- 8:00 - 8:40፣ 4:45 - 5:25፣ 2:40 - 3:20እና 8:00 - 8:40

ምልከታ የተደረገበት የክፍል ምድብ:- 9ኛ "S"፣ "W"፣ "C" እና "F" (በቅደም ተከተል)

የመምህር ፆታ:- ሴት፣ ወንድ

## ከምልከታ አምስት እስከ ምልከታ ስምንት

ን፡- 3፣7፣9 እና 13/9/99/ ዓ.ም.

ትምህርት ቤት ስም፡- ጣና ሐይቅ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ፍለ ጊዜ፡- 4ኛ (ከሰዓት በኋላ)፣ 5ኛ (ከጠዋት)፣ 1ኛ (ከጠዋት)እና 3ኛ (ከጠዋት)፣

ዓት፡- 9:00 - 9:40፣ 4:45 - 5:25፣ 2:00 - 2:40እና 3:20-4:00

ምልከታ የተደረገበት የክፍል ምድብ፡- 9ኛ “2”፣ “4”፣ “6” እና “9” (በቅደም ተከተል)

መምህር ፆታ፡- ሴት፣ ወንድ

## ሐ. ከምልከታ ዘጠኝ እስከ ምልከታ አስራ ሁለት

ቀን፡- 10፣15(2 ጊዜ) እና 16/9/99/ ዓ.ም.

የትምህርት ቤት ስም፡- ግዮን 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ክፍለ ጊዜ፡- 1ኛ (ከጠዋት)፣ 5ኛ (ከሰዓት በኋላ)፣ 4ኛ (ከጠዋት)እና 2ኛ (ከሰዓት በኋላ)፣

ሰዓት፡- 2:00 - 2:40፣ 9:40 -10:20፣ 4:15 - 4:45እና 7:20-8:00

ምልከታ የተደረገበት የክፍል ምድብ፡- 9ኛ “V”፣ “Z”፣ “N” እና “Q” (በቅደም ተከተል)

የመምህር ፆታ፡- ሴት፣ ወንድ

# አባሪ 3

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## በጣና ሐይቅ፣ ግዮን እና ፋሲሎ ሁለተኛ ደረጃ

## ትምህርት ቤቶች በተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሴትና ከወንድ ተማሪዎች ጋር ያላቸውን መስተጋብር ለማጥናት የሚረዱ መረጃዎችን መሠብሰብ ነው፡፡ ስለዚህ እናንተ የምትሰጡት መልስ ለጥናቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላለው በጥንቃቄ በመሙላት ትብብር እንድታደርጉልኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ስለሰጣችሁኝ መረጃ በቅድሚያ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡- ይህ መጠይቅ ሦስት ክፍሎች አሉት፡፡ በየክፍሉ ላሉት ጥያቄዎች በትዕዛዞች መሠረት ተገቢ መልስ ስጡ፡፡ በመጠይቁ ስም መግለጽ አያስፈልግም፡፡

### ክፍል አንድ

አጠቃላይ መረጃ

1.1 የትምህርት ቤቱ ስም፡- ______________________

1.2 ፆታ፡- ______________

1.3 ዕድሜ፡- ______________

### ክፍል ሁለት

ከዚህ በታች በክፍል ውስጥ በተማሪና መምህር መካከል ያለውን መስተጋብር የሚያመለክቱ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዱ ሃሳብ መምህርሽ(ህ) በመስተጋብር ወቅት ስለሚያከናውኑት ተግባር ምን ያክል ትክክለኛ ስለመሆኑ የምትገልጭ(ጽ)በት አራት አማራጮች ተዘርዝረዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ምርጫ፡- 1= ፈፅሞ ሐሰት ነው፡፡

2= አንዳንድ ጊዜ (አልፎ አልፎ) ትክክል ነው፡፡

3=አብዛኛውን ጊዜ ትክክል ነው፡፡

AAU I.L.S LIBRARY

4= ሁልጊዜ ትክክል ነው። የሚለውን የሚያመለክቱ ሲሆኑ ለአንቺ(ተ)ተገቢ የሆነውን ምርጫ ቁጥር በማክበብ አመልክት(ች)።

| የመስተጋብር ጠቋሚ ነጥቦች | ፈፅሞ ሐሰት ነው | አንድአንድ ጊዜ (አልፎ አልፎ) ትክክል ነው | አብዛኛውን ጊዜ ትክክል ነው | ሁልጊዜ ትክክል ነው |
|---|---|---|---|---|
| በክፍል ውስጥ ሐሳቤን በነፃነት እንድገልጽ በመምህሬ እበረታታለሁ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ቀላል ጥያቄዎችን ብቻ ይጠይቁኛል | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ በክፍል ውስጥ ጥያቄ ሲጠይቁኝ ስሜን በመጥራት ነው | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ አስተያየታቸውን በግል ጠርተው ይነግሩኛል | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ጥያቄ እንድጠይቅ ያበረታቱኛል | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ካሉት ወንድ ተማሪዎች አንፃር ፊትም ሆነ ኋላ የተቀመጡትን ያሳትፋሉ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ጥያቄ በምመልስበት ጊዜ ስሳሳት ይገስጹኛል (ይተቹኛል)። | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ሌሎች ተማሪዎች ያልመለሱትን ጥያቄ እንድመልስ እድል ይሰጡኛል | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ጥያቄ የሚጠይቁት ስሜን ከጠሩ በኋላ ነው | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ጥያቄ ሲጠይቁኝ ለመልስ መስጫ ረዥም ጊዜ ይሰጡኛል | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ጥሩ ሥራ መምህሬ የማበረታች (የሙገሳ) ምጋቤ ምላሽ ይሰጡኛል | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ከባድ ጥያቄዎችን ይጠይቁኛል | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ አስተያየቶችን በክፍል ውስጥ ይነግሩኛል | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ሴትና ወንድ ተማሪዎች በቡድን ሥራ እንዲሳተፉ ያደርጋሉ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ጥሩ ባህርይ ሳሳይ አበረታች ምላሽ ይለግሱኛል | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ እጅ ሳላወጣ ስመልስ ይሰድቡኛል (ይገስጹኛል) | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ለጠየቁኝ ጥያቄ ተመጣጣኝ የመመለሻ ጊዜ ይመድባሉ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ካሉት ሴት ተማሪዎች አንጻር ፊት ለተቀመጡት ብቻ የተሳትፎ እድል ይሰጣሉ | 1 | 2 | 3 | 4 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መምህሬ ጥያቄውን ካቀረቡ በኂላ ስሜን እየጠሩ ያሳትፉኛል | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ትክክለኛ መልስ ስሰጥ ምንም ዓይነት ምጋቤ ምላሽ አላገኝም | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ተግባራትን በተፎካካሪነት (በግል) እንድሰራ ያደርጋሉ | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መምህሬ ለጥያቄ መመለሻ ረዥም ጊዜ አይሰጡኝም | 1 | 2 | 3 | 4 |

ክፍል ሦስት

ከታች ለቀረቡት ሦስት ጥያቄዎች ያህል (✓) ምልክት በማድረግ እንደአስፈላጊነቱ በክፍት ቦታ ላይ በመጻፍ ተገቢውን መልስ ስጭ(ጥ)።

3.1. በትምህርት ሂደቱ ሃሳብሽ(ህ)ን ለመግለጽ ስትቸገሪ(ር) መምህርሽ(ህ) ምን ያደርጋሉ?

☐ ትችት (ሒስ) ይሰነዝራሉ

☐ በጥሞና ያዳምጣሉ

☐ ንግግሬን ጣልቃ በመግባት ያቋርጣሉ

☐ ፍንጭ ይሰጣሉ

☐ ዕድሉን ለሌላ ተማሪ ይሰጣሉ

☐ ደግመው ይናገራሉ (ያነባሉ)

ሌላ ካለ ጥቀሽ(ስ)______________________________።

3.2. በመምህርሽ(ህ) ወይም በሌላ ተማሪ ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ እንድትሰጪ(ጥ) ተጠይቀሽ(ህ) የተሳሳተ ምላሽ ብትሰጪ(ጥ) መመህርሽ(ህ) ሊያደርጉ ይችላሉ ብለሽ(ህ) የምታስቢ(ብ) ውን በቅደም ተከተል ፃፊ(ፍ)።

ሀ. ______________________ መ. ______________________

ለ. ______________________ ሠ. ______________________

ሐ. ______________________

3.3. መምህርሽ(ህ) የምትሠሪ(ራ)ውን ሥራ በሚመለከት አበረታች አስተያየት ሲሰነዝሩ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማሽ(ህ) በቅደም ተከተል አስፍሪ(ር)።

ሀ. ______________________ መ. ______________________

ለ. ______________________ ሠ. ______________________

ሐ. ______________________

# አባሪ 4

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## በጣና ሐይቅ፣ ግዮን እና ፋሲሎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

## ቤት በመምህራን የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸውን መስተጋብር ለማጥናት የሚረዱ መረጃዎችን መሠብሰብ ነው፡፡ በመጨረሻም ጥናቱ የክፍል ውስጥ መስተጋብርን ለማጎልበት የሚያስችሉ ነጥቦችንና አመላካች ሃሳቦችን እንደሚሰነዝር ይታመናል፡፡ ለጥናቱ ውጤታማነት የመምህራን ተሳትፎ ወሳኝ በመሆኑ እርስዎም ለጥናቱ ትክክለኛ መረጃ እንደሚሰጡኝ በመተማመን ለሚያደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

ማሣሠቢያ፡-ይህ መጠይቅ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ በየክፍሉ ላሉት ጥያቄዎች በትዕዛዞች መሠረት ተገቢ መልስ ይስጡ፡፡ በመጠይቁ ስም ማስፈር አያስፈልግም፡፡

### ክፍል አንድ

አጠቃላይ መረጃ

1.1 የትምህርት ቤቱ ስም፡-__________________

1.2 ፆታ፡- ________

1.3 ያገልግሎት ዘመን፡- __________

1.4 የትምህርት ደረጃ፡- ___________

1.5 የስልጠና ሁኔታ

ዓብይ፡- _______________

ንዑስ፡- _______________

### ክፍል ሁለት

ከዚህ ቀጥሎ በክፍል ውስጥ በተማሪና መምህር መስተጋብር ያለውን ሁኔታ የሚለኩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ያለዎት አመለካከት ምን እንደሆነ ለማመልከት በስተቀኝ አምስት ምርጫዎች በደረጃ ሠፍረዋል፡፡ በዚህ መሠረት ምርጫ፡-

1=በፍጹም አልስማማም

2=አልስማማም

3=ለመወሰን እቸገራለሁ

4=እስማማለሁ

5=በጣም እስማማለሁ የሚሉትን የሚወክሉ ሲሆን ለጥያቄዎች ተስማሚ ነው

የሚሉትን ምርጫ (✓) ምልክት በማስፈር ይመልሱ፡፡

| ተ.ቁ | የመስተጋብር ጠቋሚ ነጥቦች | በፍጹም አልስማማም | አልስማማም | ለመወሰን እቸገራለሁ | እስማማለሁ | በጣም እስማማለሁ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የተሳሳተ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች አበረታች ምጋቤ ምላሾችን እሰጣለሁ | | | | | |
| 2 | ብዙ ጊዜ እጅ ሳያወጡ ተጠይቀው ትክክለኛውን መልስ የሚመልሱ ወንድ ተማሪዎች ናቸው፡፡ | | | | | |
| 3 | በክፍል ተሳትፎ ውስጥ ፈቃደኛ ካልሆኑ ተማሪዎች ይልቅ ብዙ ጊዜ ፈቃደኛ ለሆኑት ቅድሚያ እሰጣለሁ፡፡ | | | | | |
| 4 | ሴት ተማሪዎችን የማበረታታው ከትምህርት ተሳትፏቸው ይልቅ ጥሩ ባህርይ ሲያሳዩ ነው፡፡ | | | | | |
| 5 | ተማሪዎች ጥያቄ ተጠይቀው መመለስ ሲቸገሩ ረዘም ያለ ጊዜ መስጠት ተገቢ ነው፡፡ | | | | | |
| 6 | በክፍል ውስጥ ያሉ ሴትና ወንድ ተማሪዎች ጥያቄዎችን የመጠየቅ እኩል ተነሳሽነት የላቸውም፡፡ | | | | | |
| 7 | ስም ጠርቶ ጥያቄ ከማስከተል ይልቅ ጥያቄዎችን ከጠየቁ በኋላ ተማሪዎችን በስም እየጠሩ ማሳተፍ ተገቢ ነው፡፡ | | | | | |
| 8 | ተማሪዎች ጥያቄ ተጠይቀው ሲሳሳቱ አሉታዊ የሆኑ ምጋቤ ምላሾችን እሰጣለሁ፡፡ | | | | | |
| 9 | ተማሪዎችን በተመሣሣይ ፆታ በቡድን ሥራ ከማሳተፍ ይልቅ ሁለቱም ፆታዎች በጋራ ቢሠሩ ይመረጣል፡፡ | | | | | |
| 10 | የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ለማጎልበት በተደጋጋሚ ቀላል ጥያቄዎችን መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡ | | | | | |

# ለመምህራን የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ

1. በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ያለውን የትምህርት አቀባበል ልዩነት ቢዘረዝሩ?
2. መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ ሁለቱንም ፆታዎች በእኩል ሁኔታ ማስተናገድ ይችላሉ? እንዴት?
3. ከመምህራን የሚሰነዘሩ ምጋቤ ምላሾች ለሴቶችና ለወንዶች በጥሩም ሆነ በመጥፎ መልኩ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ ይችላሉ ብለው ያስባሉ? ቢያብራሩ?
4. በክፍል ውስጥ ተግባራት ለሁለቱም ፆታዎች እኩል የሃላፊነት ድረሻ ይሰጣሉ? እንዴት? በምን መልኩ?

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገጸለው የድህረ ምረቃ ተማሪ ይህ ጥናት የራሴ መሆኑና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን የመረጃ ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ቶማስ ተቀባ ወርቁ

ፊርማ

አድራሻ አዲስ አበባ

የማስረከቢያ ቀን ነሐሴ 7 1999 ዓ.ም